مؤسسة دار الفكر
Dar Al-Fiker Foudation
فنفني – إثيوبيا

# إشكالية الاستبداد والفساد في التاريخ الإسلامي

عبد الحميد أحمد أبو سليمان

# የአምባገነናዊ አገዛዝና የማበላሸት ጣጣ በኢስላማዊ ታሪክ ውስጥ

አዘጋጅ፡
ዐብዱልሐሚድ አሕመድ አቡሱለይማን

ተርጓሚ፡
ዳር አል ፊክር ፋውንዴሽን

ፊንፊኔ- ኢትዮጵያ 2017

# إشكالية الاستبداد والفساد

# في التاريخ الإسلامي

## عبد الحميد أحمد أبو سليمان

# የአምባገነናዊ አገዛዝና የማበላሸት ጣጣ

# በኢስላማዊ ታሪክ ውስጥ

አዘጋጅ:

ዐብደልሐሚድ አሕመድ አቡሱለይማን

**ተርጓሚ፡-**

**ዳር አልፍክር ፋውንዴሽን**

የቅጂ መብት በህጋዊ መንገድ ለዳር አልፍክር ፋውንዴሽን
የተጠበቀ ነው።

***ፊንፊኔ- ኢትዮጵያ 2017***

**DF-E-TrBs-17/33**

**መታሰቢያነቱ**

**ለ**እድገት ጎዳና ወንድሞች

እውቀታቸውን በተግባር ላይ **ለ**ሚያውሉ ምሁራኖች

**ለ**መብትና **ለ**ፍትህ አብሳሪዎች

"ለሰዎች ከተገለጸች ሕዝብ ሁሉ በላጭ" የሆነችን ሕዝብ መገንባትን **ለ**ሚያበስሩ የሰውን ልጅ ና የቅኝ ስልጣኔን ከአምባገነንና ከበደል ከብልሽት ሃይሎች ለማዳን እንዲሁም ከእንስሳዊ ቁሳዊ ራስ ወዳድ ዝንባሌዎች በደሎችና እውነት ካልሆነ የወገንተኝነት የበላይነት ክርፋት

በላቀው ዓለም አበስራችኋለሁ የክብርና የወንድም አማችነት የመረዳዳት የሰላም ዓለም ይበልጥ ቅኑ ይበልጥ ትክክለኛ ለሆኑ ትውልዶች ዓለም።

**ማውጫ**

መግቢያ....4
**የአምባገነናዊ አገዛዝና የብልሽት ጣጣ**....4
ሚናዎችን ማዋሀድና መለያየት....5
የማበላሸትና የአምባገነንነት ጥምረት....7
ቁርኣናዊ ግንዛቤዎች....12
ሚናዎችንና ግዴታዎችን መከፋፈል....16
በኢስላማዊ አስተሳሰብ ውስጥ የመጡትን አባባሎች መከለስ....18
ሰውኛ ኢስላማዊ ሀገር....22
የለውጥ ጎዳና....30
**ከዘመናዊ ኢስላማዊ ቡድኖችና እንቅስቃሴዎች ተፈላጊው አቋም**....37
የመንገዱ ካርታ....37
ደዕዋ（ወደ አላህ መጣራት） ና ፖለቲካ....41
ሕዝቡ እሱ ነው ሞግዚት....44
የቡድኖች ፓርቲዎች ማለት ምን ማለት ነው？....45
የቱርኩ ተሞክሮ ሊከተሉት የሚገባ ትምህርት ነው....48
ደዕዋና ማደስ....49
በሰውኛ ኢስላማዊ አስተዳደር ና በዓለማዊ ሊበራሊስት
መሀከል ያለው ልዩነት....52
**ማጠቃለያ**....58

መግቢያ

በተከበረችዋ መካ ባስተዳደጌ ተፈጥሯዊ ሁኔታ ከልጅነቴ ጀምሬ ከምመለከተው አስደማሚ ልዩነት የተነሳ ግራ በመጋባት ውስጥ ነበርኩኝ፡ ያም በማነበው የነብይነት ዘመን ትውልድ ታሪክና _የዓለምን ገጽታ ከለወጡት በሰው ልጅ ታሪክም ውስጥ ለታላቅ ስልጣኔ መሰረት የሆኑ ስኬቶችን ያረጋገጠውን ትውልድ_ በምመለከተው በምታደመውና በምኖረው የኢስላሙ ዓለም ልጆች ሁኔታ መካከል እነዚያ በየዓመቱ የሐጅን ግዴታ ለመፈጸም በተለያዩ ቀለሞቻቸውና ቋንቋዎቻቸው እንዲሁም የዘር ሀረጎቻቸው ወደ መካ የሚተሙ ስለሆነም በመጀመሪያ የመረዳት ሁለተኛ ደግሞ የማስተካከል ሀሳብ ነበር እድሜዬን ሙሉ አእምሮዬን ተቆጣጥሮት የነበረው :

የተከበራችሁ አንባቢያን ሆይ ! ይህ ከፊትለፊታችሁ የምታገኙት ትንሽ መጽሐፍ ከበርካታ ስራዎች አንዱ ነው : የኢስላሙን ኡማ ጉዞና የኡማውንም ሆነ የስልጣኔውን ውድቀት መንስኤዎች ለመረዳት ከሞከርኩባቸው ስራዎች : ደካማና የተገለሉ የነተቡ ስርዓቶች : ተቋማቶች ባለቤቶች እስከሚሆኑ ድረስ።ለብዙ ጊዜም በኡማው ፖለቲካዊ ታሪክ ውስጥ የአምባገነናዊ አገዛዝና ማበላሸት ለማየል የሚያነሳሱ ነገሮችን ለማወቅ ሞክሬያለሁ : ያውም የተከሰተው የኢስላም ፍሬነገሩ ፍትህ ሆኖ ሳለነው።

የቻልኩትን ያህል የኡማውን ጉዞ ለመምራት -ከተከሰተው የኡማው ወጣቶች እንቅስቃሴ አንጻር በከፊል ኢስላማዊ ዓለም አህጉሮች ውስጥ የማበላሸትና የአምባ ገነናዊ አገዛዝ ስርዓቶችን መቃወምና መጋፈጥ እንዲሁም ቀሪ አህጉሮቿ አለመረጋጋት-ሞክሬያለሁ : ይሀውም ስህተቶችን እንዳን ደግምና እንቅስቃሴውን እንዲሁም የለውጡን አቅጣጫዎች ጥሩ የሰራን መስሎን እንዳናጨናግፍ ነው።

ኡማችንን ና ወጣቶቹን በውስጡ ያሉ የለውጥ አራማጆችንም መልካም ነገር ና ትክክለኛነት መምራት ይገጥማቸው ዘንድ አላህን እለምናለሁ፡ እግዣኝም ሆነ መገጠም ከሱ ነውና፡ እሱ በሁሉ ነገር ላይ ቻይ ነው።

## የአምባገነናዊ አገዛዝና የብልሽት ጣጣ

የተከበረው ቁርኣን በርካታ አመለካከቶችን እንዲሁም ስርዓቶችና ማህበራዊ ተቋማት መስራት ሊያደርጓቸው የሚገቡ መሰረቶችን መላ የሰው ልጆችን

ለመምራት አቅርቧል፡ እውን የማድረጉን መንገድ ና ተለዋዋጭ ታዳጊ መሳሪያዎቹን፡ የጊዜ ና የቦታ ሁኔታዎች እድገት ለሚጠይቁት እንዲሁም የሳይንስ ና የ እውቀት የሰው ልጅ ስልጣኔ መሻሻል ጣሪያ ለመስፋቱ/ከፍ ለማለቱ ትቶታል፡ ያንን ተከትለው ለሚመጡ ለውጦች ና እድገቶች እንዲሁም አቅሞችና ተግዳሮቶች።

ሙስሊም ተመራማሪዎች ከተገነዘቧቸው ይበልጥ ግልጽ አመለካከቶች- ከቅርብጊዜ ወዲህ- ምክር አስፈላጊ የሆነ ፖለቲካዊ ና ማህበራዊ ተቋም መሆኑን ነው፡ ለአስተዳደሩ የሚሰጥ ምክር አሊያም ከእርሱ የሚበረከት ችሮታ አለመሆኑን፡ በዚህ ጠባብ አመለካከት ውስጥ ምክርን መወሰን እሱ ነው የጭቆና ና የጭፍለቃ መሪዎችን የምክሩን ጉዳይ ችላ ማለታቸውን የሚገልጸው፡ ስለዚህም ( ሹራ) መመካከር - ኡማው ልባዊ ፍላጎቱን ና ውሳኔውን ጥቅሞቹን ና ሁለንተናዊ ሕይወቱን የሚያስኬድበት -መኖር ና የሚጠቀስ ተጽዕኖ ያልነበረው፡ እሱ ነው የኡማውን ስልጣኔ መፍረስ ና ህዝቦቹን ማዳከምም ሆነ ማራቅያቀለለው፡ ይህውም ነገር ዛሬ የመመካከርን ተቋም በድጋሜ ለመገንባት ና ፖለቲካዊ ዜጋዊ ኢስላማዊ ስርዓት ተጨባጭ ውስጥ ለማንቀሳቀስ የግድ የሚለው እሱ ነው።

የተከበረውን ቁርአን ንባብ መድገም ና ማስተንተኑ ላቅ ያለ ና የከበደ አስፈላጊነት አለው፡ ለ አጠቃላይ ግንዛቤ ማንበቡ የግድ ነው፡ ለምክክር አመለካከትም ብቻ አይደለም፡ ይልቁንም የተከበረው ቁርአን ያመጣቸውን ሌሎች በርካታ አመለካከቶችንም ጭምር ነው፡ እነሱም የ ማህበራዊ ኢስላማዊ ዘመናዊ ስርዓት ተቋማትን አመርቂ ና ተስማሚ በሆነ መልኩ ለመገንባት የግድ የሆኑ አመለካከቶች ናቸው፡ የትምህርት ና የዳዕዋ ተቋሞችም ከነሱ ይመደባሉ።

## ሚናዎችን ማዋሀድና መለያየት

ሙስሊም ተመራማሪዎች የ አላህ መልዕክተ ኛ (ሰ.ዐ.ወ) በሕይወታቸው ይወጧቸው የነበሩትን ሚናዎች ባህሪ የአይነት ብዛት ለመገንዘብ በበቂ ሁኔታ አልነቁም፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በአንድ ጊዜ ወሕይ የሚወርድላቸው፡ አድራሽ መልክተኛ፡ ዳዕዋ አድራጊ/ሰባኪ፡ የሐገር መሪ፡ የማህበረሰብ ገንቢ ነበሩ፡ እነኝህም ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ህልፈት በኋላ ሙስሊሞች ከፊሉን ከከፊሉ ሊለዩቸው የግድ የሆኑ ሚናዎች ነበሩ።

የነብይነት ና በመልዕክተኝነት ማዕረግ ላይ ሆኖ መልዕክትን ማድረስ የ አላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.) በማለፋቸው ተጠናቀቀ ሆኖም ግን ሱፊያዎች ና ሺዓዎች የቻሉትን ያህል ለዚህ ሚና ቀጣይነት ሰርተዋል፡ ያ ምናቦቹ በመሪዎች ና በ አላህ ወዳጆች እንዲሁም በጥብቆችና በሚነሳሱ መንፈሶቻቸው እዉን የሆኑ።

ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንደ (ዳዒ) ወደ አላህ ተጣሪናእንደ አስተማሪ የነበራቸው ሚና ከህልፈታቸው በኋላ ከመንግስት መሪ ና ከ አመራር ከስልጣን ተቋማት ሚና መለየቱ ይገባ ነበር፡ የመንግስታት ና የፖለቲካ ፓርቲዎች ተቋሞቻቸውም ሊወክሏቸው ከሚችሉት የፖለቲካዊ ና ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ተሰሚነት ባለቤቶች ና እነሱን የሚወክሉ ሰዎች አመለካከቶችን የሚገልጹ ፖለቲካዊ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እቅዶችም ጭምር መለየት ነበረባቸው።

ስለዚህም የ ዳዕዋን ና የትምህርትን ግዴታ ከ ፖለቲካዊ ባለስጣናት ና ከህግ አስፈጻሚ ባለስልጣናት ግዴታ መለየቱ የግድ ነው፡ ይህውም የ ህዝቡ የጋራ ጥቅሞች ና ክብሮቻቸው እንዳይደፈሩ ነው፡ ሃይማኖት ና ቅድስነቱ ከፖለቲካ አንጻር የብልሹ ሃይሎችን ጥቅሞች በማገልገል ላይ እንዳይውል ነው፡ ይህ መለየት ካልተረጋገጠ/እውን ካልሆነ የአንባገነናዊ አስተዳደርን ወደ ማጠናከር ያደርሳል በመቀጠልም የብልሹነት መስፋፋት ይመጣል፡ የሰው ልጆች በተፈጥሯቸው ድክመት ይፈራረቅባቸዋል፡ ቁጥጥርና መተሳሰብ የጠፋ ጊዜስ እንዴት ይሆን ! !

ከፊል የወትሮ (ዑለማኦች) /ምሁራኖች ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) በሕይወታቸው የተወጧቸውን ሚናዎች አይነት ብዛት አመለካከት የተረዱ ከመሆናቸውም ጋር በተለይም የመልዕክተኝነትና መልዕክት አድራሽነትን ሚናና የአስተዳደር ሚና፡ ነገር ግን በመልዕክት አድራሽ ነብይነት ሚናና በዳዒ (ወደ አላህ ተጣሪ) ና አስተማሪ ሚና መካከል የነበረው ልዩነት እነሱ ዘንድ ግልጽ አልነበረም፡ በፈጣን ሁኔታዎችና ስር በሰደዱ ዉርሶች ወሰን ባለፈ ጥቅም አባራሪነት (ነው ይህ የሆነው) የመጀመሪያውን ዘመን -ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ህልፈት ቡኋላ-የማህበራዊ ፖለቲካዊ ስርዓቱን ባጋጠሙት አደጋዎች (ምክንያት ) የትክክለኛ አመራር ስርዓት ከፈረሰና የጎሳዊ አመለካከቶች የሀገሪቱን ስርዓት ከተቆጣጠሩ በኋላ፡እንዲሁም በእስልምና ውስጥ የገቡት አህጉሮችና ህዝቦች ባህሎች ከተሰራጩ በኋላ፡የስልጣን ሰዎችና ያለ አግባብ ይዞታ አስፋፊዎች ጭቆናም ከተስፋፉ በኋላ፡ ጥቅሞቻቸውና

የደጋፊዎቻቸውም ጥቅም ጥፋቶቻቸውም ( ከተስፋፋ በኋላ ነው ይህ መደበላለቅ የመጣው) የተጠቀሰውን የመዲናን ትምህር ቤት ሰዎች መሪዎችንም ሆነ ተመራማሪዎቹን ማስወገዱ ይደግፋል፡ እነሱን ወደ ተመራማሪዎችና ትምህርት ነክ ጉዳዮችም ብቻ እንዲሁም ወደ ደጋፊዎችና ሰራተኞች ማግኛ ምንጭ መቀየሩ ይህንኑ ያረጋግጣል፡ ይልቁንም ጥቅሞቻቸው ከገዢ ፖለቲከኞች ጭፍራ ጥቅሞችና አንባገነነታቸው የተግባሮቻቸውም ጥፋት ጋር የሚያያዝ ጭፍራ መፍጠሩ ይህን ያጠናክራል፡ በመቀጠልም የሃይማኖትን አመለካከትና ግቦቹን ከፖለቲካዊ ሕይወት ማስወገድ፡ የጊዜው ግንባታዊና ኢኮኖሚያዊ ባህሪ ያለምንም ለውጥ ለረጅም ጊዜ መቆየቱ የምርጥ ፖለቲከኞችንና ደጋፊዎቻቸውን አላማዎች እውን በማድረግ ረገድ በእርግጥ ሰርቷል፡ እንዲሁም በአብዛኞቹ ምሁራኖች (ዑለማኦች) ና አመለካከት ውስንነትም (ተሳትፏል) ወደ ቅጂና ማመሳሰልም እንዲያዘነብሉ አድርጓቸዋል፡ አመለካከታቸውንና ሚናቸውን በቅርጻዊና ግላዊ በኩል ወስኗል።
እንደዚሁም ለማሰብ አቅም ማነስ ለአድማስና ተግባር ውሱንነት ዳርጓቸዋል፡ የሕይወት ቁሳዊ ጥቅሞች ተጽዕኖ-ለተጨባጩ ጉዳይ እጅ በመስጠት-በነብይነት ጊዜ የነበሩትን የህግ አጠቃቀሞችና አመራሮቹን አስተምህሮቹንም የቃልበቃል ትርጉም ላይ እዲገፉ አድርጓቸዋል እነዚያ በአጠቃቀማቸው አቅጣጫዎች በነብዩ ጊዜ የነበረውን ማህበረሰብ ያናገሩትን የተመለከቱ ሁኔታዎች።
ስለዚህም ከነሱ አብዛኞቹ ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል-በከፊላዊና መረጣ መልኩ፡ ጊዜው ሳይደርስ በተፈጠረ መልኩ በተጣመመ መልኩ -ጥቅሶቹን ያለ አንዳች ለውጥ ቃልበቃል በመተርጎም፡ የቁኣን ህግጋት አጠቃላይ አመለካከቶች ላይና በጊዜም ሆነ በቦታ የማይገደቡ ትርጉሞቻቸውና አላማዎቻቸውም።
አተገባበራቸውን በማሻሻሉ ላይ በማደስም ሆነ በማያቋርጥ ጥረት አልሰሩም፡ ሕያውና ክፍት በሆነ ፖለቲካዊ ማህበራዊ ተጽዕኖቹ ጋር የሚጣጣም፡ -በዚህ ሁሉም - ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) አመለካከቶችንና አጠቃላይ የሸሪዓ ግቦችን በህዝባቸው ሁኔታዎች ላይና በጊዚያቸው ዘመናዊና የቦታ ሁኔታዎች ተግባራዊ ካደረጉት ጥበብ የሚጠቅም በሆነ መልኩ። ይህ ክስተት በኢስላማዊ ምርምር ውስጥ - እንደሚታወቀው-በ"ማመሳሰል"ና "የምርምር በር መዘጋት" ክስተት ይታወቃል የተገለሉ የፈጠራ አብሪ ጀግኖችን ከመለየት ጋር፡ እንደዚሁ የኢስላማዊ ሃይማኖታዊ ምርምር-ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በግድ- በከፊላዊና በመረጣ ታወቀ እንዲሁም ነብያዊና ቅርሳዊ ጥቅሶችን በማደን ላይ በማጋነንና በቅድስነታቸው

በስተጀርባ መጠለል፡ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ቅድስናን ያላበሷቸው፡ ይህ ጉዳይ የ ሃይማኖትን ሚና ወደ ማግለልና በአሉታዊ መልኩ ምርጥ ፖለቲከኞችን አምባገነንነታቸውንና ጥፋቶቻቸውን በማገልገል ላይ ስኬታማ ወደ መሆኑ አድርሷል።

## የማበላሸት ና የ አምባገነንነት ጥምረት

አምባገነንነትና ማበላሸት የተያያዙ ሁለት ነገሮች ናቸው፡ አምባገነንነት በተለምዶ ህዝብን በማስተዳደር ና ባለ አደራነትን በህዝቡ ላይ በመጫን ቅርጻዊ ና የውሸት አሳሳች በሆኑ እምነቶች በህዝቡ እጣፈንታዎች ላይ የ በላይነት ና ቁጥጥር ይከታተላሉ።

የአምባገነን ሃይሎችን ተግባር ከሚያቃልሉ ይበልጥ ግልጽ ነገሮች፡ ህዝቦችን በማሸበር ተግባሮቻቸው ላይና በውሳኔዎቻቸው በሁሉም ጉዳዮቻቸው አምባገነን በመሆናቸው ላይ ህጋዊነትን ለማላበስ፡ የሰዎችን ግንዛቤ ወደማድከም የሚያደረርሱ ፖለቲካዎችን ማስረጽ፡ እውቀታቸውን ና ተሞክሯቸውን ውጫዊ ወደማድረግም፡ የህዝቡን እሴቶች የሚንከባከቡና የሚጠብቁ የትምህርት ና የመረጃ የህገመንግስት ተቋማቶችን ሚና ወደማራቅ የሚያደርስ። በዚህም ማህበረሰቡ በተዘጋ ቀለበት ና አጥፊ የሆነ አዟሪት ውስጥ ይገባል።

የግንዛቤ ድክመት ወደ አምባገነንነን ያደርሳል፡ እሱ ደግሞ በበኩሉ ወደ ብልሹነት ያደርሳል፡ በመቀጠልም ወደ ተጨማሪ አላዋቂነት ና የግንዛቤ ድክመት እጅ መስጠትና መቅለስለስ ወደተጨማሪ አምባገነንት፡ ተጨማሪ ብልሹነት። ይህ ነው የህዝባችን መጨረሻ የሆነው ከክብርና ከዝና ከሃይል በኋላ።

ስለዚህም ህዝቦች በሕይወት ስርዓታቸውና በስልጣኔ እድገታቸው ለግንዛቤ እድገት የሆኑ ተቋሞችን መገንባት አለባቸው።

ባለስልጣኖችንና ጉልበተኞችን ረዳቶቻቸውንም ከሞግዚትነት ተግባራትና ከማጥፋት፡ መከልከል፡ ህዝቡን በ ጫንቃዎቻቸው ላይ ወደሚቆጣጠሯቸው አላዋቂዎች ከመቀየርም ነፍሶቻቸውን ተቀናቃኝም ዳኛም የሚያደርጉ ከሆኑት ።

ያለ ግንዛቤ ያለ አንድነት ና የ ልጆችን አስተዳደግ ያለ ማሳመር ያለማስተማርና እነሱን ብቁ ያለ ማድረግ፡ አምባገነንነትና መበላሸት አይነቀሉም፡ ኡማውም ከአፈጻጸም ብቃት የግድ የሆነውን ያህል ለማግኘት አይችልም በማህበረሰቡ ውስጥ የሃይሎችንና መመዛዘን እውን ማድረግ አይችልም።

አምባገነንነት ና ብልሹነት የተያያዙ አንዱ ሌላውን የሚመግብ ከሆነ ይህ በማህበረሰቦች ሕይወት ጥምጥም አፍራሽ መጥፎ ገድ የሆነ ክብ ቀለበት ሊሰበር አይችልም ኡማው -በተመራማሪዎቹና የ ስነ ትምህርት ባለሙያዎች የለውጥ አቀንቃኞች ጀግናና ታማኝ ትግሎች - የፍጥረተ ዓለሙን ስልጣኔያዊ አመለካከቶቹን ካላስመለሰ በስተቀር ፡የአመለካከቱን ስልቶች ካላስተካከለ፡ ስልጣኔውን ካላጣራ፡ የትውልዶቹን አስተዳደግ ካላሳመረ ፡የስርዓቶቹን ግንባታ ካላስመለሰ፡ የማህበራዊና ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ የገንዘብ አያያዝ ትምህርታዊ፡ ስብከታዊና የመረጃ ተቋማቱን ካላስመለሰ፡ የሕዝብ ደንብ ና ስርዓት ስልጣን ወደ ህዝቡ ካልተመለሰ፡ የተመራማሪዎችና የ ስነትምህርት ባለሞያዎች ፡የለውት ተቀናቃኞች እንቅስቃሴዎች ካልተገለጹና፡ የስልጣኔያዊ ፍጥረት ዓለማዊ እይታን በድጋሜ ለመገንባት አስፈላጊውን ትኩረት ካልሰጠቻት፡ የአስተሳሰብ መንገድ ደህንነትን ፡ስልጣኔ ማጣራት፡ የስነትምህርት ስልቶችን ማሳመር፡ የማስተማር መንገዶች ደህንነት የተለያዩ የማህበረሰቡን ተቋማት መገንባትና የአፈጻጸሟ ደህንነት።

ያለዚያ ኡማውን ለማሳደግም ሆነ አቅሙን ለማጎልበት የሕይወትና የግንባታ የፈጠራ ፍላጎቱን በውስጡ ለማንቀሳቀስ እድልም ሆነ ተስፋ የለም።

በርግጥ የሁለቱ መሪዎች አቡበክረ ሲድቅና ዑመር ኢብኑልኸጣብ ዘመን ስኬት እንዲሁም የመሪው ዑስማን ዘመን መጀመሪያ ላይ፡ ለሁላቸውም አላህ ይውደድላቸውና የደዕዋና የስነትምህርት የማስተማር ሚና ከስልጣን ና ከአስተዳደር ሚና ያልተለየ ከመሆኑ ጋር ስኬታማ መሆኑ የአስተዳደሩና የሰዎች ቅደምተከተል ሚናዎቻቸውም ሰሓባዎቹ ታማኝነት (ኢኽላስ) ስላላቸውና በነዚህ ጊዚያቶች ውስጥ ገለልተኞች ስለነበሩ፡ በነብይነት ጊዜ ሁኔታውና ስርዓቱ በነበረበት ቀጥሏል።

ከነዚያ አስሓባዎች ብዙዎች በመሞታቸውና ሰማእታት በመሆናቸው ከነሱ የቀሩት አብዛኞቻቸው በመድከማቸው፡ በእድሜም ስለገፉ፡ የሰዎችና የጊዜ ሁኔታዎች ሃገር ከመስፋቱ በኋላ በመለወጡ በድሎችም መስፋፋት፡ የሀገርና የአስተዳደር ስርዓትም የዐረብ ዘላኖች ጎሳዎች የድል ጦርሃይሎችን በማሸነፋቸው ሰበብ የፖለቲካ መሰረቱ ከሚያደቡ ተቃዋሚ ግዛቶችም ጋር ትግል በመግባታቸው ፡በስርዓቱ ባህሪና፡ በግለሰቦችም ሆነ በሚናዎቻቸው ውስጥ በወሕይ (ራዕይ) የተደገፉት ነብዩ (

ሰ.ዐ.ወ.) ካለፉ በኋላ ለውጦችና ስህተቶች ግድፈቶች ከመከሰት ሊቀር የማይችል ነበር።

-ከነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ህልፈትና ከጊዚያቸው መጠናቀቅ በኋላ -በዬትኛውም ጊዜና ቦታ ውስጥ የሰዎች ሁኔታ እኩል ከመሆን አይቀሬ ነበር ከሃይማኖቱና ከመርሆቹ፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የወገናቸውን አመራር ሲያስተዳድሩ ካደረጓቸው አቅጣጫዎች ማስያዞች መጠቀም ፡ማለትም በማንኛውም ሰውና ማንኛውም ኡማ ማንኛውም ህዝብ ላይ - በተቻለው አቅም -የሃይማኖቱን እይታና መርሆቹን እሴቶቹን ማክበር፡ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጥበብም መጠቀም አለባቸው ኢስላማዊ እይታንና እሴቶቹን መርሆቹን ተግባራዊ በማድረግና ግቦቹንም ሆነ አላማዎቹን በወገናቸው ሁኔታዎችና ጊዜ ላይ እውን በማድረግ፡ በዬትኛውም ጊዜና በዬትኛውም ቦታ ሃይማኖቱን ይይዛሉ፡ የቻሉትን ያህል የሙጥኝ ብለው መያዝም አለባቸው አላህ እንዲህ ይላል

فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ مَا ٱسۡتَطَعۡتُمۡ وَٱسۡمَعُواْ ﴿١٦﴾ (التغابن: 16 )

"አላህንም የቻላችሁትን ያክል ፍሩትት" (አት-ተጋቡን፡16) ።

በዚህ በተጠቀሰው የነብያዊው ጊዜ እንዲቀጥልና ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ካለፉ በኋላ የጊዜም ሆነ የቦታ ቅጂ ተግባራቶቹና ቅደምተከተሎቹ ቀጣይ እንዲሆኑ አልተፈለገም፡ አጠቃላይ ሙስሊሞችና የትእዛዝ የምርምር የአመለካከት የልምድ ባለቤቶች ተስማሚ ከመሆን አልተወገደም ብለው የተመለከቱትና የሃይማኖታቸውን ግቦችም ሆነ የነሱን ጥቅሞች እውን የሚያደርግ ሲቀር፡ ከሁኔታዎቻቸው አዲስ ለሚፈጠረው ተስማሚ የሆነ ነገር መፍጠርም አለባቸው። ለውጥ አልባነትንና ዝንጉ ጭፍን መከተልን የሙጥኝ ብለን ከተያያዝን፡ የዚህ ትርጉሙ የነብይነት ዘመንና ኢስላማዊ መልእክቱም፡ የሰው ፈጠራ ነው፡ ጊዜውን ይይዛል፡ አላማዎቹን ይጨርሳል፡ ያልቃልም፡ ስልጣኔያዊ ተግባሩም ሁኔታዎች በመቀያየራቸውና አቅሞች ጉዳዮች ተግዳሮቶች በማደጋቸው ይጠናቀቃል ማለት ነው። እነዚያ አብዛኛቹ የድል አድራጊን የጦር ሃይል ሊከውኑ ዘንድ የጎሰኝነት የዘረኝነት ባህሪዎች በነሱ ላይ የተላከኩ ከመሆን ያልተወገዱ፡ በዚህም የቅን ምክትልነት ዘመንና የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ትውልድ ዘመን፡ የሃገራቸውም ዘመን ተጠናቀቀ።

እዚሁም የጥራትና የስልጣኔ መውረዱ ቀስበቀስ ጀመረ፡ የስልጣኔ ጎማ ከመሽከርከሩ እስከቆመና ግንባታውም እስከፈረሰ ድረስ፡ ኢስላምና ስልጣኔው እስከተገለለ ድረስ።

ከኡመያዎች አገር መቋቋም ጋር፡ የዘረኝነትና ጎሰኝነት እንዲሁም ህዝበኝነት ተግባራት ግልጽ ሆኑ፡ አምባገነንነትና በደል ኢ-ፍትሃዊነት የተሞላበት አስተዳደር በኢስላማዊ መንግስታቶች ስርዓት ውስጥ ስር ሰደደ፡ ይህንንም የተከተለ ሁሉ ከጥፋቶችና በደሎች፡ ያም እሱው ህግ ሆነ፡ ከሱ ውጭ ያለውም ህግ ያልተከተለና ያንን ህጉን የሚያጠናክር ሆነ።

አምባገነንነትና በልሹነትን ማጠናቀቅ ግንዛቤን መፍጠር ይጠይቃል፡ ግንዛቤው ለቤተሰብ ትኩረት ከመስጠትና ከአባትነት ግብረገብነት ጀምሮ የሚነሳ የሆነ፡ የህጻኑን ስሜት ለማዳበር ሚናው እጅግ አስፈላጊ ስለሆነ ነው።

እንደዚሁም የስነትምህርትና የትምህርት የደዕዋ ተቋማት ነጻነትም ሊያስቀሩት የማይቻል ጉዳይ ነው፡ በነሱ የተለየ ነጻ ተቋም ወይም ተቋማት ማቋቋም የነሱን ጉዳይ ስልጣኑን ቀጥታ ወደ ህዝብ ማስረከብ ነው፡ የሙስሊሙን ማንነትና ስሜቱን መገንባት ስልጣኔውን ማጣራት ነጻ ሚናውን ለህዝቡ ማስቻል።

የኢስላምን ኢኮኖሚያዊ አመለካከቶች ማንቀሳቀስ አይቀሬ ነገር ነው፡ የህዝቡን የገቢ ምንጮችና ሃብቶቹን አጠቃላይ ጥቅሞቹን ለመጠበቅ፡ የጉልበት የስልጣን ባለቤቶች ፖለቲከኞች ከአስተዳደር የማከናወኛ ተቋማት የነሱ ደጋፊዎችም፡ በቁጥጥራቸው ስር ከማዋልና“ በመካከላቸው ተዘዋዋሪ ምርኮ“ ከማድረግ በመጋረድ፡ እነዚያ ህዝቡን ወደነሱ ፍላጎት ለማምጣት የሚስገድዱ፡ ከፖለቲከኞችም ጋር ቃል የሚገባቡ፡ እነዚያ ከነሱ ጋር የሚመሳጠሩና ፖለቲከኞቹና የ አስተዳደሩ አካሎችም ለነሱ መሳሪያዎች ይሆናሉ።

የዜጋ ግንዛቤ መኖርና ሃላፊነቱም የ ሃይማኖትን የእሴቶችን ሚና በማደላደል፡ የአስተዳደሩን ባለስጣኖችና የግል ጥቅሞች ባለቤቶችን ድርጅቶች አቅጣጫ ማስያዝና መቆጣጠር እሱ ነው ተግባራዊው መንገድ ያ ባለስጣኖች ህዝቡን ከማሳሳትና ከአምባገነንነት ብልሹነትና ህዝቡን ከማበላሸት ተግባር እንዳይደላደሉ የሚጋርድ፡ የህዝቡን ስርዓትና መብቶች ጥቅሞችና የገቢ ምንጮች ከጥፋትና ከማባከን የሚጠብቅ፡ ከህዝቡ ፍላጎቶች ጋር እንዲስማሙ አቅጣጫ የሚያስይዛቸው የህዝብ አገልጋይ ተቋማቶችን የሚያሳምር፡ የህዝቡን የፈጠራ አቅም የሚያፈነዳ፡ በአስተዳደሮችና ፖለቲካዊ ፕሮግራሞቻቸው ላይ፡እንዲሁም በአስተዳደር ተቋማት ላይ ሞግዚት የሚያደርጋት በተቃራኒ ሳይሆን።

የሰዎች ሕይወት ገጽታዎች ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) በኋላ - ለረጅም ጊዜ -በአንጻራዊ መርጋት በእርግጥም ታውቃለች፡ በጊዜው ባህሪ ምክንየትና ምሁራኖችን ተመራማሪዎችን ጨቋኝ የሆኑ ምርጥ ፖለቲከኞች በጫኑት ፖለቲካዊ መፈናቀል ከህዝቡ ጠቅላላ ሕይወት፡ በአጠቃላይ ሕይወት ውስጥ ሚናቸውና ግንዛቤን በማስፋፋት ተግባራቸውም፡ ተቋማትን በመገንባትና በማስተዳደግ ደከመ፡ በምሁራኖችና ምእርጥ ተመራማሪዎች ፊትለፊ የተከበረውን ነብያዊ ሱና ቃልበቃል መያዝ እንጂ አማራጭ አልነበረም የሕይወትን ቅደምተከልና፡የአስተዳደርን፡ የፖለቲካዊ ጉዳዮችን በሚመለከት፡ እርሷ በጥቅሉ የጊዜና የቦታ መጠኖችና ስፋቶች ባለቤት ከመሆኗ ጋር።

የፖለቲካዊ ማራቁ ምሁራኖች እነዚህ ቅደምተከተሎች ዘንድና በቅድስነታቸው በስጀርባ ወደመደበቅ አድርሷል፡ በተለይ በግላዊ ጉዳዮች ሜዳ፡ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ ) ዘመን በኋላ የሰዎችን ሕይወት በዐረቢያ ደሴትም ሆነ ከሱ ውጭ፡ መላ የሰውን ልጅ ያዳረሱ ችግሮችና ክስተቶች የተፈጠሩ ከመሆናቸውም ጋር ይህ ነገር ተከሰተ። የዚህ አይነት የነብያዊ ሱና አያያዝ ውጤቱ የምሁራኖች/ዑለማኦችና የምርጥ ተመራማሪዎች ለተከበረው ቁርኣን ትኩረት መስጠትና ማስመንጨት እሱን መያዝ ማነስ ሆነ ፡እሱ ያ በአመለካከቶቹ በእሴቶቹ በመርሆቹ የጊዜና የቦታ ገደብ የለሽ ጥልቀቶቹ የተለየ ሆኖ ሳለ ፡እነዚያ ተግባራዊ የህይወት ቅደምተከተሎችን ለማበልጸግና የዘላለማዊውን መልዕክት ግቦች እውን በሚያደርግ ነገር ለማደስ መልሶ ማጤንን የሚያመቻቹ ፡በዬትኛውም ጊዜና ከተማ እንደ ሁኔታዎቹና ለውጦቹ ።

## (ቁርኣናዊ ግንዛቤዎች)

በዚህ አገባብ ውስጥ አትኩሮታችንን ወደ ሁለት የተከበሩ አንቀጾች እናዞራለን ፡ የደዕዋንና የሥነ-ትምህርትን የሃይማኖታዊ ትምህርትን ጉዳይ ወደ ማህበራዊና ሥነ-ትምህርታዊ ተቋም ማስደገፍን የሚያረጋግጡ ፡ -ከመጀመሪያ- በሙስሊሞች ላይ ነጻ ተቋም አድርገው ማቋቋም ነበረባቸው ፡በህገመንግስት ተቋምና በፖለቲካና ቁጥጥር ፡ህግ ማዘጋጀት ተቋም ፡የፍርድ አስፈጻሚ ተቋም ፡ማስተካከል ነበረባቸው ፡ከመሰረታዊ ማህበራዊ ስርዓት ተቋማቶች እንደማንኛውም ሌላ ተቋም ፡የደዕዋን የሥነ-ትምህርት የሃይማኖታዊ ትምህርት ተቋም እንደሌሎች ህገመንግስታዊ

ተቋማቶች ነጻ ገንቢ ሚናዋን አመርቂ በሆነ መልኩ የምትወጣ ተቋም እንድትሆን ።

በዚህ ክበብ ውስጥ የቤተሰብን ተቋም በደዕዋና ግንዛቤ በመፍጠር በሥነ-ትምህርት በሃይማኖታዊና እሴቶች ትምህርት ማንቀሳቀስ ይካተታል ፣ በዓላማዎችም እንደዚሁ ፣እሷን ስኬታማ ለማድረግም ዘዴዎችንና መሳሪያዎችን ማሟላት ፣ከማግለል ችግር በመራቅ ፣የዲንንና የደዕዋን የእሴታዊ ትምህርትን ግንዛቤ ወደ ትርጉም የለሽ ባዶ መፈክሮች በመቀየርና በዓሎችን መውሊዶችን በማቋቋም ውሱን ማድረግ ፣እሱንም ለባለስልጣኖችና ፖለቲካዊ ፍልሚያዎቻቸው ድጋፍና እርዳታ ያላቸውን ሃይማኖታዊ መልሶች (ፈታዋዎችን) በማግኘት ተግባር ላይ ማዋልና በመጠቀም ፣ሃይማኖትንና ቅድስናውን ለማጠልሸት የፖለቲካና የስልጣን ሰዎች እንዲሁም የግል ባለጥቅሞች እሱን ተግባር ላይ በማዋል እሱን ፍርሃትና ሽብርን ለመንዛት ፣አፎችን ለመለጎም ፣አእምሮችን ለመሰረዝ መጠቀም ፣የጉልበት ባለቤቶችንና ድርጅቶቻቸውን ፣ለማገልገል ለስልጣን ሰዎችና ፖለቲካዎቻቸውም ለግል የግፍ ጥቅሞቻቸውም ለማዋል ።

እነዚያ የተከበሩ ሁለት አንቀጾች ወይም ሁለት ቁርኣናዊ ግንዛቤዎች የተባሉት እነዚያ በፖለቲካዊና ማህበራዊ ኢስላማዊ ሕይወት ስርዓት ውስጥ እነሱን በአግባቡ መረዳት የግድ የሆኑ ፣እነሱ የጠራና ከፍ ያለ ሲሆን የኣላህ አባባል ናቸው ፣

وَلْتَكُن مِّنكُمْ أُمَّةٌ يَدْعُونَ إِلَى ٱلْخَيْرِ وَيَأْمُرُونَ بِٱلْمَعْرُوفِ وَيَنْهَوْنَ عَنِ ٱلْمُنكَرِ ۚ وَأُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْمُفْلِحُونَ

﴿١٠٤﴾ (آل عمران:104

“ከናንተም ወደበጎ ነገር የሚጠሩ በመልካም ስራም ፣የሚያዙ ፣ከክፉ ነገርም የሚከለክሉ ሕዝቦች ይኑሩ እነዚያም እነሱ የሚድኑ ናቸው ”(ኣሊ-ዒምራን፡104) የኣላህ አባባልም ነው ፣

وَمَا كَانَ ٱلْمُؤْمِنُونَ لِيَنفِرُوا۟ كَآفَّةً ۚ فَلَوْلَا نَفَرَ مِن كُلِّ فِرْقَةٍ مِّنْهُمْ طَآئِفَةٌ لِّيَتَفَقَّهُوا۟ فِى ٱلدِّينِ

وَلِيُنذِرُوا۟ قَوْمَهُمْ إِذَا رَجَعُوٓا۟ إِلَيْهِمْ لَعَلَّهُمْ يَحْذَرُونَ ﴿١٢٢﴾ ( التوبة:122)

“ምእመናንም፡ (ነብዩ ጋር ካልሆነ) በሙሉ ሊወጡ አይገባም ከነሱ ውስጥ ከየክፍሉ አንዲት ጭፍራ ለመን አትወጣም (ሌሎች) ሃይማኖትን እንዲማሩና ወገኖቻቸውን ወደነሱ በተመለሱ ጊዜ እንዲጠነቀቁ ይገሥጹዋቸው ዘንድ (ለምን

አይቀሩም）”（አል-ተውባ፡122）እዚህ ቦታ “አል-ኡመህ” የሚለው ቃል ጭፍራ ማለት ነው አሊያም ህዝብ በዘመኑ ቋንቋ ተቋም ወይም ነጻ ድርጅት ማለት ነው። ስለዚህም መስጂድ የደዕዋ ተቋም ልብ ሊሆን ይገባል ፡የደዕዋና የማስተማር የትምህርት የሃይማኖታዊ ማሕበራዊ ትምህርት የመረጃ መንገዶችም የደዕዋና የሃይማኖት ትምህርት ተቋማትና የመረጃ ተቋማቶች ብቻ ከሚለዩባቸው ጉዳዮች መሆን አለባቸው ።

ህዝቡና ብቁየ ተመረጡ ተወካዮቹ የነዚህን ተቋማቶች አመራሮችና የአስተዳደር ሰዎች የነሱን ሃይማኖታዊ ስልጣኔያዊ አቅጣጫ ሰጪዎች የአፈጻጸም ተቆጣጣሪዎችንም ይመርጣሉ ፡በዚህም ለህግ አስፈጻሚ ባለስልጣን ፡ወይም በሃገር ውስጥ ልዩ ለሆነ ማንኛውም ሌላ ጭፍራ በነኝህ ተቋማቶች ላይ ምንም አይነት ቁጥጥርና ስልጣን አይኖረውም ።

ህዝቡ ለሃገር ፖለቲካና ህግ አስፈጻሚ ባለስልጣናት የትእዛዝና የአቅጣቻ ማሳየት ባለቤት ነው ።በዚህም የመታየት መጠን ሊጠራና ፡የሃይማኖታዊ ማህበራዊ አመለካከት ሊስተካከል ፡ሊያድግ ፡ሊለማና ሊታደስ ይችላል ፡ -ከአጠቃላይ መረጃ ተቋማቶች ጎንለጎን-ም የአምባገነንነት አገዛዝንና የማበላሸትን ምንጮች በማድረቅ እንዲሳተፍም ነው ፡ሃብቶችንና እጣፈንታዎችን በመጠበቅ ላይ ይረዳል ፡ የአስተዳደርና የአጠቃላይ ህይወት ተቋማቶችን በኢስላማዊ አህጉሮች ውስጥ ለመገንባት ።የሃይማኖት ትምህርት የደዕዋና ወደ ቀድሞው አብረሃማዊ

ሃይማኖቶች የመስበክ ተቋማቶች ተጽዕኗቸውና ስጦታቸው ንብብር ይበልጥ ውጤታማ መሆናቸው የሚቻል መሆኑን መገንዘብ አለብን የነዚህ ሃይማኖቶች በጊዜና በቦታ ውሱንት ባህሪ ባልነበር ፡በስተመጨረሻው እነዚህን ሃይማኖቶች ያጠቃቸው ነገር ከማፈንገጥም ሆነ ማበላሸት አፈታሪክና ከህኖታዊነት ባልነበረ ፡ ኢስላም ሊያስተካክላቸውና ለሃይማኖት የመምራት ሚናውን ሊመልስ የመጣ የሆነው ፡ከበኋላ በወደፊት ዓለምአቀፋዊ ጌዜና ተግዳሮቶቹ ውስጥ ከሰው ልጅ ሁኔታ ጋር እንዲስማማ ።

ኢስላም የመጨረሻው አምላካዊ መልከት ነው ፡ባለፉት መልዕክቶች ሁሉ ላይ ተቆጣጣሪ ነው ፡ኣላህ እሱን በመጠበቅ ቃል የገባው የተከበረው ቁርኣን እሱ ነው ለዚህ ሃይማኖት መሰረታዊና የመጀመሪያ ምንጩ ።

የምሁራኖች ትግሎች ሰሒሕ/ትክክለኛውን ነብያዊ ሱና ከዘገባም ሆነ ከጥቅሶቹ በኩል በርካታዎቹን ቃላትን ከመለወጥና ከቅጥፈት በእርግጥ ጠብቀዋል ፡በነሱ ውስጥ（ቁርኣንና ሱና）ነጻ የደዕዋ የግንዛቤ መፍጠሪያ የሃይማኖታዊ ትምህርት

የኢስላማዊ ባህል የመረጃ ተቋማቶችን በመገንባት ላይና እነዚህን ተቋማቶች ከስልጣንና ከአስተዳደር ተቋም በመለየት ላይ የሚረዱ መርሆችና አቅጣጫዎች አሉ።

በቁርአንና በሱና ውስጥ የህዝቡን ሃብቶች ለመጠበቅ ዋስትና ያለው ነገር አለ ፡ እንዲሁም የአጠቃላይ ጥቅሞቹን እጅ በማስቀመጥ ወይም በሃሰተኛ በዳይ የባለቤትነት መብቶችን ይገባኛል ብሎ በመሞገት ከመዝረፍና ከመቀማት የሚጠብቅ አለ ፡እሱ የአምባገነንነትንና ማበላሸትን ምንጮች በማድረቅ ዋና አካል ተደርጎ ይቆጠራል ፡እነዚህ ሁለት ጉዳዮች በፖለቲካዊ ታሪካችን ውስጥ በብዙ በኩል የአስተዳደርና የስልጣን ባህሪ ነበሩ እስካሁንም ድረስ አልተወገዱም ። በእርግጥም የህዝቡ ስርዓት ሁኔታ መላቅጡ የጠፋበት ሆኖ ተገለበጠ የሃይማኖቱ ንግግር -በማወቅም ሆነ ባለማወቅ- የሙስሊሙ ማሕበረሰብ ማለት እነሱ "እነዚያ የማያውቁ" ና"እነዚያ የማይረዱ" ናቸው ብሎ የተመለከተ ጊዜ ፡የአስተዳደርና የስልጣን ሰዎች ከሃይል ባለቤቶችም ከነሱ በስተጀርባ ያሉት እንዲሁም የትምህርት ማዕረጋት ባለቤቶች ፡የአካዳሚክ መስኮችና የሚያቃጭል ተሚያስተጋባ የትምህርት ማዕረጋት ባለቤቶች እነሱ"እነዚያ የሚያውቁትና የሚረዱት"የሆኑ ጊዜ ፡ በመቀጠልም በህዝቡ ላይ ባለ አደራ የሆኑ ጊዜ ምስቅልቅሉ ወጣ ።

በሃይማኖታዊ ወይም ማህበራዊ ሞያዊ ጉዳይ ውስጥ ከአዋቂዎችና ምሁራኖች የሞያተኞች የልዩ አዋቂዎች እውቀት ዬቱን ያህል እንኳን ቢሰፋ ሚናቸው ሃሳብን ከመግለጽና ከምክር ከመተግበር አያልፍም ፡ ፖለቲካዊ ውሳኔ ማስተላለፍ መብታቸው አይደለም ፡የህዝቡን ጉዳይ የሆነውን ፡የስልጣኔያዊ ተስፋዎቹን እውን እንዲያደርግና ፖለቲካዊም ሆነ ሕይወታዊ ጥቅሞቹን እንዲጠብቅ ።ከዚህ ውጭ ያለው እሱ ወረቀቶችን ማደባለቅ ነው ።

የሰዎችን ግንዛቤ እጥረትና ባለስልጣኖችም ሆኑ ረዳቶቻቸው የሚሞግቱትን መሃይምነት መሞገት ፡እርሱ ብልሹ ሙግት ነው ፡እርሱም ሰበብ ነው ፡እዚህጋ ጉዳዩ የፖለቲካዊ ምክርና የውሳኔ ጉዳይ ነው ፡እሱ ደግሞ የውሳኔ ባለቤት የህዝቡ መብት ነው "ነገራቸውም በመካከላቸው መመካከር ለሆነው " (አል-ሹራ፡38) ፡ እርሱ የምክክሩን ውሳኔዎች ተግባራዊ ከማድረግ የሚለያይ ጉዳይ ነው ፡ የአጠቃላይ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች በመመካከር መንገድ ይተገበራል ፡ከልዩ ባለሙያዎች ልምድ እንደሁኔታው ከመጠቀም ጋር ።

ህዝቡን በመሃይምነትና በድክመት ማጠልሸትን መሞገት እርሱ ውሳኔዎችን በመወሰንና የሕይወቱን ጉዳዮቹን አቅጣጫ የማስያዝ መብቱን ለመቀማት መፍቀድ

ብቻ ነው ፡የአምባገነንነትን አገዛዝ በመቀጠልም ማበላሸትን ማደላደል ነው ፡ምርጥ ፖለቲከኞችና መሳሪያዎቹ ሰራተኞቹ እነሱው አዋቂ ቅን ብሩሕ ባለአደራ እንዲሆኑ!!

መሐይምነት ወይም የግንዛቤ ድክመት ህዝቡ ዘንድ መኖሩን በፖለቲካዊ ማሕበራዊ ግንዛቤና ፖለቲካዊ ውሳኔ በማስገኘት ደረጃ ብንቀበል እንኳን ፡የዚህ ጉዳይ መፍትሄ በተጨማሪ ትምህርትና ማስተማር በማሳወቅ በመረጃ ፡በደዕዋ ፕሮግራሞችና በማሕበረሰቡ መቀበል ነው የሚሆነው ።

## (ሚናዎችንና ግዴታዎችን መከፋፈል)

የቀድሞ ጌዜ ሰዎች በሺዎች የሚቆጠሩ የመማሪያ መጽሐፎችን (ሙቱን) ና የግርጌ ማስታወሻዎችን (ሐዋሺ) አጫጭር ሞያዊ መጻሕፍቶችን ( ሙኽተሰራት) አላወቁም ነበር። ማንኛውም ሳያስቡትና ያለምንም መጨናነቅ ወይም ያለ ብልጣብልጥ ሀሰተኛ መከራከሪያ ያወቁት ነገር ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ህልፈት በኋላ የማሕበረሰባቸውን እንቅስቃሴና ፖለቲካዎቹን አቅጣጫ ለማስያዝ፡ እሱ የተከበረው ቁርኣንና የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) አቅጣጫ ማስያዝ እንዲሁም ያስቀመጡት ቅደም ተከተል ነው፡ የመመካከር የፍትህ የእዝነት የለውጥ የማቅናት መርሆችንና እነሱን ተጨባጭ ማድረግን በመያዝ፡ እነሱ የኢስላም መሰረታዊ እሴቶችና መርሆች ግቦቹ ናቸው አንዳንድ ጊዜ ከሃይማኖት የግድ የሚታወቁ በመባል የሚጠሩ ናቸው።

ከዚያ በስተጀርባ ያለውማ እሱ የልዩ ሞያና የመመካከር ዝርዝር ነው፡ ጉዳዮች የሚወጡባቸውና፡ ውሳኔዎች የሚተገበሩባቸው ዝርዝሮች ናቸው። ዑመር ኢብኑል ኸጣብ (ረ.ዐ) በርግጥም ይህን ተረድተዋል ቀጣዩን በተናገሩ ጊዜ፡ "አንተ የኸጣብ ልጅ"አብብ"ማለት ምን ማለት እንደሆነ አለማወቅህ አይጎዳህም"

ጥራትንና ልዕልዕና ወደሚገባው ኣላህ አባባል እየጠቆሙ ነው፡

وَفَٰكِهَةٗ وَأَبّٗا ﴿٣١﴾ (عبس: 31)

"ፍራፍሬንም ገለባንም (ያበቀልን መሆናችንን ይመልከት) "{ዐበሰ፡ 31} ማለትም የፖለቲካዎችና የአጠቃላይ ጥቅሞችን መረዳት ከአካዳሚካልና ከፈትዋ ሞያዊ ጉዳዮች የተለየ ነው፡ እንዲሁም ከዳኝነት ውሳኔዎችና ፖለቲካዎችን ውሳኔዎችን

ተግባራዊ ማድረግና ይህ ነገር የሚጠቀመውን ሞያዊና ቴክኒካዊ እውቀቶች፡ ከሕይወት ጉዳዮች ዓይነቶች በዬትኛውም ዓይነት ውስጥ።

እንዲህ አይነት ቴክኒካዊ ተግባራዊ ጉዳዮች እነሱ ናቸው ጥልቀትንና ልዩ ሞያዊ እውቀት የሚጠይቀው፡ የህክምና መድሃኒቶችንና ውርሻዎችን ማከፋፈልን ይመስል የውሎችን ደህንነት ይመስል

የጉዳዩ ብርሁነት ይጨምራል በእርሻ ጉዳዮች በፖለቲካዊና በሞያዊ ቴክኒካዊ መካከል የለያየን ጊዜ። ለፖለቲካዊ አመራሮችና ለህዝባዊ መሰረቶቻቸው የአጠቃላይ የሀገርን እርሻ ሁኔታ ባህሪውንም አቅሞቹንም፡ በደንብ ማወቅ አስፈላጊ ነው ፡ተስማሚ በሆኑ እርሻዊ ስቶች ላይ ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ፡የተለያዩ ፖለቲካዊ ግምቶችን በዚህ ባህሪና ችሎታዎች ክበብ ውስጥ ለመያዝ።ሞያዊ የእርሻ እውቀት የሆነን ምርት መለያ ባህሪያትና የአዘራሩን ሁኔታ፡የመዝሪያ ጊዜዎችን፡ ለሱ አስፈላጊ የሆኑትን የማዳበሪያ አይነቶች በደንብ ማወቅን የሚጠይቅ ሲሆን፡ ገበሬዎችን ለመምራት እንዲዘሩትና እንዲያመርቱት ለገበያ አቅርበው እንዲሸጡት እነሱን ለማነሳሳት የግድ የሆኑትን እውቀቶች ለሰፊው ህዝብ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ ግምቶች ጋር በሚስማማ መልኩ መረዳትን ይጠይቃል።

ይህ ምሳሌ ከህይወት መስኮች በሁሉም መስክና ሜዳዎች ላይ፡ ለምሳሌ የትምህርት ነክ ፍልስፍናዊና የፊቅህ ህጋዊ የህክምና ጤናዊ መስኮች። ህዝቡንና ፖለቲካዊ ተወካዮቹን የግድ አጠቃላይ በሆኑ ፖለቲካው ውሳኔዎችን በመወሰን ረገድ ለነቅፉ ቦታ የለውም፡ ህዝቡና የፖለቲካ ሰዎች ከነዚህ ከሕይወት መስኮች በዬትኛውም የግድ የሞያዊ የቴክኒካው ልዩ ባለቤቶች አይደሉም በሚል ስም። በአስተዳደር ባለስልጣን (የህግ አስፈጻሚ ባለስልጣን) ና በደዕዋ ጉዳዮች በሃይማኖታዊ ባህላዊ ማስተማር ጉዮች መካከል ባለው ትስስር ውስጥ ያለው አመለካከታዊ ፖለቲካዊ ማህበራዊ ኢስላማዊ ማቀላቀል አለመቀጠሉ አስፈላጊ ነው። በመጠያየቅ ጊዜን ማባከን አስፈላጊ አይደለም።

የባለስጣኖችን እጅና ጥቅሞቻቸውን ብሎም የረዳቶቻቸውን እጅ በሀገርና በማህበረሰብ ውስጥ በሃይማኖት ተቋማቶች ላይና በሃይማኖት በደዕዋ በስነ-ትምህርት በማስተማር በባህል በመረጃ ተቋማቶች ላይ ጫና ከመፍጠር መካከል አወንታዊ ነገር ተደርጎ ይቆጠራል ወይስ አሉታዊ ነገር? እሱ (መለየቱ) ሃይማኖትንና እሴቶችን ከሃገርና ከፖለቲካ መለየት ነውን፡ ወይስ እሱ ፍሬ ነገሩ ሃይማኖትንና ደዕዋን ማደላደል ነው የባለስልጣኑን እጅ ሃይማኖትንና መርሆቹን እሴቶቹን ህግ በማፍረስ ወይም በማገልገል ወይም በመበዝበዝ የአስተዳደርና

የአመራሮችን ተቋም ጥቅሞች ብሎም የግል ጥቅሞች ባለቤቶችን ለማገልገል ከማጠልሸት መከልከል ነው? በርካታ ሰዎች በዐረቡና በኢስላሙ ዓለም ውስጥ ሃይማኖትንና የደዕዋን የማስተማርን የሃይማኖታዊና ባህላዊ ትምህርትን ጉዳዮች ከአስተዳደር ተቋማት ጫናዎችና ከሕይወታዊ ፖለቲካዊ ፕሮግራሞች በተለይ ከህግ አስፈጻሚ ባለስልጣናት የመለየትን አስፈላጊነት አልተረዱም፡ ጉዳዩም በተራ ሕዝቡ ላይና በበርካታ ምሁራን ላይ ተደባልቋል። ይህ መከልከልና ማራቅ መለየት ሃይማኖቱን ከሀገርና ከፖለቲካ መለየት አይደለም፡ ነገር ግን እሱ የስራ አስፈጻሚ ባለስልጣኖችን እጅ ለሃይማኖትና ለእሴቶች ለቅድስና መጥፎ ከመስራት ማራቅና መለየት መከልከል ነው፡ ሃይማኖትን ከማግለልና ከማጠልሸት በጣም ማራቅ ነው፡ ለአምባገነንነትና ማበላሸት መበከል ምክንያትየት እንዳይሆን ነው፡-ሁኔታው ይህ ከሆነ መከልከሉ-ለኡማውና ለሀገር አገልግሎት ይሆናል።

የአስተዳደር ተቋማቶች፡ የህግ አስፈጻሚ አስተዳደር ባለስልጣንም ጭምር "ሀገር" እነሱ ብቻ አይደሉም፡ ይልቁንም በሀገር ውስጥ የአስተዳደር ስርዓት ተቋማቶች አንዷ ነች፡ ኡማውና "የሀገሩ ህዝብ" እነሱ ናቸው አጠቃላይ ፖለቲካውን አቅጣጫ በማስያዝና ሀገርን በመመስረት መሰረትና እጅግ አስፈላጊ አካል፡ ከደጎቻቸው ብቻ የአስተዳደሮችና የህጎች ህጋዊነት የሚወሰደው። ይህም ከሃይማኖት አመለካከቶችና እሴቶቹ አላማዎቹ መንገድ ነው።

በዚህም የኡማው ፖለቲካዊ ውሳኔዎቹ በተከበረው ቁርኣን አላማዎች ላይ በተገነቡ ቅድሚያዎቹና ተሞክሮዎቹ መሰረት እንዲሁም በታሪክ ትምህርቶች ላይ፡ ከሰዎች ባህሪዎች ጋር በመስማማት ላይ የተገነቡ፡ ግንባታውንና ማህበራዊ ፖለቲካዊ ስርዓቶችን በደዕዋ በስልጣኔ በትምህርትና በመረጃ ማስተካከል።ተፈላጊው ቀጥተኛውን ሃይማኖት በፖለቲካና በአስተዳደር መስክ ማደላደል ነው፡ እሱንም ማስወገድ አይደለም፡ ይልቁንም የስልጣንና የአስተዳደር ሰዎችን ማስወገድ ነው እንጂ፡ ሃይማኖትን እሴቶችን እንዳያጠላሹና አምባገነንነትን እንዳይፈጽሙ በዳይ ጥቅሞቻቸውን እንዳይወዱ ለመጋረድ ነው።

## "በኢስላማዊ አስተሳሰብ ውስጥ የመጡትን አባባሎች መከለስ"

ዛሬ በምንኖረው ጊዜ ውስጥ፡ በብዙ መንገዶች ፈጽሞ ባለፉት ክፍለ ዘመናት ውስጥ የሰው ልጅ ሁኔታዎች የተራራቀ የሆነ፡ የአጠቃላይ ኢስላማዊ አስተሳሰብ አባባሎች በተለይም ከሱ ፖለቲካዊው የስር ነቀል ምርምር አስፈላጊነት በእርግጥ ጫን ያለ ሆኗል፡ የምዕራቡ አስተሳሰባዊ ጥቃት ከመጨመሩ ጋር፡ በተለያዩ

ሚዲያዎችና የኢንተርኔት መረቦቹ በሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሃይሉ፡ በሙስሊሞች ላይ በተለይ ወጣቶቻቸው ላይ ያለው አሉታዊ ተጽዕኖ። ተፈላጊው እነዚያ ክለሳዎች በሁለንተናዊ ክለሳ ውስጥ በኡማው ስልጣኔያዊ እይታና ሕይወታዊ መንገዶች በሚያያዙ ጉዳዮች ሁሉ እንዲሆን ነው፡ ከቅርሳዊ ህግጋቶች ከነዚህ ስልቶች ጋር ተያያዥነት ላለው ጉዳይ ሁሉ ነው፡ ያም የነቢያዊን ጊዜ መረዳትና ሚናዉን መላ የሰው ልጅ አመራሩን በመረዳት፡ ወደ ቁርኣናዊ አመለካከቶች መነሻና ግቦች በመመለስ ይሆናል፡ ሀይማኖታዊ ሳይንሳዊ እሴታዊ ማህበራዊና ቅኛዊ በሆነ ግንዛቤ፡ ያም የሚሆነው የኡማው አመለካከት፡ ህግጋቶቹና ስርዓቶቹ ከሰው ልጅ ስልጣኔ አቅሞቹና ተግዳሮቶቹ እድገቶች ተሃድሶ ጋር እንዲጎዳኝ ነው፡ ኢስላማዊ ቋሚ ጉዳዮቹ ቋሚ ካልሆኑት ጋር እንዳይቀላቀሉ መልዕክቶቹና ህግጋቶቹ ስርዓቶቹ ከሁኔታውና ከጊዜው ተጨባጭ ጋር በማይስማሙ ሁኔታዎች ትኩረቶች ቅርጾችና ገለጻዎች ላይ እንዳይቀሩ፡ ምንጊዜም የቁርኣን መመሪያ ዓላማዎችና የተፈጥሮን ባህሪያቶች አላማዎቹንም ከቦታዎችና ጊዜዎች መከታተልና መለያየት ጋር እውን እንዲያደርጉ።

የዘመናዊ ኢስላማዊ ፖለቲካዊ ማህበራዊ አመለካከትን መመርመርና ተቋማቶችን በድጋሜ መገንባት፡ (ከባለስጣን ነጻ) የደዕዋ የሥነ-ትምህርት የማስተማር የባህልና የመረጃ ተቋማትን ጨምሮ፡ ጤነኛ የፖለቲካዊ ማህበራዊ ኢስላማዊ ግንዛቤ መሰረት ለመገንባት አስፈላጊ እርምጃ ነው፡ ትምህርትና ግንዛቤ እነሱ ናቸው በህግጋቶችና ፖለቲካዊ ፕሮግራሞች የነዋሪዎችን አማራጮች እውን ለማድረግ ዋስትና ያላቸው።

እዚህ ጋ ያለምንም ማጭበርበር ወይም ማስገደድ በኡማው ምርጫና እምነት ላይ ተንተርሰው የሚመጡ ፖለቲካዊ ፕሮግራሞችና ቅደምተከተሎች እውነተኛ ፖለቲካዊ ሃይል ያላቸው መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡ እነሱም በዚሁ ተግባራዊነታቸውና ቀጣይነታቸው ዋስትና ያለውና የህዝብድጋፍ ያላቸው ምርጫዎችና ፖለቲካዎች ይሆናሉ፡ ከግል የበላይ ሃይል ጥቅሞችና አስገዳጅነት ከመጡ ፕሮግራሞችና ቅደምተከተሎች በተቃራኒ የህዝቡን ጥቅሞችና እምነት እንዲሁም እንዲሁም ምርጫዎች የማይገልጹ። ይህ ነው በአቅመቢስ ህዝቦችና ንቁ ህዝቦች መካከል ያለው ልዩነት።

ሃይማኖትንና ቅድስናን ከህግ አስፈጻሚ ባለስልጣኖች ቁጥጥር ማራቅ ሰዎችን ድካም የሚመጣባቸው፡ ወደ ማፈንገጥና ጉጉቶች ተለዋዋጭነት የሚያዘነብሉ ከመሆናቸው የመጣ ነው፡ በብዙ ሃገሮች ላይ እንደምናየው፡ ፖለቲካዊው

በሃይማኖታዊው ላይ ከመሾም፡ በፖለቲካዊ ታሪካችንም ውስጥ እንዳየነው ከዚያም በፊት በሮማን ክርስትና ተግባራት ውስጥም፡ እሷን ከቀደሙትም ከቀድሞ አምባገነናዊ ስልጣኔዎችም ከጥንት የግብጽ ነገስታትና የፋርስ ነገስታት ጊዚያቶችና የቀደሟቸውም የተከተሏቸውም።

ሃይማኖት ለድልና ለማሸነፍ ለአምባገነንነት ለማበላሸት መሳሪያ በመሆኑ መካከል ወይም ለፍቅር ለእውነት ለበጎ መጣራት፡ መርሆች አመለካከቶች ስነምግባር ሰበካና ትምህርት ከመሆን ትልቅ ልዩነት አለ።

ኡማውን አዛብቶ ከመረዳትና ከጉዞ ማፈንገጥ ለመጠበቅ ኡማውንና አመለካከቱን ሚና ሚናዎችንና መልዕክቶቹን ከማቀላቀል በመቀጠልም አመለካከቶችን ከመቀላቀል ማራቁ ይገባል።

ቀጣዩን ማለታቸው ከዚሁ ይታያል፡ “አላህ በቁርኣን የማይከለክለውን በባለስልጣን ይከለክላል ” አስተዳደሮች በሰዎች ጫንቃዎች ላይ የሚያደርጉትን ጫና እነሱን ማሸበራቸውም ለመፍቀድ። እምነቶችና መርሆች አመለካከቶች ስነምግባሮች መንገዳቸው ጥሪና ማሳመን ማስተማር ብልሃት መልካም ግሳጼና በመልካም ዘዴ መከራከር፡

ٱدۡعُ إِلَىٰ سَبِيلِ رَبِّكَ بِٱلۡحِكۡمَةِ وَٱلۡمَوۡعِظَةِ ٱلۡحَسَنَةِۖ وَجَٰدِلۡهُم بِٱلَّتِي هِيَ أَحۡسَنُ ﴿١٢٥﴾
(النحل: 125)

“ወደ ጌታህ መንገድ በብልሃትና በመልካም ግሳጼ （በለዝብታ ቃል） ”አል-ነሕል፡125）

وَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ إِلَّا رَحۡمَةٗ لِّلۡعَٰلَمِينَ ﴿١٠٧﴾ (الأنبياء:107).

“ （ሙሐመድ ሆይ！） ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጂ አላክንህም“ （አል-አንቢያእ፡107） ።

ይህ ሁሉ ከአስተዳደር ከሃገር ሚናና በተግባሩ ውስጥ ከሚከሰተው ስልጣንንና ሃይሉን በደሞች በክብሮችና በገንዘቦች ላይ ህገወጥ በሆኑት ሰዎች ላይና በወንጀለኞች ላይ ቅጣት በማውረድ በመጠቀም የተለየ ነው፡ እነዚያን የደዕዋ መምራት ያልገሰጻቸቸውን ፡ ከሙጉዳትና ከወንጀል ያልከለከላቸውን። ስለዚህም፡ አጠቃላይ የቁርኣንና የሐዲስ ጥቅሶችን በተለይ ነብያዊ ሱናን በመረዳት ላይ በእውቀታዊ ዘዴያዊ እይታ ላይ ማተኮር አለብን በቅድሚያ የሱናን አላማዎችና

ግቦች መገንዘብ አለብን፡ ዘዴያዊ የጥንቃቄ መሳሪያዎችን ሁሉ መያዝ፡ ከቅርጽም ከይዘትም በኩል”ሙተዋቲር“/ ተደጋጋሚ ያልሆኑትን ጥቅሶች ሁሉ በሚያጋጥማቸው ጉዳይ -ጥንቃቄው ዬቱን ያህል እንኳ ቢሆን-ማጋለጥ በነሱ ላይ መንቃት ያልቻሉ ስህተቶችና ማቀላቀል መርሳት፡ ዝንጋቴ መቀያረርና ማጭበርበር ይከሰታል የሚል ግምት ከመገኘት። አንድን ንግግር ወይም ሌላን ያመጡ የጊዜ ወይም የቦታ ሁኔታዎችን ወይም አንድን ስራ ወይም ሌላን ያመጣ ከሁኔታዎቹና መልዕክት ከሚተላለፍለት ሰው ሁኔታ ጋር በሚጣጣም መመልከት።

ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ከሌላ ሰው የተለዩባቸውን ሚናዎች መለያየት የግድ ይሆናል፡ በጊዜና በቦታ ውስጥ አድራሽ መልዕክተኛ በመሆኑ፡ በዚያው ጊዜ ውስጥ ለወገናቸው ወደ አላህ ተጣሪ አስተማሪ የስነ ትምህርት ባለሞያ፡ ለነሱና ከነሱ በኋላ ላሉትም አርአያ በመሆኑ፡ እሳቸውም (ሰ.ዐ.ወ) በዚያው ጊዜ ውስጥ የአስተዳደር ባለስልጣን መሪና ማህበረሰብ ሃገር ገንቢ ነበሩ፡ በሰዎች ሕይወት ተጨባጭ ውስጥ የሰውን ልጅ በሕይወቱ ጉዳዮች ውስጥ ተስማሚ ለመሆኑና መርሆቹ እሴቶቹ አመለካከቶቹ እውን ለመሆን መቻሉ ማስረጃ እንዲሆን።

በኢስላም የሚመራን ሃገርና ህዝብ መመስረት እነዚህን እሴቶችና መርሆች አመለካከቶች በጊዜና በቦታ ተጨባጭ ላይ በማውረድ ስልቶች ውስጥ ያለውን የ“ጥበብ”ሚና ገሃድ ያደርጋል ያንን ሁሉ በማስመንጨትም ውስጥ የነብዩን ተግባሮችና ንግግሮች በመረዳት፡ እነዚያን ሃገርን ወደ መገንባትና የሰው ከተሜ ስልጡን ማህበረሰብ ለገንባት ያለሙትን።

የኢስላምን እሴቶችና አመለካከቶች መርሆች ተግባራዊ የማድረግን ጥበብ አስፈላጊነት እንረዳ ተግባራዊነቱ ወደ ገጠሬነት በሚቀርቡ ጎሳዎች ላይ ሆኖ እናገኘዋለን፡ የቀደሙ ሃገሮችና ስርዓቶች ማህበረሰቦች የስልጣኔ ብቃት ባለቤቶች አልነበራቸውም፡ “ሙስሊሙ”ና ነዋሪው ይሆናልና -የዜግነትን መብቶችና ግዴታዎች እስከጠበቀ ድረስ- ለሙስሊሙ ወንድም ነዋሪም ይሆናል፡ ለሙሊሞቹ ያላቸው መብት ለሱም አለው፡ በነሱ ላይ ያለውም ግዴታ በሱም ላይ አለበት፡ “አይበድለውም አይከደውም ” (1) “አላህ ባሪያውን በመርዳት ላይ ነው ባርያው ወንድሙን በመርዳት ላይ እስካለ ድረስ”

ያ ለዚህ የአካሄድ ግልጽነት አመለካከቶችንና መልዕክቶችን ሚናዎችን በመገንዘብ ውስጥ ማፈንገጥና ቅድስናን በመገልገል ያለ አግባቡ መጠቀምን መራቅ አይቻልም፡ መጨፍለቅንና አምባገነንነቱን ማበላሸቱንህጋዊነትን ለማላበስ፡ ያለአስተዳደርና

የስልጣን ሰዎች፡ ረዳቶቻቸውና ወዳጆቻቸው ጥቅም የሚሰፍን፡ ለሃይልና ለገንዘብ ባለቤቶች ለተከታዮቻቸውም ጥቅም በዐረብ ሃገራት ውስጥ እንዳለው ሁኔታ፡ እነዚያ ኡማውንና መላ የሰው ልጆችን ከ “ወሕይ መመራት”ና ከሰው ልጅ ተፈጥሮ መመራት የከለከሉ፡ የተፈጠሩለትን አላማ እውን ለማድረግ ሕይወትን በእውነትና በፍትህ በወንድምነት በእዝነት በሰላም ለመገንባት።

## “ሰውኛ ኢስላማዊ ሀገር”

በእርግጥ እነዚህ ስርዓት ያላቸው እይታዎች የለውጥ ቅደም ተከተሎች፡ በዚህ መሰረት የኢስላማዊው ኡማና ህዝቦች ስርዓት ይሆናል ማለት ነው የኡማውን አመለካከቶችና ኢስላማዊ አላማዎቹን የሚገልጽ ይሆናል፡ ሕያው ኡማ መንግስትና ሰውኛ ኢስላማዊ ስርዓት ያለው፡ ነዋሪዎችን የሚያገለግልና በአጠቃላይ የሕይወት መብቶችና ግዴታዎች ውስጥ በመካከላቸው እኩል የሚያደርግ። እዝህ ጋር “ኢስላማዊ” ማለት ሃይማኖትና ኢስላማዊ ሃይማኖታዊ እሴቶች እነሱ ሁለታቸው የኡማው አመለካከት ፍሬ-ነገርና ስሜቶቹ፡ የውሳኔዎቹና የምርጫዎቹ ክበብ ናቸው ማለት ነው። እዚህ ጋር “ሰውኛ” ማለት ደግሞ ኡማውና ጭፍሮቹ፡ ማህበራዊ ሰብዓዊ የስምምነት ቅደምተከተሎችን መያዝ፡ እነዚያ የዲንን አላማዎችና እሴቶቹን የሚያረጋግጡና የማይጋጩት፡ ነዋሪዎች በምርጫዎቻቸውና በእምነታቸው በህገመንግስት ጥቅሞቻቸውን ለማረጋገጥ በሱ ላይ የሚስማማበት።

ኢስላማዊው ኡማ እነሱ በአብዘሃኞቹ ሙስሊም ነዋሪዎች ማንነትና ባስተዳደጋቸው በእሴቶቻቸው በአመለካከቶቻቸው በአላማዎቻቸው በምርጫዎቻቸው ና በቅድሚያዎቻቸው ኢስላማዊ ናቸው። ሃገራቸውም ኢስላማዊ ዜጋዊ ሃገር ነው፡ በተሻለ እሴታዊ ፍጥረት ዓለማዊ ዓለም አቀፍ ኢስላማዊ ጭብጥ ና አመለካከቶች አላማዎች ላይ የተገነባ ስለሆነ፡ ሕይወታዊ ጥቅሞቻቸውን የሚያገለግል፡ ከሌላ እምነት ተከታዮች ሙስሊም ካልሆኑ በቁጥር አነስተኛ ከሆኑ ወገኖች ሁሉንም ነዋሪዎች ይቀበላል፡ በተፈጥሮ ና በአእምሮ በሃይማኖታት ፍሬ ነገር።

ስለዚህም እነዚህን መርሆችና እሴቶች ግቦች በሰነድና በስምምነት ህገመንግስታዊ ስርዓት መወሰኑ አይቀሬ ነው፡ የሙሉ ማህበረሰቡን ጭፍሮች ሙስሊሞችንም ሆነ ሙስሊም ያልሆኑትን ጥቅሞች ለመጠበቅና፡ ማንነቶቻቸውንም ለመጠበቅ፡ ቅድሚያዎቻቸውንና ምርጫዎቻቸውን ለመጠበቅ፡ ዜጋዊ ኢስላማዊ ሃገር ውስጥ

ነዋሪ እንደመሆናቸው፡ ዜጋዊ ስርዓት፡ ፍሬ ነገሩ ኢስላማዊና ሰውኛ የሆነ፡ እዚህጋ ሰውኛ ማለት እሴቶችንና አጠቃላይ የሰው ልጆች የሚጋሯቸውንና የሚስማሙባቸውን ሰውኛ ስነምግባራዊ መሰረታዊ መብቶችን የሚገልጸው አመለካከት ማለት ነው፡ ለሃይኖቶቻቸውና እምነቶቻቸው እንዲሁም ለስነመግባራዊ ማሕበራዊ ውርሶቻቸው ትኩረት ስንጥል።

በነኚህ መሰረቶች ላይ የተገነባ መንግስት እርሱ “ኢስላማዊ መንግስት ነው” እሱ በዚሁ ሰዓት ውስጥ “ሥነ-ዜጋዊ መንግስት ነው” ወደህዝብ ፍላጎት ይጠጋል፡ በዬትኛውም ዓይነቶቹና እሴቶቹ ምርጫዎቹ፡ ግንባር ቀደሙም በሃገር ውስጥ የሙስሊሙ ዓይነት ፍላጎትና እሴቶቹ ምርጫዎቹ ከማንነቱና እሴቶቹ መርሆቹ ኢስላማዊ አስተዳደጎቹ የመነጬ ቅድሚያዎቹ ናቸው፡ እነዚያ የፍትህና የሕብረትን የትብብርን የበጎ አድራጎትን ተግባር፡ የወንድምነትን የመመካከርንና የሰላምን እሴቶች ከፍ የምታደርግና የምትይዝ።

በዚህ ቦታ ላይ በዴሞክራሲያዊ ዓለማዊ አስተዳደር ስርዓትና በኢስላማዊ የመመካከር የአስተዳደር ስርዓት መካከል መለየታችን እጅግ አስፈላጊ ነው። የዴሞክራሲያዊ ዓለማዊ የአስተዳደር ስርዓት እርሱ ቁሳዊ ዓለማዊ ለሆነው ምዕራባዊ ስርዓት ፖለቲካዊ ገጽታ ነው፡ ያ በኢኮኖሚ መስክ በካፒታሊስት (መንግስት የንብረት ባለቤት የማይሆንበት የኢኮኖሚ ስርዓት) ሥርዓት በማህበራዊ መስክ ደግሞ የፖለቲካ ተቀናቃኝ ባልሆነ ስርዓት/ነጻ አስተሳሰብ ያለው (ሊበራል) በፖለቲካዊ መስክ ደግሞ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ራሱን የሚገልጸው። (የመንግስት ሥልጣን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የህዝብ የሆነበት ሥራዓት) የዓለማዊ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርዓቱን ከምክክራዊ ኢስላማዊ ፖለቲካ ስርዓት የሚለየው መሰረታዊ ገጽታ፡ እሱ ፍልስፍናዊ ገጽታ ነው፡ ያ ለየትኛውም ስርዓት የግድ በሚሆኑ ከፊል ቅደም ተከተል አቅጣጫዎች ላይ ራሱን ማንጸባረቅ የማይቀር የሆነ፡ በመካከላቸው በከፊል አቅጣጫዎችና ደንቦች መመሳሰል ያለ ከመሆኑ ጋር።

ከዚህ መመሳሰል አይነቶች ለምሳሌ፡ የምርጫ ስርዓት ነው፡ ማለትም የአብላጫ ሕዝብ ምርጫ መነሻነትና የ-ህግ አውጪ ባለስልጣን የህግ አስፈጻሚ ባለስልጣን የህግ ተርጓሚ ባለስልጣን -ስልጣኖችን መለያየት፡ በስልጣን ሃይሎቻቸው ውስጥ ሚዛናዊነትን ለማረጋገጥ።

የምዕራቡ ዓለማዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት-ሃይማኖታዊና ክህነታዊ አፈ ታሪኮች በመስፈናቸውና በምዕራቡ ማህበረሰቦች ውስጥ በቀዳሚ ተግባራቶቹ ሰበብ- ወደ ቁሳዊ አመለካከት የሚደግፍ ፖለቲካዊ ስርዓት ነው፡ የሰውን ፍላጎት እውነታና ትክክል የተሻለ የሆነውን ነገር ለመወሰን የመጀመሪያውና የመጨረሻው ያደርጋል፡ ማለትም መብትና እውነታበመጨረሻ ግለኛ ሰውኛ ጉዳይ ነው፡እያንዳንዱ ግለሰብ ለራሱ እውነታና ትክክል ያለውን ይወስናል፡ ማንምአካል በማንም ሌላ ሰው ላይ እሱ ከሚያምንበት ውጭ መወሰንም ሆነ መጫን አይችልም።

ለሰው ልጅ አንድ ግለሰብ በራሱ ብቸኛ ሆኖ መኖር ስለማይቻልና እሱ ከሌሎች ጋር መረዳዳት የማይቀር ነገር ነውና፡ በማህበረሰቡ ግለሰቦች መካከል ስምምነት መፈጸም የማይቀር ነገር ሆነ፡ ጉዳዮቻቸውን እንደግል እምነቶቻቸው ለማግራት የሚታዘዙት አጠቃላይ ስርዓት መውደድም የማይቀር ሆነ፡ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ተገኘ-በአብላጮች ውሳኔ መመራት-ያ ብዙሃንም ሆነ በቁጥር አነስተኛ የሚታዘዙት ዳኛ የሆነ። አብላጮቹ ሃይልን የምትወክል ብትሆንም መሰረታዊ የሆኑ የአነስተኛ ቁጥሮችን መብቶች መጠበቅ አለባት፡ ዬትኛውም እስከመጎዳት ድረስ በአነስተኛ ቁጥሮች መብቶችና መሰረታዊ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸም በደል ወደ ተቃውሞና አመጽ ማህበረሰቡ ወደ አለመረጋጋት የሚያደርስ መሆኑን መገንዘብ አለባት፡ ይህ ደግሞ ለአጠቃላይ የማህበረሰቡ አይነቶች አብላጫም ሆኑ አነስተኛ ቁጥር ታላቅ ኪሳራ ያስከትላል።

ከዚህ ቁሳዊ (ዓለማዊ) ከሆነ ስርዓ ተግባራቶች በሚቆምበት ፍልስፍና መስራት መሰረታዊ የሆኑ አይ አዎ (እርስ በርስ የሚጋጩ ነገሮች) ተፈጥረዋል፡ ምክንያቱም የነጻነት ግንዛቤ-በመጨረሻ-የማህበራዊና የሥነምግባራዊ ስርዓት አልበኝነት ማለት ሆኗል፡ እሴቶችና መርሆች ፈረሱ፡ ስነምግባራዊ ልጓሞችም ጠፉ ግላዊነትና እንስሳዊነት መሰረት ስለሆኑ፡ ግላዊ ፈጣን ፍላጎቶች ስሜቶችና ዝንባሌዎች ሰፈኑ፡ እነዚያ መጥፎ አመለካከቶቻቸው ከነኚህ ማሕበረሰቦች በብዙዎቹ ይፋ መሆን የያዙና፡ እነዚህ ማሕበረሰቦች ከነዚያ ቤተሰብን ከሚዳኙ ሰዋዊ ማሕበራዊ ግንኙነቶች ዋጋ መክፈል ጀምረዋል፡ ቤተሰብ ትውልድን ለማሳደግ ታማኝ ጥቡቅ ማሳደጊያ አልሆነም፡ መንፈሳዊ ልቦናዊ ስሜታዊና ቁሳዊ ጉዳዮቻቸውን የምታሟላም አልሆነችም፡ ነገሩ ካለፈው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ጀምሮ ያን እነዚህን ማህበረሰቦች ወደ ስርዓት የለሽነት ስነምግባራዊ መፈራረስ ጠርዝ የገፋፋውን ነገር ሆነ፡ ልክ ከበፊት ዘራቸው ከምድረ ገጽ የጠፋ ህዝቦችና

አገሮች ስልጣኔዎች ታሪክ ባለፈበት ላይ፡ እንደ ዓድና ሰሙድ ወገኖች እንዲሁም እንደሉጥና የፊርአን ህዝቦች።

ኢስላማዊው የመመካከር ስርዓት በቁርአናዊ አመለካከቶችና እውነተኛ የቁርኣን ዓላማዎች መሰረቶች ላይ የተገነባ ከሆነ ሙስሊሞች የማህበረሰቡን ምርጫና የብዙሃኑን ውሳኔዎች መያዝ አለባቸው፡ ልክ እንደ ዴሞክራሲያዊ ዓለማዊ ስርዓት ሁሉ። ነገር ግን የምክክራዊ ኢስላማዊ ስርዓት ከዴሞክራሲያዊ ዓለማዊው ስርዓት ይለያል፡ ሙስሊም መብትንና እውነታን እውነታ ላይ የተመሰረተ ስሜት አዘል ያልሆነ ጉዳይ አድርጎ ይቆጥራቸዋል፡ አጠቃላይ ፍጥረተ ዓለማዊ እውነታ እሱ ከሰው አስተሳሰብ አቅም በላይ ነው፡ ሙሉ ፍጥረተ ዓለማዊ እይታምየሰውን ልጅ መንፈሳዊውንም ሆነ ስነምግባራዊ ማሕበራዊ ስልጣኔያዊና ግንባታዊ ጉዞ ለመምራት የግድ የሆነ ጉዳይ ነው፡ የሰው ልጅ ጉዞ በሕይወት የተሻለ እንዲሆን፡ የሰው ልጅ ለእድለኛነቱና ስነልቦናዊ መረጋጋቱ ይህን እይታ መጨበጥ አይቀሬ ነገር ነው።

ሙስሊም ነዋሪዎች እስልምናቸውን እውን እንዲያደርጉና ማህበረሰባቸውን በኢስላማዊ እይታና እሴቶች መሰረት ላይ ማህበረሰባቸውን እንዲያቆሙ፡ ኢስላማዊ ፍጥረተ ዓለማዊ እይታንና መርሆችን እሴቶችን አመለካከቶችንና የተሻሉ መንፈሳዊ ሥነ ምግባራዊ ግንባታዊ አላማዎችን በውሳኔዎቻቸውና በምርጫዎቻቸው ውስጥ መቀበልና ጽኑ እምነት ማመን መያዝ አለባቸው።

ይህ ሁለንተናዊ ራዕይና ኢስላማዊ እሴቶች አመለካከቶች እንዲሁም ፍልስፍናው በሙስሊሙ ስሜት ውስጥ ግልጽ ሊሆኑ ይገባል፡ ነገር ግን እሱ ቀላል የተወሰኑ ፍጹም ግልጽ የተረጋገጡ የታወቁ የተሻሉ ሰውኛ ራዕይና መርሆች እሴቶች እንዲሁም አመለካከቶች ጉዳይ ነው።

ማንገላጀትና እርባናቢስ ነገሮች ከሱ ጋር ተያያዥነት የላቸውም፡ እነዚህ እይታዎች እነሱ በ “ወሕይ” የወረዱ እይታና መርሆች እሴቶች እንዲሁም አመለካከቶች ናቸው፡ በነብይነት ጊዜ ውስጥ በሰዎች ተጨባጭ ላይ ተግባራዊ ሆነዋል፡ ስለዚም እነሱ ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ጋር ይጣጣማሉ፡ ያደላድሉታሉም አእምሮንም በጽኑ ያሳምናሉ፡ ልቦናና መንፈስም ይደሰቱባቸዋል፡ የስሜትን ጥም ይቆርጣሉ፡ ስርዓቱን በተሻለ ሰውኛ መንፈሳዊ ሥነ ምግባራዊ ግንባታዊ መሰረት ላይ የሚመሰረቱ ክልልና የማይለወጡ ሁኔታዎችን ያረጋግጣሉ። በነሱ ያመነ ሰው የሚያምነው በማስረጃ ላይ ብቻ ተንተርሶ ነው፡ ከተቀበላቸውና ጽኑ እምነት ካመነባቸው፡ ልቦናውና ስሜቱም ከወደዷቸው ምርጫው እሱ ኢስላም የመሆን ምርጫ ነው

ማለት ነው፡ መሰሮቶቻቸውንና አላማዎቻቸውን የማይቀይሩ ሁኔታዎቻቸውን እንቢ የሚል ላለማወቅ አሊያም ለተወራሸ ነገር፡ ለሱ እንደ አንድ ፍጡር ሰው በዚያ ነገር ሙሉ ነጻነት አለው፡ በዚያ ነገርም የተነሳ ሙስሊም አይሆንም። ሙስሊም እንዲሆን መሰረቶችንና ቋሚ ነገሮችን የመቀየርና የመለወጥ መብት እንደሌለው መገንዘብ አለበት።

የዚህ ትርጉም ማንኛውም ግለሰብ ሙስሊም መሆን ወይም አለመሆን ይችላል ማለት ነው፡

لَآ إِكۡرَاهَ فِي ٱلدِّينِ ۖ (البقرة : 256).

"በሃይማኖት ማስገደድ የለም "{አል-በቀረህ፡256} ነገር ግን ለማንም ሰው በመሰረቶች በቋሚ ጉዳዮችና በዓላማዎች መቀየርና እሴቶችን አመለካከቶችን ዓላማዎችን ማጣጣል አይችልም፡ ለራሱ ምክንያታዊ ሳይሆን የሌለውን ባህሪ ሊያላብስና ለህዝቡ እውነት ከሱ ጋር ዝምድና የሌለውን ማንነት ሊያውጅ ዘንድ።

በኢስላሙ ኡማ ውስጥ ፖለቲካዊው የአስተዳደር ስርዓት ዞሮዞሮ እይታ ልዩ ክብር አለው ውሳኔዎቹና ፖለቲካዊ ስርዓቶቹም በኡማው ጽኑ እምነቶችና መቀበሉ ውስጥ ይያዛል፡ ማለትም ኢስላማዊ ስርዓት "እነደ ምዕራባዊው የጥንታዊ ግሪክ አገላለጽ " እሱ "ዴሞክራሲያዊ" ስርዓት ነው በውሳኔዎቹ የብዙሃን ነዋሪዎችን አብላጫ አስተያየት ያከብራል፡ ነገር ግን እሱ "ዴሞክራሲያዊ" ኢስላማዊ ምክክራዊ ነው፡ "ዴሞክራሲያዊ" ቁሳዊ ዓለማዊ አይደለም።

በፖለቲካዊ ኢስላማዊ ምክክራዊ ስርዓት ዝግጅቶች ውስጥ የሙስሊሞች ተግባር እሱ በተለያዩ የሂይወት ጉዳዮችና ባማራጮቻቸው መመካከር ነው፡ በዚህ እይታና በነዚህ እሴቶች አመለካከቶች ጊዜና ቦታ መሰረት፡ ለሁኔታው እንሚስማማና በመቀጠልም ማንነታቸውን እንዲያረጋግጥ፡ ጥቅሞቻቸውን እንዲጠብቅ በማህበረሰቡ ግለሰቦች በአይነቶቹ መካከል በስምምነታዊ መልኩ።

ይህን ስምምነት ለማረጋገጥ ስርዓቱ የአብዛኞች ጽኑ እምነት በኢስላማዊ መሰረታዊ እይታ አመለካከትና አላማዎች ክበቦች ውስጥ፡ እነዚያ ከማህበረሰቡ ልጆች አባልነት በሰውነትና በነዋሪነት ወንድምአማችነት የሚመነጭ። ስርዓቱ የወንድምአማችነት የፍትህ የትብብር የህብረትና የእዝነት መርሆችን ይይዛል፡ ስለዚህም ይህ ስርዓት የሰውን ልጅ ክብር ለነዋሪዎቹ መሰረታዊ መብቶችን፡ ከነሱ ለያንዳንዱ በያይነቶቻቸው ለተከበረ ኑሮ ዋስትና መሆንን የጠብቃል ለምንም

ነገርትኩረት ሳይደረግ ለዘር ወም ለሃይማኖት ወይም ለአቅም ወይም ለደረጃ፡ ስርዓቱ በነዚህ እሴቶች ላይ መውጣት ወይም ችላማለት አይችልም።
በምክክር ስርዓት ጥላ ስር፡ ለማንኛውም እምነቱን ለያዘ ሙስሊም ሲታወቀው ሙስሊ ጥሩ በሆነ ህሊና በማንኛውም ሌላ ሰው መብት ላይ ድንበር ማለፍን ወይም በደልና ግፍ መፈጸምን ሊቀበል አይችልም፡ ሙስሊምም ቢሆን ወይም ከሙስሊም ሌላ ቢሆን፡ የግል ጥቅሙን ፈልጎ ወይምለማንም ሌላሰው፡ የቅርብ ቅርብ ዘመመዱ እንኳን ቢሆን፡ ምክንያቱም ለአንድ ሰው በጐ መዋል የሻ ሰው ከግል ትግሉና ገንዘቡ ሊውልለት ይችላል፡ ከዚህ ውጭ ያለ ነገር እሱ በደል ነው ድንበር ማለፍ ነው፡ ከሃይማኖትም ከፍትህም በምኑም የለበትም።
በምክክራዊ ዜጋዊ የኢስላም ፖለቲካዊ ስርዓት ጥላ ስር የፖለቲካ ፓርቲዎችና ዓይነቶች በሚያረጋግጡ ሕይወታዊ ፖለቲካዊ መርሃ ግብሮችን በማቅረብ መወዳደር ላይ ያጠረ ነው፡ በኡማው እይታና ቅደም ተከተሎቹ መሰረት።
በዚህ ስርዓት ውስጥ በብዙነት ወይም በስልጣን ቅብብል፡ ችግር የለም፡ በሰዎች ግንዛቤና ከህኖታዊ ርዕዮተ ዓለም ጫናን ባለመቀበላቸው ሰበብ ያ በቅዱስ ስምና ሁሉን አጠቃሎ መያዙን የሚሚግተውን ፍጹም እውነታ የሚያወራ - በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በግንዛቤ ወይም ወይም ግንዛቤ ሳይኖር- በሱ መሰረት በነሱ ላይ የባለአደራነትን መብት የሚተገብር፡ ውሳኔዎቻቸውን ጥቅልል አድርጎ የሚይዝ አምባገነንነትንና መበላሸትን የሚያደላደል።
እነህ ሁሉ ጥንቃቄዎች -የግድ- አምባገነናዊ ስልጣናት በማንኛውምስም ወይም በማንኛውም የሃሰት ቃል ከመቋቋም ይከለክላሉ ኡማውን ብቻውን ሲሆን የውሳኔ ባለቤት የስልጣን ምንጭ ያደርጉታል፡ በዚህም ምክንያት በዚህ ኢስላማዊ ምክክራዊ ዜጋዊ ስርዓት ውስጥ ይገኛሉ፡ ዜጋዊ የሚንከባከቡት መንግስታት በነሱላይ ፖለቲካዊ ፓርቲዎች ይተካካሉ የእነሱን ፕሮግራም የመቀበሉና ያለመቀበሉ ወደ ህዝብ ይመለሳል፡ በዚህ ስርዓት ውስጥ በማንኛውም ሁኔታ የኡማውን አመኔታ ያላገኘ ማንኛውም መንግስት ወይም ፓርቲ ስልጣንም የለው ህጋዊነትም የለው።
እስካውን ካሳለፍነው ሁለቱ ስርዓቶች፡ “ዴሞክራሲያዊ” ቁሳዊ ዓለማዊና “ዴሞክራሲያዊ” ኢስላማዊ ምክክራዊ በከፊል ዓይነቶቻቸው ቢመሳሰሉ እንኳን - በተለይ ስልጣኖችን በመለየትና የብዙሃንን ውሳኔ በመያዝ - በመካከላቸው ጥልቅ መሰረታዊና ፍልስፍናዊ ልዩነቶች አሉ፡ በሁለቱም ማህበረሰቦችና በሁለቱ ስልጣኔዎች መካከል ጥልቅ የፍልስፍና ልዩነቶች ስላሉ ነው፡ “እውነታ ለሃይል

ነው” እና “ሃይል ለእውነታ ነው” የሚሉት ሁለት አመለካከቶች በመቃረናቸው የሚቃረኑ። እነኝህ ፍልስፍናዊ መሰረታዊ ልዩነቶች ውሳኔ በመወሰን ስልቶችና በህልውናዎቹ ተቋሞቹና ስርዓቶቹ ራሷን ማንጸባረቋ የማይቀር ጉዳይ ነው።
ኡማው ከሚሰቃይበት ችግር “የቁሳዊውን  ዴሞክራሲ ” በጭፍን በማመሳሰል በምርጫዎችና ውሳኔዎች ገጽታዎች -የቀልድ አሳፋሪ ሃሰተኛ የምርጫ አማካይ ውጤቶች እነዚያ መቶ በመቶ ሊደርሱ የሚቀርቡ - የነዚህን ቅደም ተከተሎችና የሚያመላክቱትን የዓላማዎቹን ሳይገነዘቡ ከሱ ተስማሚን ጠቃሚን መያዝ ሳይችሉ፡ ከሱ ኢስላማዊ እይታ አስተሳሰብ ስልጣኔ ስርዓት እንዲጠቀም፡ ፍልስፍናዊ ሕይወታዊ ባሕሪውና ግቦቹ ጋር በሚስማማ።
ከሁለቱ ስርዓቶች ልዩነት ውጤት በእርግጥ ቀጣዩ ይገኛል፡ ኢስላማዊ ምክክራዊ ”ዴሞክራሲያዊ“ ና ቁሳዊ ዓለማዊ በኢስላማዊው ስርዓት ውስጥ ምክክርን መያዝ ብዙ ጊዜ በዘመናዊ ፖለቲካዊ ስርዓቶች ቅደምተከተሎች ውስጥ ”ፓርላማዊ ፓርቲዎች“ ብሎ መጥራቱ የሚቻል ነገር ይፋ ወደመሆኑ ያደርሳል፡ በኢስላማዊ ስርዓት ውስጥ ተመካካሪዎቹ ከመያዝ የመነጨ ነው በህሊና ማመን እውነታና ፍትህ ጥቅም ለሆነው ነገር በፓርቲ ቋሚ ቀድመው የተወሰኑ አቋሞች አይደሉም።
የዚህ አይነት ሁኔታ በአባባሎችና ብዙሃኖች አቋሞች ተጽኖ ሊፈጥር ይችላል፡ በማስተዋልና መመካከር ሳቢያ የእምነቶች ሁኔታዎች ሲቀየሩ። -በከፊል ሁኔታዎች- በህግ አስፈጻሚ መረጋጋበፖለቲካዎቹ መቀጠልም ላይ ተጽዕኖ ሊፈጥር ይችላል የፓርላማ መሰረቶች መዋቅሮች ለመለወጣቸው። ይህ ሁኔታ “ፕሬዚዳንታዊ ስርዓቶችን” -በሆነ መንገድ- ለምክክራዊ ኢስላማዊ ስርዓት የበለጠ ተስማሚ ሊያደርግ ይችላል- እሱ በፖለቲል ሳይንሶች ተማሪዎች ዘንድ “ፓርላማዊ ስርዓት” በመባል የሚታወቀው አይደለም የህገመንግስታዊ ቁጥጥር በመሪው ስልጣኖች ላይ በተሟላ ሁኔታ መከናወን አለበት፡ ግዴታዊ በሆነው እንጂ በነሱ ውስጥ ያለመስፋፋት፡ የህግ አስፈጻሚ ባለስልጣን ሚናውን ከመወጣት ለማስቻል ሲባል።
ኡማው የመነሻዎቹን እውነታ የፍጥረተ ዓለማዊ እይታውን የስርዓቱንና የስልጣኔያዊ ፍልስፍናውን ባህሪ መገንዘብ አለበት፡ ተቋማቱንና የህገመንግስታዊ ስርዓቶቹን በዚያ ትክክለኛ ስኬታማ፡ ከባህሪውና አላማዎቹ ጋር የሚስማማ ስልት እንዲገነባ፡ ተብላልቶ ከመለወጡና ስልጣኔያዊ አብሪ ውይይቶቹ እኔት እንደሚጠቀም እንዲያውቅ፡ የህዝቦች ልዶችና የሌሎች ዘመናዊ ስርዓቶች ካረጋገጡትና ከገለጹትም ከ“ሳይንሳዊ እውነታዎች”ና ከስኬታማ ማህበራዊ

ህይወታዊ “ስርዓቶች” ጉዳይ፡ በብዙ ጉዳዮች “ችኮላን መፍጠር” መድገም አያስፈልገንም እንደሚባለው።
በዚህ አይነት አወንታዊ ስልጣኔያዊ ልውውጥ ለህዝቡ በተቻለ ቀላል ሃይል የማህበራዊና ስልጣኔያዊ ስርአቱን ማንቀሳቀስ ይችላል፡ የሰው ልጅ በስልጣኔያዊ ሂደቱ ካረጋገጠው ማንኛውም የተሻለና ገንቢ ትግል ተጠቅሞ፡ በሌሎች ስልጣኔያዊ ሰዋዊ ስርዓቶችን በመምራት ኢስላማዊ ስልጣኔያዊ ስርዓቶቹና በተሻሉ ፈጠራዎቹ ውስጥ በሚናው እንዲሳተፉ።
ኢስላማዊው ዜጋዊ ምክክራዊ ስርዓት የመንግስታቶችና የህግ አስፈጻሚ ባለስልጣቹ የሃይማኖትን ቅድስና አይዘረጉበትም፡ የግንዛቤ መፍጠርና የደዕዋ የትምህርት የማስተማር የባህልና የአጠቃላይ ብዙሃን መገናኛዎች ጉዳዮች በሱ ውስጥ ነጻ ተቋማቶች ይሆናሉ፡ የነሱ ጉዳይ ቀጥታ ወደህዝቡና በዚህ ጉዳይ ወደ ልዩ ተወካዮቻቸው እጅ ይመለሳል።
በዚህም -በኢስላማዊ ዜጋዊ ስርዓት ውስጥ- ለነዚህ ፓርቲዎችና ፖለቲካዊ ቡድኖች ሃይማኖታዊ ባለአደራነት፡ ወይም የቅድስና መለዮ ሊኖራቸው ዘንድ ቦታ የለም፡ ፊትለፊታቸው ህዝቡን ለማገልገል የጠራ ፖለቲካዊ ውድድር እንጂ የለም፡ በፖለቲካዊ ህይወታዊ መርሃ ግብሮች፡ በውስብስ የህትወት ግምቶች ላይ የምትገነባ፡ ከተወሰኑ ኢስላማዊ ህገመንግስታዊ ፍልስፍናና እሴቶች አመለካከቶች ዓላማዎች የሚነሳ ቢሆን እንኳን፡ ስለዚህም አመለካከቶችና ቅደም ተከተሎች አስተሳሰቦች ይበዛሉ፡ ሁላቸውም የህዝቡን ህገመንግስት የሚይዙ ህጋዊነታቸውን ህዝቦች እነዚህን ፕሮግራሞች ከመቀበላቸውና ከመውደዳቸው እንዲሁም ከነዚህ መንግስታቶች ተግባር የሚያመነጩ ቢሆን እንኳን።
በዚህ ዜጋዊ ኢስላማዊ ሰውኛ ሃገር ስርዓት ውስጥ ውጤቱ የእምነትን ነጻነትና የመነሻዎችን ጤንነት መጠበቅ፡ ፍትህን ማስፈን፡ የገቢ ምንጮችን መጠበቅ፡ የደዕዋና የግንዛቤ መስጠት የስነ ትምህርት የማስተማር የባህልና የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ተግባር ደህና መሆን፡ በአስተዳደሩና በባለስልጣኑ ላይ ለህዝቡ ሞግዚትነት ሊኖረው መሪውና ባለስልጣን የህዝቡን በአጠቃላይ ዐይነቶች ጥቅሞች ታማኝ አስፈጻሚ ታማኝ ዘበኛ እንዲሆኑ።
በዚህ ዐይነት ስርዓት በኢስላማዊ አህጉሮች ውስጥ መንግስታቶችና ተቋማት የህዝብን ፍላጎትና ምርጫዎችን ገላጭ ይሆናሉ ከሱና ከፍላጎቱም ተወካይ ይሆናሉ የግል ጥቅሞችን የሚያባርሩ ድቃላና አታላይ አምባገነን ብልሹ መንግስታቶች አይሆኑም ከህኖታዊ አምባገነን ብልሹ የአምላክን ፍላጎት ከፍቃድና ማዕረግ

ባለቤቶች በሰራተኞቹ ካህናት አፎች መግለጽን የሚሞግቱም መንግስታቶች አይሆኑም። ባለስልጣኑ ፍላጎቱንና ሞግዚትነቱን በዘበኞች ሃይል አማካይነት በህዝቡ ላይ ይጭናል የምርጥ ባለሃብቶችንና ፖለቲከኞችን ጭፍሮች ጥቅሞች ለማገልገል ሲል።

## (የለውጥ ጐዳና)

ማንኛውም ባለስልጣን ወይም ጭፍራ ድንበር ሲያልፍ ወይም ሲያፈነግጥ በሙስሊሙ ማህበረሰብና በሙስሊሙ ሃገር ወስጥ በፖለቲካ ትግል ሃይል ህጋዊነት የለውም፡ እሱም በቀጣዩ ነብያዊ አባባል ውስጥ የሚገለጸው ነው፡ “ሰሐባዎቹ አሉ፡ አንተ የኣላህ መልክተኛ ሆይ አንዋጋቸውምን ? ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) አሉ፡ አንዋጋቸውም እስከሰገዱ ድረስ“።

ከዚህ ሃዲስ በደልንና ማፈንገጥ ብልሹነት አምባገነንነትና የህዝቡን መብት መጨፍለቅን መቀበልን አንረዳም -የችግር ጊዜ ምክክርና ነቀፋ ትችት የወደቀ ጊዜ -ኡማው ለድንበር ማለፍና ማፈንገጡ ለበደሉ ለብልሽቱ አምባገነንነቱ መቋጫ ማድረጉን ሃላፊነት መውሰድ አለበት፡ ከድንበር አላፊዎች ጭፍሮች ወይም ባለስልጣኖች እግሮች ስር ምንጣፉን መሳብ አለባቸው ወደ ማህበራዊ ህዝባዊ ሰላማዊ ተቃውሞ በመደገፍ።

ከታወቁ የተቃውሞ ስልቶች- የማህበረሰቡን ደህንነት ያለማጓደል - መናገርና ሰላማዊ ሰልፍ መውጣት መቃወምና ሰላማዊ አመጽ ነው፡ ያም መብቶችን ለማስከበር፡ ድንበር አላፊነቶችን ለመከልከል ማስተካከሎችንና ተፈላጊ ለውጦችን ለማረጋገጥ፡ ወይም ስልጣንንና ህጋዊነትን ለመመለስ፡ “በላጩትግል (ጂሃድ) ፍትህ የለሽ ባለስልጣን ዘንድየሐቅን ቃል መናገር ነው” እንዲሁም “ፍጡር ፈጣሪን በመወንጀል ሊታዘዙት መብት የለውም” “ሙስሊም የሆነ ሰው በወደደውም በጠላውም ጉዳይ መስማትና መታዘዝ አለበት፡ በወንጀል መታዘዙ ሲቀር፡ በወንጀል የታዘዘ ጊዜስ መስማትም መታዘዝም የለበትም” “በበጐ ነገር እንጂ መታዘዝ የለም”። የሙስሊሙ ማህበረሰብ ወደ ቡድኖችና አህጉሮች በልዑል በገዢ ወደሚተዳደሩ የተለያየ ጊዜ፡ ትግሉም ቡድንተኛ ወይም የታጠቀ ወገንተኝነት ትግል የሆነ ጊዜ፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የኡማው ጀመዓ ለማስማማትና ለእርቅ ተንቀሳቃሽ አካል መሆን አለባቸው አእምሮንና ፍትህን ወንድምነትን ማስዳኘት እንዲሁም ለታሰቡት ወገኖች ለህዝቡ የበላይ ጥቅሞችን መጠበቅ።

አንድ ወገን ወይም አንድ ቡድን በግፍና በወሰን ማለፍ ላይ ችክ ካለ፡ በተገፋው አካል ጐን መቆምና ገፊውን -ጉዳዩ ካስፈለገ ሃይልና መሳሪያን በመጠቀም እንኳን ቢሆን- ወደ ሃቅና ፍትህ እንዲመለስ ማስገደድ፡ ኣላህ እንዲህ ይላል፡

وَإِن طَآئِفَتَانِ مِنَ ٱلْمُؤْمِنِينَ ٱقْتَتَلُوا۟ فَأَصْلِحُوا۟ بَيْنَهُمَا ۖ فَإِنۢ بَغَتْ إِحْدَىٰهُمَا عَلَى ٱلْأُخْرَىٰ فَقَٰتِلُوا۟ ٱلَّتِى تَبْغِى حَتَّىٰ

تَفِىٓءَ إِلَىٰٓ أَمْرِ ٱللَّهِ ۚ فَإِن فَآءَتْ فَأَصْلِحُوا۟ بَيْنَهُمَا بِٱلْعَدْلِ وَأَقْسِطُوٓا۟ ۖ إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلْمُقْسِطِينَ ﴿٩﴾

(الحجرات : 9 ).

"ከምእመናንም የሆኑ ሁለት ጭፍሮች ቢጋደሉ በመካከላቸው አስታርቁ ከሁለቱ አንደኛይቱም በሌላይቱ ላይ ወሰን ብታልፍ ያችን ወሰን የምታልፈውን ወደ ኣላህ ትእዛዝ እስከምትመለስ ድረስ ተጋደሉ ብትመለስም በመካከላቸው በትክክል አስታርቁ በነገሩ ሁሉም አስተካክሉም ኣላህ አስተካካዮችን ይወዳልና።"{አል-ሑጅራት፡9} ይህ የታሰበበት ከህዝቡ ግዴታ ይቆጠራል ምንግዜም ሰልፎቻቸውን አንድ በማድረግና በመተባበር ላይ ሁሉንም ህዝቦች አንድ በማድረግ ላይ መስራት አሕዛቦችና ቡድኖችና ቡድኖችም ሆነው ባለመፈረካከስ ላይ። አንድነትና ጥምረት መሞላላትና መተባበር ከተቃራኒዎቻቸው የተሻሉ ናቸው፡ በዚህም ሃይላቸውና አሸናፊነታቸው ደህንነታቸው ድሎታቸው ይገኛል።

ይህ ተመራማሪዎችና "የለውጥ" መሪዎች ቃሎችን ለሞምላትና ለፍጻሜ ደህንነት ወደ "ተቋማት" አስፈላጊነት ካልነቁ በስተቀር አይረጋገጥም፡ አለበለዚያማ የለውጥ አቀንቃኝ መሪዎች ራሳቸው ወይም ተተኪያቸው በራሱ በወጥመዱ ውስጥ እስኪመገቡ አይቆዩም እነሱም ሆኑ ተተኪዎቻቸው እንደሰው አምባገነንነትንና ባለአደራነት ብልሹነትን ወደ መፈጸም ከመድረስም፡ የአሁኑ ህዝቦችና ከህዝቦች የቀደሟቸውም ወደዚህ ነገር እንደ ደረሱ።

ኡማው በሃሳባዊ ዝግ ትርጉም አልባ ለውጥ ቀለበቶች ውስጥ እንዳይሽከረከር ከሱጋር በማያልቅ የወረደ ክብ መሽከርከሪያ ውስጥ እንዳይኖር፡ ከአሸናፊነትና ክብር ልማትና ግንባታ ህልሞች ሲሪብዶ፡ እንዲሁም አምባገነንነትና ብልሽነትን ድህነትን ግፍን የመደምሰስ ሲሪብዶ፡ የለውጥ ተቀናቃኞችና ተመራማሪዎች የስነትምህርት ባለሙያዎች -በእውነት ለውጥን ማምጣትና የህዝቡን እድገት የሚፈልጉ ከሆነ- በልቦናቸውና በማህበረሰቦቻቸው ውስጥ ወደ ንግግሮች ሳይሆን ወደ ተግባራት ማየትን አፈጻጸሙን በሙግቶች ሳይሆን በውጤቶች መለካትን

መትከል አለባቸው፡ ወደዚያ ወደ አመርቂ ተቋማት ወደ ማይደገፈው ጣፋጭ ንግግር ብቻ መዝመት የለባቸውም።
-በታሪክ ውስጥ- በአምባገነን ስርዓት ውስጥ ሃይማኖታዊም ሆኑ ሃይማኖት የሌላቸው ወደ ምርጥ ፖለቲከኞችና ስልጥኖች የሚዲያ ሰዎች ብንመለከት የሚያጋራቸው ባህሪ እናገኛለን ባዶ ጣፋጭ ንግግር በማስገኘት የውሸት ተደጋጋሚ ቃሎችን በመግባት ድካ ማለፍ የተለያዩ ህዝቦች ምርጦችና ገገር ክፍሎች ሁላቸውም የጥሩ ንግግር ፕሮፓጋንዳዎችንና የለውጥ ሃሳባዊ የውሸት ቃልኪዳኖችን በመልቀቅ ይስማማሉ ህዝቡን በማገልገል የፍትህና የድሎት ማህበረሰቦችን በማቋቋምና ብልሽነትን በማጥፋት ቃል በመግባትም በተጨማሪም በዘላለማዊ ስለትግሎቻቸው በማውራትም እንደሚመሳሰሉ ሁሉ፡ አምስትዮሽና የአስር ዓመታት የሺህ ዓመታት ሃሳባዊ የልማት እቅዶችን በማውጣት የትምህርትና የጤና አስተዳደሮችን በማሻሻል ሃብትን በማስገኘት አጠቃላይ የድህነትንና የበሽታን መንስኤዎች በመጨረስ፡ ፋብሪካንና ንግድን በማነቃቃት ላይ በልብ ላይ የሚታወስንና የማይታወስንም ነገር ሁሉ ልቦናዎች ከሚወዱት ነገር ሁሉ። አንድ ቡድን ይጓዛል ሌላ ቡድን ይመጣል።
አንድ መንግስት ይወድቃል ሌላ ደግሞ ይሾማል፡ አንድ ሃገር ይወገዳል ሌላ ይመጣል፡ ወደ ህገ መንግታዊና የተሟላ አመርቂ አገልግሎታዊ ተቋማት የማይደግፍ ወሬና ቃልኪዳን ማደንዘዝ በየቀኑ ይደጋገማል ለምንም ነገር ከዚያ ከወሬና ቃልኪዳን ተጽኖ ሳይኖር፡ ይልቁንም የነዚያ ህዝቦች ሁኔታ በተጨባጭ ከክፉ ወደ ባሰ ክፉ ይሄዳል፡ ተቋማትና መልካም አስተዳደር የህዝብ ቁጥጥር በመጥፋት ምክኒያት።በሽታዎቹን ለማከም የመጀመሪያው ነጥብ እሱ ህግ በማውጣትና በማስፈጸም በመተሳሰብና በቁጥጥር የተቋማትን አስፈላጊነት መገንዘባችን ነው፡ እንዲሁም በስነትምህርትና በትምህርት በሃብትና በገቢ ምንጮች በገንዘብ ጉዳዮች፡ በመገናኛ ብዙሃን ጉዳዮች ማወቅ በመጨረሻ ኡማው -በግንዛቤውና በለውጣዊ ዜጋዊ ሃይማኖታዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተቋማቱ- እሱ ነው የአፈጻጸምን ደህንነት ዋስትና ያለው፡ እሱው ነው ተቋሞችን የሚያንቀሳቅሰው እነዚያን በሚናቸው የህዝብ መሰረቶችን በመገንባት የሚሳተፉ አቅጣጫውን የሚያስይዙ የአፈጻጸምን ደህንነት የሚጠብቁ መስነፍንና ድንበር ማለፍን፡ የአፈንጋጮችንና የቸልተኞችን እጅ መምታት ከመግለጽ አትዘነጋም ችላም አትልም።
ከተመራማሪዎችና የስነ ትምህርት ባለሙያዎች የለውጥ አቀንቃኞች ማየትንና

ሳይንሳዊ ጥናት መጠናት የሚሻ ጉዳይ አለ፡ በሱ ጉዳይ ከሁሉም ህዝብና ሙስሊም ሃገር ጋር በማህበራዊም ሆነ ፖለቲካዊ ውሳኔ ለመወሰን። ይህ ጉዳይ እሱ ዜጋውን የምርጫ መብቱን መምረጥም ሆነ መመረጥ ለመተግበር ብቁ የሚያደርገውን መወሰንና ፖለቲካዊ ህጋዊ ውሳኔዎችን በመወሰን መሪዎችን በመምረጥ መጋራት፡ የጥቅም ባለቤቶችና በምዕራቡ ስርዓቶች ውስጥ የመገናኛ ብዙሃኑንና ትምህርትን የህዝብን ሃብቶችና የባንኮች ገንዘቦች የተቆጣጠሩት የኡማውን ፍላጎት ለማጭበርበር ብልሹ እነሱን መበዝበዝ የፈለጉትን አቅጣጫ ማስያዝ በነሱ ላይ ጫና መፍጠር የሚቀል መሪዎችን መፍጠር በእርግጥም ችለዋል። የህዝቡን ፍላጎት ለማጭበርበር ከሚጠቀሟቸው ስልቶችና መንገዶች ውስጥ -በብዙ ሃገሮች ውስጥ- ከታዳጊ ወጣቶችና እድሜ ትንንሾች የቁጥር ብዛትን መፍጠር መሞከር ነው፡ እነዚያን በሕይወትና በማህበረሰብ ጉዳዮች በቂ ልምድ የሌላቸውን፡ አብዛኞቻቸው ተግባሮቻቸውና ምርጫዎቻቸው በማህበረሰቡ ላይ መንፈሳዊና ማህበራዊ አቅጣጫዎችንና ቀጥተኛ ያልሆኑ ውጤቶቻቸውን የረጅም ጊዜ ተጽዕኖቻቸውን አይገመዘቡም፡ ለመጥፎ መዝናኛዎች ነጋዴዎች ለብልሹ ራስወዳድ ጥቅሞች ፕሮፓጋዳ ማሽኖች ሰለባና ፈረስ ሆነው ይወድቃሉ። ከዚያ ነገር ማህበራዊ መፈረካከስና እሴቶችን ስነምግባሮችን ውድቅ ማድረግ ይፈተራል።

ይህ ደግሞ በቁሳዊ “የሰው ልጅ አእምሮ የፈጣሪን መኖር አለመኖር ማወቅ አይችልም ብሎ የሚያምን” ማህበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት ያለው ቢሆንም እሱ በኢስላማዊ መንፈሳዊ ስነምግባራዊና ሰውኛ ግንባታዊ ስልጣኔያዊ ማህበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት የለውም አይታሰብም።

በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ በአጠቃላይ ፖለቲካዊ ጉዳይ ውሳኔ ውስጥ መሳተፍ ግለሰቡ ጥቅሞችን ማስገኘት በሰላማዊ ህጋዊ መንገዶች መሆን አለበት በሚል ግንዛቤ መሰረትና የተለያዩ የማህበራዊ ስነምግባራዊ ኢስላማዊ አቅጣጫዎችን መጠበቅ አለበት የሚል እምነት አለ፡ በማህበረሰብ ትርጉም፡ በቤተሰብ ትርጉም፡ የሴትንና የህጻንን መብቶች መጠበቅ፡ ጥፋቶችንና ወሰን ሃላፊነቶችን በመከልከል እነዚያን ግፎችን የሚያሰራጩ፡ ስነምግባሮችን የሚያበላሹ፡ ቤተሰብን የሚያፈርሱ፡ ግንኙነቶችን ያዳክማሉ፡ የማህበረሰቡን መሰረቶች ያፈርሳሉ። ስለዚህም የድምጽ መስጠትንና የመመረጥን እድሜ ዝቅ በማድረግ ማጋነን አተቃላይ የማህበረሰቡን ጥቅሞች በማገልገል አይወጣም፡ ይልቁንስ በጥቅሉ የራስ ወዳድ የግል የጥቅም ተኩላዎችን ጥቅም ያገለግላል፡ ብቃት የሌላቸውን መሪዎች

መምረጥን ያስከትላል ፖለቲካዊ ውሳኔዎችን በለጋ እንጨትና በአናሳ እውቀትና ልምድ ህዝቦች ስም መወሰንም ያስከትላል።
የዘመናዊ ህይወት ጉዳዮች በፋብሪካዎችና ቴክኒኮች እውቀት ዘመናዊ ማህበረሰብ ውስጥ የመሪና የሞያ አባሎችን የማዘጋጀት አድማሶች መስፋት አብዛኛዎቹን ታዳጊዎች በትምህርት ገበታ ላይና በስልጠና ላይ የአንዳቸው እድሜ ከሃያ አመታት እስከሚያልፍ ድረስ ያቆያል በስራው ዓለም ሳይገባ በፊት በመቀጠልም የጋብቻን ህይወት ለማከናወንና ማህበራዊ ስነምግባራዊ ተጠያቂነቱን ሳይገነዘብ በፊት፡ በቤተሰብና በማህበረሰብ ውስጥ የተለያዩ ወገኖችን የመጠበቅን አስፈላጊነት ሳይረዱ በፊት።
የሙስሊሙ ማህበረሰብ ባህሪና አላማዎቹ ግቦቹ ታዳጊውንና ወጣቱን ቁሳዊም ሆነ ሞራላዊ ስልጣኔያዊ ተጠያቂነቶቹን ለመረዳት ፓይ እስከሚሆን ድረስ ከፍ ያለ የምትክነት ሚናውን እስከሚገነዘብ ድረስ። ከዚህም በሙስሊሙ ማህበረሰቦች ውስጥ ተስማሚ እድሜን መወሰን ጠንካራ ለሆነ ጥናትና ምርምር ለግምገማ ማቅረብ የግድ መሆኑ መጣ ሙሉ ወደ ሆነ እምነት ለመድረስ ከኢስላማዊ ስልጣኔያዊ ልምድና ከዘመናዊ ማህበራዊ ጥናቶች የዘመናዊ እድገት ፍላጎቶች በመነሳት፡ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ኢስላማዊ ውሳኔ በመወሰን የበሰለ ጠንቃቃ ቀጥተኛ ተሳትፎን ለማረጋገጥ፡ የማህበረሰብንና የቤተሰብን የግለሰብን ጥቅሞች በሚያገለግል መልኩ፡ የህዝቡን እሴቶችና ግቦቹን በውስጥ በውጭም፡ በኡማው ልጆች መሃከል በተለየ ሁኔታ በአጠቃላይ በሰው ልጆች መሃከል ከፍትህና መተዛዘን መረዳዳት አኳያ። ዋናው ጥያቄ፡ የኢላማዊ ለውጥ ሰዎች የንቃቱንና የለውጡን የግንባታውንና የሚያስከትለውን ቅኝ ርቀትና የኡማውን ማዕከላዊ አመራር ሚና መመለስን ከዬት ይጀምራሉ? በኡማው አስተሳሰብና በፖለቲካዊ ታሪኩ ውስጥ የአምባገነናዊነትና የብልሹነትን ተያያዥነት መጨረሱ እንዴት ይረጋገጣል? ! የተመራማሪዎችና የስነ ትምህርት ባለሙያዎች ትግላቸው መረባረብ አለበት፡ ኢስላማዊ ፍጥረተ ዓለማዊ ስልጣኔያዊ እይታን በመግለጽና በህዝቡ ልጆች ሃሳብና በህሊና ውስጥ መልሶ መገንባት፡ ከተከበረው ቁርአን ከተከበረው ነብያዊ ሱና የመነጨ እንዲሆን በጊዜና በቦታ ተጨባጫችን ላይ ተግባራዊ የማድረጉን ጥበብ የመግለጽም የተከበረውን ቁርአን የዘረዘረውን ጉዳይና የገለጸውውን ከሱ ላይ ሽፋኑን ያነሳውን፡

ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ጉዳይ በምድር ላይ ተተኪ በማድረግ፡ በጭቃዊ እንስሳነቱ ውስጥ መንፈስን በመንፋት፡ ኣላህ ለሱ ከሰጠውም መሳሪያዎች፡ ከፍላጎትና ምርጫ አደራም ያስገደደውን፡ ለሱ ለገንባትና ለማቅናት ያገራለትን አቅሞችና ችሎታዎች፡ ኣላህ ምድርንና በምድር ላይ ያሉትን ነገሮች ያሉትን ሰዎች እስከሚወርስ ድረስ የሰው ልጅ ራሱንና ተፈጥሮውን እውን እንዲያደርግ፡ የቁርአናዊ ፍጥረተ ዓለማዊ ስልጣኔያዊ እይታ እሱ የሰውን ልጅ ትርጉምና ለእውነተኛ ተፈጥሮው ያለውን ግንዛቤ የአቅሞቹንና የችሎታዎቹን የተገኘለትን የአላማ ይህን ህይወት ሲሰጥ የሚናውን ባህሪ ትርጉም መግለጽና እውን ማድረግ ነው።

ይህ ለሰው ልጅና ለፍጥረተ ዓለም ለሕይወት ቁርአናዊ አጠቃላይ እይታ፡ በማንኛውም ሁኔታ በሰው ልጅ ወይም በፍጥረተ ዓለም ልምዳቸው ውስጥ በሌላ ባህሪ ወይም ጥሩ አፈጣጠር ሸክሞችና መቸገር ወይም ማስገደድ አይደለም ይህ እይታ ጥሩ የሰው ህልውናን በ"ትዳር ጓደኞች መካከል ጥሩ ግንኙነት" ውስጥ ማረጋገጥ ነው።

እንዲሁም "በጂሃድ እስጥ ሰማእትነትንና ድንበር ማለፍን መከልከል ከክብሮች መከልከልን" በመፈለግ ውስጥ እንዳለው፡ እሱም በዚህ ህይወትን መምራት ነው በሁለቱም አገር እደለኛነትና ልቅናን ክብርን ማምጣት ነው። ኢስላማዊ እይታን ማስመለስና መግለጹ ከመቀየርና ከማጠልሸት ማዳኑ ያስከትላል የአስተሳሰብ መንገዶችና የአስተዳደግ ስልቶች ባህሪ ማጥራት፡ ስልጣኔንና ግንባታ መገንባት።

የህዝቡን እድገት መፈለግና፡ የእይታና እንዲሁም የግንዛቤ መፍጠርን ህጎች መደልደል መጀመር የእምነት ማሳመርንና እውቀታዊ አስተሳሰብን ተቋማዊ ስነትምህርትን መጀምርም እሱ የተመራማሪዎቹ የስነ ትምህርት ባለሙያዎቹ የለውጥ አንጋቢዎቹ ተግባር ነው፡ እነዚያ የእምነታዊ አስተሳሰባዊ ስነ ትምህርታዊ ለውጥ እንቅስቃሴ መደገፍና ወደ ማህበረሰቡ ማድረስ ያለባቸው፡ የለውጥንና የማሳመርን ሃሳብ ለማመንጨት የመሰረት ድንጋ ከሚወክለው ቤተሰብ በመጀመር፡ በትምህርት ቤትና በመምህር በደዕዋ አድራጊዎች በመስጂድ መሪዎችና ኸጢቦች

(ንግግር አድራጊዎች) በማለፍ እነዚያ ገባጮች ከመሆን አለመቆጠብ የሚጠበቅባቸው፡ እንደውም መሪዎች አባቶችን በሳይንሳዊ ስነትምህታዊ አስተሳሰብ የሚያሳዩ የስነ ትምህርት ባለሙያዎች መሆን የሚገባቸው በልጆቻቸው አስተዳደግ ሁኔታ፡ ኢስላማዊን እሴት በታዳጊ ህይወት ውስጥ ወደ ምግባራዊ ማህበራዊ ተግባር በመለወጥ፡ በዚያ ጉዳይ አጠቃላይ ብዙሃን መገናኛዎችና

ተጽዕኖ ፈጣሪ ቀጥተኛ ትምህርት የሚደግፉቸው ሆነው፡ ሁሉም የመገናኛ ዘዴዎች፡ መልእክቱን ወደ ማህበረሰቡ በሁሉም አይነቶቹና ደረጃዎቹ በጥሩ ሁኔታ ማድረስ እንዲገኝ።

ለውጥን ለማምጣት ይፋዊ ቢሆኑም ባይሆኑም አምባገነን ብልሹ ስርዓቶች ተቋማት ላይ መደገፍ ከታላላቅ ስህተቶች ይቆጠራል፡ ተቋማት በዬትኛውም ስርዓት ውስጥ በተፈጥሯቸው ያለውን ሁኔታ ወደ ማረጋገጥ ይሮጣሉ ወደ መለወጥ አይደለም።

የለውጥ መነሻ የአባቶችና እናቶች ተፈጥሮ መሆኑ ጥርጥር የለበትም የልጆቻቸው ጥቅም ባለበት በመጓጓት፡ በህጻኑ ላይ ከወላጆቹ የበለጠ ተጽዕኖ ሊፈጥርበት የሚችል የለም። ተፈላጊዋ ፍሬ ከማስተካከልና መለወጥ ፍሬዋን እንድትሰጥ ተመራማሪዎችና የስነ ትምህርት ሰዎች አብሪ የደዕዋ ሰዎች ላይ አባቶችንና እናቶችን ለልጆቻቸው ጥቅም ያለውን ነገር ግንዛቤ መስጠት ነው፡ በጥሩ አመለካከቶች ላይ ማሳደግ ነው፡ “በአንዳች ነገር ላይ ያደገ ሰው በሱ ላይ ያረጃል” ያለውን ይመስል “ከናንተ በድንቁርና ጊዜ ውስጥ ምርጦች የሆኑት በኢስላምም ውስጥ ምርጦቻችሁ ይሆናሉ አዋቂዎች ከሆኑ” “እንደሁኔታችሁ ይሾምባችኋል”

إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُغَيِّرُ مَا بِقَوۡمٍ حَتَّىٰ يُغَيِّرُواْ مَا بِأَنفُسِهِمۡۗ ﴿١١﴾ (الرعد:١١).

“ኣላህ በህዝቦች ዘንድ ያለውን ጸጋ በነፍሶቻቸው ያለውን ሁኔታ እስከሚለውጡ ድረስ አይለወጥም ” (አል-ረዕድ፡11) ።

ያኔ ኡማው በድጋሜ ተቋሞቹን ከውስጥ ለመገንባት በሰላም የህይወቱን አይነት ለማሳደግ ይችላል፡ ሃይል መጠቀምን ሳይሻ፡ ያም የአባባሎችንና የመሪዎችን አይነት እንዲሁም የተቋማቱን ይዘት በመቀየር ይሆናል፡ የፍትህን ህይወት ለማረጋገጥና ለማቋቋም፡ የክብር እኩልነት፡ የወንድምአማችነት፡ የመስጠት የማጥራት የማሳመር መንፈስ ህይወትን ለመገንባት፡ የኡማውን ቁርጥ ሃሳብ ለማንቃትና አቅሞቹን ለማጕልበት ገንቢ የተሻለ ስልጣኔያዊ ሚናውን ለመመለስ፡ ጉዞውን እንዲቀጥል፡ ያኔ የመረዳዳትና የለውጥ የግንባታ የሰላም ዓለም ህጐች ይደላደላሉ በጫካውና በግፉ በውድመቱ እንዲሁም በቅኝ ግዛቱ ዓለም ምትክ።

## (ከዘመናዊ ኢስላማዊ ቡድኖችና እንቅስቃሴዎች ተፈላጊው አቋም)

## (የመንገዱ )

ባለፉት ገጾች "የአምባገነንነትና የማበላሸት ጣጣ በኢስላማዊ ታሪክ ውስጥ" በሚለው ርእስ ጥናት ስናካሂድ በደረስንበት መሰረት፡ በአጠቃላይ ዐረብ ሃገሮችና በተለይ በግብጽ በተከሰተውና ዛሬም እየተከሰተ ባለው እንቅስቃሴ መሰረት (ግብጽ በዐረቡ ዓለምና በመካከለኛው ምስራቅ አካባቢ ምህዋራዊ ክብደትና ሚና ስለ አላት) ጥያቄው ኡማው በመንትያ መንገድ ላይ ነውና ለነኚህ ኢስላማዊ በድኖችና እንቅስቃሴዎች ትክክለኛ አቋምና መንገድ ምንድነው የሚለው ይሆናል ? አቋሞቻቸው ወደ ስርዓቶቹ ለውጥና ተከታይነትን ወደ ማጠናቀቅ ያደርሳልን፡ ወይስ የአረቡንና የኢስላሙን ዓለም ለመበታተንና ስርዓት አልበኛነትን ለማሰራጨት፡ ተጨማሪ ትግሎችን በዘራዊና ቡድናዊ መሰረት ለመፍጠር፡ በመቀጠልም ተጨማሪ ድክመትና ኋላቀርትን ተከታይነትን በመፍጠር ግልጽ የተደረጉ እቅዶችን ወደ ማገልገል ነው ? ትክክለኛና በላጩ ኡማው አዲስ ማህበራዊ ፖለቲካዊ ለዘመናዊ ኢስላማዊ ስልጣኔያዊ እድገትና ለውጥ መገንባት ነውን ወይስ የለውጥና የማስተካከል እንቅስቃሴዎች የኢስላማዊ እንቅስቃሴ ቡድኖች ከመንጋውና ውጭ መዘመር ነው ? እሱ ደግሞ ለጠላቶች በውጭም በውስጥም በዚህ ለውጣዊ የማስተካከል እንቅስቃሴ መክበብና ማፍረስን የሚያቀልላቸው ነው፡ በተለይ የማስተካከልና የለውጥ እንቅስቃሴዎች ግምታዊ ቅጽበታዊ የውሸት ጥቅሞችን ማግኘት የጓጉ ጊዜ፡ ያኔ ከአብዮትና እንቅስቃሴ የተከሰተው ከዲክታቶሮችና ከውድቀት መፈንቀለ መንግስቶች አንዱ አዲስ ቀለበት ብቻ ነው የሚሆነው፡ እነዚያን የሰማእታቶችን ደም የሚያጠፋ አምባገነንና ብልሹ ስርዓቶችን ማደላደልም ያስከትላል፡ በመቀጠልም ሌላ ታሪካዊ እድል ከኡማው እጅ ያመልጣል፡ የነጻነት ጊዜ እንደ አዲስ ይጀመራል የጥራትና የለውጥ እንቅስቃሴዎች ትግሎችን ከግፎችና ፍርሰቶች ውርደቶች ረጅም ክፍለ ዘመናቶች በኋላ ዘውድ ለመጫን።

ከነዚህ ትምህርቶችና ተግሳጾች ካልተማርን ተጠባባቂ ጠላቶች የኡማውንና የወጣቶቹን አቢዮት በህዝቡ ላይና በምጣኔ ሃብቶቻቸው ላይ ተጨማሪ ጨቋኝ ቁጥጥራቸውን ተግባራዊ ያደርጋሉ ኋላ ቀርነታቸውንም ያደላድላሉ

ድልቦቻቸውንና ሃብቶቻቸውንም ይቀማሉ አሁጉሮቻቸውንና ምድሮቻቸውን ህዝቦቻቸውን የመከፋፈል እቅዶቻቸውን ተግባራዊ ያደርጋሉ።
የለውጥ እንቅስቃሴዎች በሙሉ በተለይ ኢስላሚስቶቹ ለአጋጣሚ ፍርፋሪ ጥቅሞች መጓጓት ኡማውን እጥፍ ድርብ ዋጋ ለመክፈል የሚደረግ መሆኑን መረዳት አለባቸው፡ በአዲስ መልኩ የግፍና የብልሽት የአምባገነንነትን ሃይል ያመቻቻል፡ የትላንቶቹን መራራ ልምዶች እንዳየነው፡ ወደፊት የሚመጣው ደግሞ በጣም የመረረና የከበደ ነው የሚሆነው።
በዒራቅ የተከሰተው ለታቀደውና ለተገለጸው ናሙና ነው፡ የሱ አምሳያ በብዙ ዐረብና ኢስላም ሃገሮች ተከስቷል እየተከሰተም ነው እንደ ሱዳንና ሰማሌ የመንና ፓኪስታን፡ ይህን ያስጠነቅቃል በሴሜን አፍሪካና በምዕራቡ ከነሱም ውጭ ከኢስላሙ ዓለም አህጉሮች የተከሰተውና እየተከሰተ ያለውም።
ወደ ዒራቅ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ወታደሮች በእርግጥ ገብተዋል፡ ከዚያም ጋር ሃገሩን በስርዓት አልበኛነት ሁኔታ ላይ አድርገውታል፡ ሁለት ሚንስትሮችን መቆጣጠር ሲቀር አንዱ የነዳጅ ዘይት ምኒስተር ነው፡ ከዚያም አገሮችን በውሸትና በሃሰት አያያዟቸው፡ ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች ሆንብሎ የታቀዱ ግጭቶች በዐረቦች መካከል ፈተናዎችን ለመቀስቀስና ቅጥረኛ ወታደሮችን ገልግለዋል፡ ወደ ሁለት የሚጋጩ የሚጣሉ ጭፍሮች ለመክፈል በቡድናዊ መሰረት ላይ በደቡብ ሺዓ በመካከል ሱና፡ የሱና ሰዎች ደግሞ በዘር መሰረት ተከፋፈሉ በመካከልና በደቡብ ዓረብ በሴሜን ኩርዶች።
ይህን ይመስላል በሴሜን አፍሪካ ሞሮኮ ላይ እየተከሰተ ያለው፡ ያ ከዐረቦችና አማዜጐች የሚመሰረተው ከኢባዲያና ከማሊኪያም ነው የሚመሰረተው፡ የዚሁ አምሳያ ነው ከሃይማኖትም ሆነ ከዘር በኩል ከጐሳ በፓኪስታንና በአፍጋኒስታን በምዕራብ አፍሪካ። ጉዳዩን ካልደረስንበትና ካላስተካከልነው እጣፋንታችንንና ውሳኔያችንን በእጃችን ካላደረግን፡ ጠላቶች ይጠባበቁናል፡ ከጨለማው እጣፋንታ ገዢም ተገዢም አይድንም።
በበህረይን ግዛት ውስጥ ከወገንተኛ ፍልሚያ እየተከሰተ ያለውን አንርሳ የበለጠ ከምፈራው ነገር ከአዋቂ ተከታታይ የማይደበቀው የሁኔታ መመቻቸት ነው ይህ ግጭት ለአምስተኛ ጠላቶች እቅድ የሚያወጡለትና የሚያስተናብሩት ለባህረ ሰላጤ ጦርነት መግቢያ እንዲሆን ይህ ጦርነት ለኡማው በአጠቃላይ በሁሉም የባህረ ሰላጤው ሃገሮች በተለየ ሁኔታ ካለፉት ሁሉ አረመኔ ይሆናል፡ የባህረ

ሰላጤው ሃገሮች በሙሉ ስለሚፈርሱ፡ ከተለያዩትም የበለጠ ስለሚለያዩ ከተቀሙትም የበዛ ስለሚቀሙ ከማውደሙ የህይወትና የመገኘት ምንጭ የሆነው ውሃ እንኳን አይድንም፡ እነኚህ ህዝቦችና መንግስቶቻቸው የሚያካብቧቸውን አደጋዎችና የሚመጡባቸውን ሁኔታዎች ካልደረሱባቸው በስተቀር፡ ጉዳዮቻቸውን በአእምሮና በፍትህ በትክክል ካልፈቱ በስተቀር፡ እድሉ ከማለፉና ጊዜው ከማምለጡ በፊት፡ ከመራራ ትምህርቶችና ከጠንካራ ተግሳጾች ያለፉትም ይበቁናል።

የኢስላማዊ እንቅስቃሴ ቡድኖች በዚህ ያልታሰበ መንትያ ላይ ጠንካራ መቆምን መቆም እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው ይልቁንም እሱ ዱብዳ ነው "የግመሉን ጀርባ ያደቀቀው እንጨት ነው" የህዝቡ ሁኔታ ከውርደትና ረሃብ ስራፈትነት አምባገነንነት ብልሽት ጣሪያ የደረሰ ጊዜ ህዝቡንና በተለይ ወጣቱን ክፍል በሁለት ምርጫዎች መካከል አደረጋቸው፡ ወይም መሞት፡ ወይ ለውጥ ክብር የመኖርን ጉራሽ ለማግኘት የመስራት ክብር።

በነኚህ ከታሪካችን ቁርጥ ቅጽበቶች ከግንዛቤያችን የሰው ልጅ በኢስላም ውስጥ በተፈጥሮ የተከበረ መሆኑ እንዳይርቅ የግድ ይሆናል፡ ያም በወንድምነቱ መብት ነው ከአንዲት ነፍስ በምድር ላይ ተተኪ እንዲሆን፡ በሷ ውስጥ የህይወትን የመገንባቷን ተጠያቂነት እንዲሸከም፡ ይሃ በሰው ልጆች መካከል እኩልነትንና በመካከላቸው የባህሪያቶችንና የአቅሞችን መበላለጥ ጥበብ ማን የግድ ያደርጋል፡ ነጩና ጥቁሩ ቀዩ ቢጫው አለ፡ ብልህና የበለጠ ብልህ፡ ደካማና ሃይለኛ የበለጠ ሃይለኛም አለ፡ ጥበቦችን የሚወድ፡ እውቀቶችን የሚወድ አለ፡ ጤናማ ጠንካራ አለ፡ ደካማ አካለ ስንኩል አለ፡ ነገር ግን እነሱ ሁላቸውም በሰው ልጅ ክብራቸው እኩል ናቸው፡ በአቅሞችና በችሎታዎች እንኳን ቢተላለፉ። ይህ መተላለፍ እሱ የሞሞላላትና የሰው ልጅ ፈጠራ ፍሬ ነገር ነው ያ ህይወት በሱ መሰረት ላይ የምትቆመው ማህበረሰቦችና ህዝቦች ኡማዎች የሕይወትን ጉዳዮች የሚገነቡትናየሚሞሉበት።

በምድር ላይ ምትክ መሆንና የሰው ልጅ ክብር መረዳዳትን የግድ ያደርጋሉ፡ ምክንያቱም እጁን ለሚዘረጋ ፈላጊ ክብር የለውምና፡ ስለዚህም አቡበክር በውስራ ዘመቻ ሁሉንም ገንዘባቸውን ሰደቃ ላይ አውለውታል፡ ኣላህና መልዕክተኛው የሃገሩ መሪ ለሳቸውና ለቤተሰባቸው ጉዳይ ዋስ ስለሆኑ።

ከዚያም በፊት ስደቶኞቹንና ረዳቶቹን በወንድምአማችነት ማስተማርና በመካከላቸው ገንዘብን መከፋፈል ማጋባት ስለተከሰተ፡ "ሱፋ"ም ለሚሻው ሰው

ምግብን ለማቅረብ ቦታ እንደሆነ ሁሉ እሱ ነው ያ የዚያን ትውልድ ጥንካሬና ያሳካውን ነገር የሚብራራልን፡ እሱ በሺዎ ይቆጠር የነበረ ከመሆኑም ጋር፡ ለምን ሎማ እነደሆኑም ያብራራልናል፡ ራስ ወዳድ የማይስማሙ ግለሰቦች ያልሆኑት።

ባደጉት አገሮች ከዋስትናዎችና አገልግሎቶች እንዲሁም እርዳታዎች የምናየው የነዚህን ህዝቦች አኗኗሪዎች መረዳዳት ገሃድ ያደርጋል፡ ለምን እነሱ እርስ በርሳቸውም ሆነ በሌሎች አጠገብ ለማንም መንካቱ የማይቀልና እሱን መንካቱ የማይፈቀድ ክብር እንዳገኙ ያብራራልናል።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እይታችንን ወደመጨረሻይቱ መልዕክት ማዞራቸው አይደንቅም፡ እንዲሁም ወደ አመለካከቶቹ እነዚያ የሰው ልጅመመሪያ መንገድ ፍሬ ነገር የሆኑት እስከ እለተ ትንሳኤ ድረስ ቀጣይ ወደሆነ ፍላጎቱ (ማለትም የመልዕክቱን አመለካከቶች አዳጊና ተለዋዋጭ በሆነው ጊዜና ቦታ ተጨባጭ ላይ በድጋሜ ተግባራዊ ወደ ማድረግ) በየመቶ ዓመት ሁሉ (ማለትም ግዜው በራቀቁጥር) ። የቁርአን አመለካከቶችን ተግባራዊ ማድረግን ማደስ የግድ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ስለሆነ በዱትም ቦታና ጊዜ፡ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ምዕተ ዓመታቶች ባለፉ ቁጥር ሃማኖቱን "ማደስ"አስፈላጊ ወደመሆኑ አንቅተውናል። ከዚህ በመነሳት ለህዝቡ አጠቃላይ ጉዳይን በማስተዳደር ምህዋራዊ የሆነን ይህን አመለካከት ተጨማሪ ገለጻ ለማድረግ ሲባል ምሳሌ ማምጣት የግድና አስፈላጊ ሆኖ እናያለን። የመመካከር አመለካከት

وَأَمْرُهُمْ شُورَىٰ بَيْنَهُمْ ﴿٣٨﴾ (الشورى:38)

"ነገራቸውም በመካከላቸው መመካከር ለሆነው" (አል-ሹራ፡38) አጠቃላይ

(ፖለቲካዊ) ሕይወት ጉዳዮችን በማስተዳደር እስከ አንድ ምዕተ ዓመት በፊት - በሩቅ ግምት- የሃገሪን መሪ ለመምረጥ በዋና ከተማ ሰዎች ብቻ ያሳጥር ነበር፡ ምክንያቱም ይህ አደገኛ ስልጣንና ተጠያቂነቶቹ ተጓገችና መንገደኞች ከሃገሪቱ አቅጣጫዎች ክልሎች ለመናገርና ቃል ለመግባት እስከሚመጡ ድረስ ባዶ መሆንየሚታሰብስላልሆነ።

በአሁኑ ጊዜማ ዘመናዊ መሳሪያዎች "የምክክሩን" ተግባርና ምርጫውን ለአጠቃላይ የህዝቡ ግለሰቦች ቀላል ነገር ያደርጋል። በአህጉራዊ ሃገሮች ውስጥ ለምሳሌ እንደ አሜሪካ የተባበሩት ግዛቶች ምርጫው ጠዋት ይጀምራል ውጤቱ ደግሞ ማታላይ ይታወቃል ይነገራልም። በዚህ አይነት ሁኔታ ላይ ለዋና ከተማ ነዋሪዎች እንደ

ዋሽንግተን የሃገሪቱን መሪ የመምረጡ ጉዳይ በነሱ ላይ ብቻ እንዲያጥር ችክ ለማለት እድል የለም፡ ሌሎች ቀርተው በክልሎችና በተራራቁ አካባቢዎችከሚኖሩት።

ከዚህ በመነሳት በኢስላማዊ እንቅስቃሴ መነሳት ሁኔታዎች መሃከል ኦቶማን አመራር የመውደቁና የቅኝ ግዛት አውሮፓውያን ሃገሮች የተረፉትን ኢስላማዊ ሃገሮች የመውረር ጊዜ ያለውንና አሁን በተጨባጭ ባሉት ሁኔታዎች መካከል ያለውን ማስተካከል ትክክል አይሆንም። በዚያን ሰዓት ኢስላማዊ እንቅስቃሴ -የግድስለሆነ- ለተንኳሹ ቅኝ ግዛታዊ ጥቃት የአጸፋና የተቃውሞ እንቅስቃሴ ትወክል ነበር፡ የመጨረሻውን ምሽግ የኢስላማዊ ኦቶማናዊ አመራር ሀገር ውስጥ እውን የሆነውን ለመጨረስ ያለመውን ጥቃት።

ዛሬማ የተለያዩ ኢስላማዊ እንቅስቃሴ ስርዓቶች ላይ ስራቸው የመጀመር ሃላፊነትና የተጠና ከተጨባጭ ጋር ከሁሉም ተግዳሮቶቹና አቅሞቹ ጋር የተብላላ ስራ እንዲሆን የግድ ይላል፡ ሀገርን በድጋሜ ለመገንባትና ማህበራዊ ፖለቲካዊ ለውጣዊ የእድገትና ሙናዊ ኢስላማዊ ዘመናዊ ስርዓት ለመግለጽ።

## ደዕዋ (ወደ አላህ መጣራትና) ፖለቲካ

አብዛኞቹ ኢስላማዊ ሃገሮች ውስጥ የኢስላማዊ እንቅስቃሴ ተቋማት የሚጋፈጡት ታላቁ ችግር እሱ የትክክለኛ ግንዛቤ ችግር ነው ለሁለቱ ስራዎች ባህሪ የደዕዋና የፖለቲካ እንዲሁም የሁለቱ መንገዶችና ስልቶች ሜዳዎቻቸው፡ በትክክለኛ ግንዛቤ ኡማው ሁለታቸውንም የማህበረሰቡንና የኡማውን ግንባታ በአርኪ መልኩ በመመለስ ላይ ተግባራዊ ሊያደርገው ይችላል፡ እንደዚሁም የኢስላምን ግቦችና እሴቶቹን አመለካከቶቹን አላማዎቹን እውን ማድረግ ይችላል። የደዕዋ ስራ እሱ እሴታዊ ስነምግባራዊ ማህበራዊ እንክብካቤ ማድረግ ነው  ይህ ሚና ችሎታዎችንና ለኡማው ምቾት የግድ የሆኑ ሕይወታዊ ክህሎቶችን ማስተማርና ጉዳዮቻቸውን ማሟላት ተቋማት ሚና ጋር አይጋጭም። ፖለቲካዊ ስራማ አጠቃላይ የሕይወት ዘርፎችን ወደ ማስተዳደር የሚያልሙ ፕሮግራሞች ጋር የተያያዘ ነው፡ የማህበረሰቡን በሁሉም ዓይነቶቻቸው ጥቅሞች ዬትኛውንም ዓይነት ሳይጥሉ በሚያገለግል ነገር። የደዕዋ ቡድኖች ሚና በመሰረቱ የዲንን ቋሚ ነገሮችና እሴቶቹን አመለካከቶቹን አላማዎቹን በትክክለኛ ስልት በማስተማር ላይ ይመጣል፡ ያ መሪ መሃሪ ወዳጅ ከሆነው ኣላህ ውዴታ ንግግር የሚነሳ ያ አማኝን የሚወድና የሚንከባከብ፡ ምክንየቱም አማኝ ፍትህንና ለውጥን እውን ለማድረግ

ይሰራልና፡ በትክክለኛ ተፈጥሮው ኣላህ ግፍንና ግፈኞችን ወሰን ማለፍንና ወሰን አላፊዎችን ችክ ባዮችን ሞገደኞችን ይጠላል፡

وَٱللَّهُ لَا يَهۡدِي ٱلۡقَوۡمَ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٨٦﴾ (آل عمران:86)

"ኣላህ በዳዮችንም ሕዝቦች አያቀናም" (አሊ ዒምራን፡ 86)

وَٱللَّهُ لَا يُحِبُّ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٥٧﴾ ( آل عمران: 57 )

"ኣላህም በዳዮችን አይወድም" (አሊ ዒማራን፡57)

إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَهۡدِي ٱلۡقَوۡمَ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٥١﴾ ( المائدة: 51 )

"አላህ አመጸኞችን ህዝቦች አያቀናም" (አል ማኢዳህ፡ 51) የልቦናዎቻቸው ጨለማ የፍትሃዊውን ማቅናትና የእጅግ በጣም ርሕሩሕ በጣም አዛኙን እዝነት ብርሃንከመቀበልይከለክላቸዋልና።

ደዕዋ በዚህ አመለካከት በ"ኢስላማዊ ፖለቲካ" ሜዳ የመነሻ መሰረት ነው ያ ህሊናውን የአስተዳደርን ስርዓቶች ተቋማት በመገንባት ላይ በማስተዳደሩ እንድትጓጓ በሚያደርጋት፡ እንደዚሁም ፖለቲካዊ ህዝቦች ፕሮግራሞች፡ ሕይወታዊ ጥቅሞችን በእሴቶችና ከፍ ያሉ ኢስላማዊ አላማዎች እውን ማድረግንቻይእንድትሆን።

ኢስላማዊ ማህበረሰብን በድጋሜ ለመገንባት እውነተኛው ጦርነት ኡማው መብቶቹንና ግዴታዎቹን በማስመለስ ውስጥ ነው የተሰራው በስራ ነጻነት በመምረጥ ነጻነት በእምነት ነጻነት፡ ወደ መርሆችና እሴቶች ቁርአናዊ ኢስላማዊ አላማዎች የመጣራት መብት፡ እነዚያ የኢስላማዊ ልጆች ህዝቦች የማይለያዩባቸው፡ በአላህና በመልዕክተኛው በመጽሃፉ ማመንን ይመስል፡ ፍትህንና እኩልነትን ማሳመርን ጥራትን ማሰብን ይመስል፡ በማስፈርና ለውጥ ወንድምአማችነት መረዳዳት መንቀሳቀስ የነጻነትን እርካታን መብት ዋስትና ማግኘት፡ የተጠያቂነት ግዴታዎችን መሸከም መብቶችን መሸከም መብቶችን መስጠት የሰውን ልጅን ክብር መያዝ፡ የአምባገነንነትንና የብልሹነትን መልኮች ሁሉ መተው፡ የግፍንና የዘረኝነትን ተግባሮችመጣል።

የለውጥንና የእድገትን እኩልነት የደዕዋን ትግሎች ስኬት ተቋሞቹንም መጠበቅን እውን ለማድረግ ከምንም ሌላ ነገር በፊት ተፈላጊው እሱ የደዕዋንና የተቋሞቹን ስራዎች ከባለስልጣን ጭብጥ ነጻ ማውጣት ነው፡ ሃይማኖትን እንዳያጠላሹና

ስልጣኔ ለአስተዳደሮችና ለረዳቶቻቸው ጥቅሞች በማስገዛት እንዳትጠለሽ ስልጣንንና ሃብትን በአምባገነንነትና ብልሹነት ዘዴዎች ለብቻ ለማድረግ ሲባል። የደዕዋ ተቋማቶችን በጠሩ የደዕዋ ተግባራቶች እንጂ መስራት የለባቸውም ወደ ኢስላም እሴቶች በአጠቃላይ ሕይወት ግንኙነት፡ በአንድም ሰው ላይ ማንኛውንም ምርጫ ወይም እይታ በቅድሱ ስም የአንድ ፓርቲ ወይም የሌላን ወይም የቡድንን ወይም የሌላን ወይም ማንኛውንም ግለሰብ ሳይጭኑ፡ ይልቁንስ ደዕዋ አድራጊዎችና ደዕዋ ተቋማቶች የሁሉንም ሙስሊም የሁሉንም ዜጋ አእምሮ ማክበር አለባቸው፡ ማንነቱንና እሴቶቹን ጥቅሞችን ያረጋግጣሉ ብሎ የሚያምነውን እንዲወስን ምርጫውን ሊያከብሩለት ይገባል። ስለዚህም ማንኛውም ባለስልጣን ማንኛውንም ዜጋ ማዘዝና ምን መምረጥ እንዳለበትም ማስገደድ ትክክል አይደለም፡ ሰዎች በምርጫ መብት እኩል ናቸው በአጠቃላይ ጉዳይ የመመካከር ንግግር ወደ ሁሉም ሙስሊሞች የተሰነዘረ ነው፡ ሌላው ቀርቶ ወደ አንድ ጭፍራ ወይም ምሪ ሊቅና የበታች አይደለም፡ በዚህ ጉዳይ የደዕው ተጠያቂነት ሁሉም የሙስሊም ልጆች የተገነዘቡ በሃይማኖቶቻቸው እሴቶችና መርሆቹ በአላማዎቹ በቋሚ ነገሮቹ አማኝ እንዲሆኑ መኳኳቷ ነው፡ የዚህ መፍትሄው ጉዳዩ በስልጣን ሲጫን አይደለም ነገር ግን በተጨማሪ ማስተማርና ግንዛቤን በመፍጠር ነው እንጂ።

ከፖለቲካና ከኢስላም እሴቶችና ከመርሆቹ የመነጬት ፕሮግራሞችቹ አይነቶች ጋር ግንኙነት ያላቸው ነገሮች እነሱ የዜጎች ህዝቦች ከሙስሊሞችም ሙስሊም ካልሆኑትም በነሱ ጉዳዮች ላይ የሚስማሙበት ነው፡ ያለው ልዩነት እሱ ሙስሊሙ የኢስላምን እሴቶችና አላማዎቹን መያዝን ሃይማኖታዊና ስነምግባራዊ መያዝ አድርጎ ይቆጥረዋል፡ ጥቅማዊ መያዝ ሳይሆን።

ከሃቅ አውራ ጐዳና ያፈነገጡትን መፍራት የለም ህዝቦችም አያዳምጧቸውም ምንግዜም የተገለሉ አናሳ ሆነው ይቀጥላሉ የግል ሁኔታዎች ህግማ እሱ ያዜጋዎች በአይነቶቻቸው ሙስሊሞችና ሙስሊም ያልሆኑ የሚለያዩበት ነው ይህ ጉዳይ ለግል ምርጫ ይተዋል፡ ለማስገደድ ክፍተት የለውም

( البقرة : 256 )﴿لَآ إِكۡرَاهَ فِي ٱلدِّينِ ٢٥٦﴾

“በሃይማኖት ማስገደድ የለም” (አል በቀረህ፡256) ሁሉም ሰው ከምርጫው ተጠያቂ ነው። ደዕዋ አድራጊዎች ኡማውን ወደ እስልምና የመላሰው ልጅ ሃይማኖት ማጣራትን ቢያሳምሩ፡ የክብርንና የነጻነትን የፍቅርን የፍትህን የመረዳዳትን ሃይማኖት ንግግር ቢያሳምሩ የትክክለኛ ልቦናዎች ምርጫ ኢስላም

ይሆን ነበር፡ ያ መልካም ስራንና የሰው ልጅ በዱንያ ሕይወት ላይበማሳመርና በመማር የተከበረ ምትክ እንዲሆን መንቀሳቀስ እንጂ የማያልም

۞ إِنَّ ٱللَّهَ يَأۡمُرُ بِٱلۡعَدۡلِ وَٱلۡإِحۡسَٰنِ وَإِيتَآيِٕ ذِي ٱلۡقُرۡبَىٰ وَيَنۡهَىٰ عَنِ ٱلۡفَحۡشَآءِ وَٱلۡمُنكَرِ

وَٱلۡبَغۡيِۚ يَعِظُكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَذَكَّرُونَ ۝٩٠ ( النحل : 90).

“አላህ በማስተካከል በማሳመርም ለዝምድና ባለቤት በመስጠትም ያዛል ከአስከፊም (ከማመንዘር) ከሚጠላም ነገር ሁሉ ከመበደልም ይከለክላል ትገነዘቡ ዘንድ ይገስጻችኋል“ (አል-ነህል) ፡፡ ማመን አለብን ነገሩ

كُنتُمۡ خَيۡرَ أُمَّةٍ أُخۡرِجَتۡ لِلنَّاسِ ۝١١٠ ( آل عمران : 110 )

“ለሰዎች ከተገለጸች ህዝብ ሁሉ በላጭ” (አሊኢምራን፡110)

ለሆነ ህዝብ መሆን አልነበረበትም አሁን ባለበት ደረጃ ከብቸኝነት ከራስ ወዳድነት ከኋላ ቀርነትና ከውርደት ለኢስላም አስተሳሰቡንና አመለካከቱን ባጋጠመው ነገር ምክንየት እንጂ በታሪኩ ውስጥ የደዕዋ ትግሎች መመናመን ሳቢያ፡ ያ የኡማው አስተሳሰብና ባህሉ ወደ መዛባት ያደረሰ የሆነ፡ ይህም የሆነው “የነገስታት ህብረቶች” የ “ካህናት ህብረቶችን” በመመልመላቸው ምክንየት ከተማሩትና ከሙያተኞች ከመረጃ ሰጪዎች፡ ከነዚያ በሃሰትና በውሸት የሃይማኖትን ካባ ከለበሱት፡ የካህናት ማህበራት በቅዱስ ስም እውቀትንና ትክለኛነትን የብቻ በማድግ በውሸት ተናጋሪዎች እንዲሆኑ፡ የ“ነገስታቶችን ማህበራት” ለማገልገል፡ ስልጣንንና ሃብትን የብቻቸው ማድረግን እንዲችሉ ለማደላደል፡ በታሪካችን ውስጥ እንዳየነው እንደምናየውም፡ በበርካታ ኢስላም ሀገራት ውስጥ በአሁኑ ጊዜያችን፡፡

## ሕዝቡ እሱ ነው ሞግዚት

ኡማው የአምባ ገነንነቱንና ብልሽቱን ጭቆና በፖለቲካው ተግባር ላይ እንዲጋርድ፡ አስተዳደሮቹን በመምረጥና የአስተዳሩን ተቋማት የማስተዳደሩን መብት የሚሰጠውን ፓርቲ በመምረጥ መብቱን መጠቀም አለበት፡ ያም በመሪዎቹና በፕሮግራሞቹ አይነት መሰረት ነው የሚሆነው፡ ያ ሕዝቡን የሚያነሳሳ ነው የስልጣንን ቁልፎችና የማህበረሰቡን ጉዳዮች ማስተዳደርን ወደ ማስረከብ፡ ኡማው በተግባራቸው ና በፕሮ ግራሞቻቸው ጥበብ እስካመነ ድረስ ላይ እንዲቀጥሉ፡፡

እዚህጋ ሃይማኖት  በፖለቲካ ውስጥ ተጽዕኖ የመፍጠሩ ሚናና የፖለቲካውን አቅጣጫ በመመካከር መሰረት ማስያዙ ይመጣል።
እነዚያ የሚያስተዳድራቸውን ሰው የመምረጥ ቁልፎች፡ እሴቶቻቸውን የሚያከብር መርሆቻቸውን የሚይዝ ይመርጣሉ፡ ጥቅሞቻቸውን በብቃት የሚያገለግሉ ፕሮግራሞችን የሚያቀርበውን ሰዎቹ ከአቅምና ታማኝነት በተቻለ ታላቅ ልክ የሚገለገሉትን ይመርጣሉ።
ይህ በማህበረሰብ ውስጥ እውን አይሆንም ደዕዋ በማድረስና በማስተማር ሚናውን ካላደረሰ በስተቀር። የህዝቡ ምርጫ የፓርቲዎቹ ፕሮግራሞች በሚደገፉበት ላይ አያጥርም ከእሴቶችና አመለካከቶች መርሆች አላማዎች፡ ይልቁንስ የዚያኑ ያህል አስፈላጊነቱ ይለጠጣል፡ ለጥቅሞቹ የፓርቲዎቹና የመሪዎቹ ፕሮግራሞች ወደሚወክሉት፡ ያ የፖለቲካ መሪዎች ፕሮ ግራሞቻቸው በመገመቱና ተግባራዊ ማድረጉን በመቻል የሚተላለፉት፡ በዚህም ኡማው በስልጣን ላይ በአስተዳደሮችም ላይ ከሚከለከሉ እጅግ አስፈላጊ ምክንየቶች ና አስተዳደሮች ሃብቶችን እንዳይቆጣጠሩ የሚጋርድ ነው፡ የአምባገነንነትና የብልሽት መሰራጨት የሕዝቡ ሃብቶች ወደ መውደም ምጣኔ ሃብታቸው ወደ መንኮታኮት ያደርሳል፡ ዜጎቹ በስራ ፈትነትና ድህነት በረሃብ እንዲሰቃዩ ትምህርትም እንዲንኮታኮት፡ ማህበረሰቡ እንዲ ፈራርስ፡ በባርነት ስር እንዲውል፡ ጫንቃዎች እንዲዋረዱ፡ ዛሬ በብዙ አገሮች እንደምናየው።
በዚህም ሃይማኖትና እሴቶቹ ከፖለቲካና የፖለቲካ ፓርቲዎችን ፕሮግራሞች አቅጣጫ ከማስያዝ የማይቆረጥ አካል ይሆናል። እዚህጋ ማንኛውም ሙግት ቦታ የለውም ወደ ማንኛውም መነጠል ወይም በፖለቲካ ሜዳ የኢስላምን ሚና ለማራቅ የሚያልም የሆነ።

## የቡድኖች ፓርቲዎች ማለት ምን ማለት ነው ?

በፖለቲካዊ ፓርቲ አባሎችና በፖለቲካዊ ፓርቲ ህዝብ መሀከል እንዲሁም በጭፍሮች ፓርቲ ወይም በፖለቲካዊ ቡድን ፓርቲ በቡድኑ ስም የሚናገር መሀከል መለየት አለብን። በፖለቲካዊ ሕይወት ውስጥ ቀኝ ክንፍ ወግ አጥባቂ ፓርቲዎችን የሚወክል አለ፡ የዘመናዊ እኩልነት ፖለቲካዊ ፍልስፍና የኮሚኒስት ሥርዓት ፓርቲዎች አሉ፡ ቀኝ አክራሪ ፓርቲዎችም አሉ፡ የሕብረተሰባዊነት ፓርቲዎች

( በላብ አደሩ የበላይ ገዥነት የሚመሰረት ና የማምረቻ መሳሪያዎች በሕዝብ ቁጥጥር ስር የሚሆኑበት ስርዓተ ማህበር) ፡ ነጻ አስተሳሰብ ያላቸው ፓርቲዎች፡ ኢስላማዊ ፓርቲዎች አሉ፡ ሕዝቡ የየአንዳንዱን ፓርቲ ባህሪ እንዴት ሊያውቅ ይችላል፡ የዚህን ፓርቲ ወይም የዚያን ፕሮግራሞች እንዴት ሊገመግም ይችላል ? ሕዝቡ የፓርቲውን ባህሪና የአባልነቱን ባሕሪ መርሆቹን ከመግለጹ አኳያ ያውቃል፡ ያ የአስተሳሰቡን ምንጭ የሚገልጽ የሆነ፡ የፖለቲካ ድርጅቱን መርሆች ማወጅ እሱ ነው የፓርቲውን ምንነት የሚወስነው፡ የኡማውን ብዙሃን የፓርቲውን ፕሮግራም ባህሪ ለመገምገም ግቦቹንናአላማዎቹን እይታውን መሪዎቹ ፕሮግራሞቹን እውን ለማድረግ መቻላቸውን ታማኝነታቸውን ና ተንቀሳቃሽነታቸውን ለማወቅ ይረዳል።

የኢስላማዊን ፓርቲ ማንነት የሚለየው መርሆቹን ማወጁ ነው፡ እነዚያ የበላይ መሰረታዊ ኢስላማዊ መርሆችና ግቦች የሆኑትን፡ ፍትህ እኩልነት መረዳዳት መብቶችንና ነጻነቶችን መጠበቅ፡ የሐይማኖት ነጻነትንና የአብዛኞቹን ሕዝብ ምርጫዎች ማክበር።

የፓርቲው መርሆች አዋጅ ግልጽ ሆኖ መምጣት ይገባዋል፡ መነሻዎቹና ህገ መንግስታዊ ግቦቹም ግልጽ መሆን አለባቸው፡ የሚሰበስብም የሚለያይ መሆን፡ ከኢስላም መነሻዎችና አጠቃላይ ሕይወትን በማስተዳደር አጠቃላይ ስነምግባራዊ ቋሚዎቹ የሚገልጽ መሆን፡ ጥቅሱ የኢስላማዊ ፓርቲዎችን ማንነት ሲያውጅ ሰፋፊ ሀገሮች ላይ ያለማሳጠር፡“የኢስላማዊ ሸሪዓ ህጎችን መያዝ” የሚለውን ሀረግ ይመስል፡ ምክንየቱም ያንን ተከትሎ የሚመጣው ጥያቄ፡ ፓርቲው በኢስላማዊ ሸሪዓና በህጎቹ ምንን ሽቶ ነው ? እነኚህ ህጎችስ በዬትኛው የኡማው መዝሀቦች ና ቡድኖች ፉቀሃኦች ተመራማሪዎች መሰረት ነው የሚያዙት ? አጠቃላይ ሕይወትን በማስተዳደር ጉዳይ እንዲህ አይነት ሰፊ መግለጫ መጨረሻ የሌለው ውስብስብ ነገር ውስጥ መግባት ማለት ነው። እያንዳንዱ ጭፍራ እያንዳንዱ ፈቂህ እያንዳንዱ ቡድን እያንዳንዱ ስብስብ በትክክለኛ መንገድ ላይ ነን ማለታቸው ግልጽ ነው።

ፓርቲው የተወሰነ አንድን መዝሀብ ወይም ትምህርት ቤት ቢይዝ ብዙዎች ተቃራኒው ይሆናሉ ጠላትነትንም ያውጅበታል። የኢስላምን ኡማ ታሪክ ጥፋትም ያሸክሙታል፡ እሱንም የዚያን መዝሀብ ወይም ትምህርት አባልም፡ እነሱ ደግሞ ከፓቲው ፕሮግራም ና ከአስተዳደር ጉዳዮች ጋር ተያያዥነት የሌላቸው ጥፋቶች ናቸው፡ ስለዚህም እሱ በስተጀርባው ጥቅም የሌለው ሁከት ብቻ ነው።

ፓርቲው ከአስተሳሰባቸውና እይታቸው እቅስቃሴዎቹን በማስተዳደር ላይ የሚቆሙት የፓርቲው አባሎችና አመራሮቹማ -እነሱ ከፓርቲው አጥቃላይ ሕዝብ ውጭ ሲሆኑ- ከመካከላቸው ለህግ አስፈጻሚ ባለስልጣን ና ለህግ አውጪ ባለስልጣን ምክርቤቶች አባልነት ምርጫዎች በመታጨት ፓርቲውን የሚወክል ይመረጣል፡ እነዚያ የፓርቲውን መርሆችና ፕሮግራሞቹን መያዝ አለባቸው፡ ከሷ በምንም ሊያፈነግጡ አይፈቀድላቸውም፡ በፓርቲው አስተዳደር ምክርቤቶች ፍቃድ ካልሆነ በስተቀር የፓርቲው አመራሮች አዲስ ነገሮችን በሚሰጧቸው ግምቶች ክልሎች ውስጥ እንጂ፡ አለበለዚያ ያ ነገር ያንን ፓርቲውን የመረጠውንና ፓርቲውን የሚወክለውን አባሉን በፓርቲው ፕሮግራም መሰረት የመረጠውን ሕዝብ የመክዳት ዓይነት ይሆናል፡ እዚህጋ ፓርቲው በወደ ፊት የምርጫ ጉዞዎቹ ውድ ዋጋ ይከፍላል።
ጭፍራን ወይም ቡድንን ራሱን የሚወክል ፓርቲ ከተገኘ አባሎቹን እሱን በመምረጥ ካዘዘና በጭፍራው ወይም በስብስቡ ውስጥ ያሉትን የስልጣን ባለቤቶች ትእዛዝ እንዲ ይዙ ካዘዘ ለጭፍራው ወይም ለቡድኑ አባል ግላዊ እምነት ቦታ ሳይሰጥ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ፓርቲው ከራሱ ጋር እየተጋጨ ነው፡ የአባሎቹን ፍላጎት የማያከብር ስልጣናዊ ጭፍራዊ ስርዓት ይሆናል፡ ጥቅሞቻቸው መረዳታቸውንም አያምንም።
የዚህ ዓይነት ፓርቲ የኡማውን እምነት ማግኘት ና እነሱን መወከል ጉዳዮቻቸውን ማስተዳደር ተስፋ ማድረግ የለበትም። ይህም በዚህ ዓይነት ፓርቲ ና በፕሮግራሞቹ ወደ አለማመን ያደርሳል፡ ተቀናቃኞቹና ተወዳዳሪዎቹ ይህን አሉታዊ ክፍተት ከሱ ስጋቶችን በመቀስቀስ ይጠቀሙታል፡ ከከፊል ኢስላማዊ ቡድኖች ጋር፡ እንደ ተከሰተው፡ እነዚያ መጨረሻቸው ወደ መከልከልና ተቃራኒ ፕሮፓካንዳ የሚሆነው፡ በመቀጠልም የፓርቲውን ፖለቲካዊ ምኞቶች ና የቡድኑን የደዕዋ ተግባራት ይጎዳል።
በኛ ታሪክና በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በፋሺስታዊ ስርዓት ተከታዮችም ታሪክ በማርኪሲዝሞች ታሪክና ርእዮተ ዓለማዊ መለያ ምልክት ባለቤቶች የሆኑ ፓርቲዎች ውስጥ ስልጣንን የጨበጡ ጊዜ ለብቻ የሚጠቀልሉት በጦሮች ጫፎች እንጂ የማይለቋት መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ዓለ።
ምክንየቱም ምንጊዜም ራሶቻቸውን በሐቅ ላይ እንዳሉ ነውና የሚያምኑት፡ ከነሱ ውጭ ያለው በስህተት ላይ፡ ስልጣን በሚያመጣቸው ጥቅሞች ተጽዕኖ፡ ብልሽት ና አምባገነንነት ይሰፍናል፡ በተለይ ከመጀመሪያው ታጋይ ትውልድ በኋላ።

ማንኛውም በህዝቡና በአባሎቹ መሀከል እኩል የሚያደርግ ፓርቲ እነዚያን ወደሱ መቀላቀልን የሚፈልጉትን አባልነታቸውን ያለማየት፡ በሚወዳደሩባቸው ስልጣኖች ላይ ከነሱ ብቃት ያሏቸውን በእጩነት ለመምረጥ መብት የማይሰጣቸው፡ ያኔ በቡድንተኝነት ና በዘረኝነት በዝግነት ይፈረጃል።
ስለዚህ የኢስላማዊ እንቅስቃሴ ቡድኖች፡ በደእዋና ሰዎችን ማስተማር ስራዎች ላይ ራሳቸውን ቢያሳጥሩ የፖለቲካዊ ፓርቲያዊን ጉዳይ የፖለቲካን ስራ ለሚፈልጉት ና በፖለቲካዊ ሞያዊ ችሎታ ለተለዩት ቢተውት፡ ኢስላማዊ ፖለቲካዊ ፓርቲዎች እንደ አመለካከታቸው ብዛት ቢበዙ፡ እነሱ በኢስላማዊ አቅጣጫቸውና መርሆቹን በመያዝ፡ ቢስማሙም፡ ነገር ግን እነሱ በአስተያየትና የኡማውን ጥቅሞች በማገልገል አቅሞቻቸው ይተላለፋሉ። የደዕዋ ተቋማት ወደ አንድ ፓርቲ ወይም ወደ ሌላ ወይም ወደ አንድ ግለሰብ ወይም ወደሌላ መጠቅለል የለባቸውም።
የዚህ ትርጉሙ ከነዋሪዎች ማንኛውም ቡድን ፖለቲካዊ ፓርቲ መመስረት ይችላሉ ማለት ነው፡ የፓርቲው ገለጻ ማንነቱን መግለጽ አለበት፡ ይህደግሞ "ኢስላማዊው" ፓርቲ ሙስሊም ካልሆኑ ነዋሪዎች አባሎችን መቀላቀል አይከለክልም መርሆቹን እስካረጋገጡና እስካመኑ ድረስ። የዚህ የፓርቲው ህዝብ ከሙስሊምና ሙስሊም ካልሆኑ ነዋሪዎች ቅልቅል መሆኑ የግድ ነው፡ ማንነቱ ከኢስላማዊ እሴቶችና አላማዎች መርሆች እንኳን ቢገልጽም፡ እርሱ እንደዚሁ ከትክክለኛ ሰዋዊ ተፈጥሮም ይገለጻል፡ በነጻነት እሴቶች በክብር ፍትህንና እኩልነትን በማሰብ በጎ በመስራት በመረዳዳት በለውጥ። ፓርቲው ሁሉንም አባሎቹን በብቃታቸውና ኢስላማዊ ተፈጥሯዊ የፓርቲውን እሴቶች እንዲሁም መርሆቹንና አላማዎቹን በመያዛቸው ሊዋዋላቸው ይገባል።

## የቱርኩ ሙከራ ሊከተሉት የሚገባ ትምህርት ነው

የቱርክ ህዝብ ተሞክሮ ንብረቶችን በስጦታ መስጠት ተቋም ላይ በመጠባበቅ ሃይማኖትን የማስተማሩን ጉዳይ ለህዝቡና ለደዕዋ ሰዎች በመተው በልጧል። የቱርክ ኢስላማዊ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ተሞክሮ በእርግጥ በበርካታ እርከኖች አልፏል፡ ከፊል ኢስላማዊ ወጣቶች የመዲናውን ኢስላዋዊ ሀገር ስልት የተከተለ አንድ ፓርቲ በመመስረት ዘውድ ጫነ፡ ነጻነቶችን አከበረ፡ ፍትህንና እኩልነትን መረዳዳትን አሰበ፡ እንዲሁም ኡማውንና ጥቅሞቹን በብቃትና በሞያተኛነት ማገልገልንም ወደ አባልነቱ ከኢስላሚስቶችሌላ አባሎች ተቀላቀሉ፡ በብቃትና ያለመለየት የፓርቲውን መርሆች በመያዝ መሰረት ተዋዋላቸው፡ ያ ነገር

የኢስላሚስቶችን ፓርቲ ከኢስላማዊም ሆነ ኢስላማዊ ካልሆነ የቱርክ ሕዝብ ዓይነቶች ድምጻቸውን ለማግኘት አበቃው፡ ምክንየቱም እሱ ሃይማኖታዊ ደዕዋዊ ኢስላዋዊ ድርጊት ነጻነትን አገልግሏል፡አሟልቶላቸዋልም፡ ኢስላማቸውን አጥብቀው ከያዙት ሙስሊሞች ላይ የዲምሰሳንና የጭቆናን የበዳይ ወገንተኝነቶችን ስልት በደል አስወግዷል፡ ያ ጭቆና ከግላዊ መብት ጉዳዮችና ከግላዊ ሁኔታዎች ኢስላማዊ ተደርጎ የሚቆጠረውን እንኳን ያካትታል፡ ከነዚያ ውስጥ ሽፋኝ ትሁት የሆነ ልብስ የሴትን የራስ ጸጉር በመሸፈን፡ ሊበራል ፓርቲዎች ሴትን -በሂጃቧ ምክንየት- ከመሰረታዊ መብቷ ከትምህርት ና ከአጠቃላይ አገልግሎት ስራዎች ሒጃቧን ካወለቀች በኋላ እንጂ ከከለከሉ በኋላ። የኢስላማዊ የደዕዋ አብሳሪ እንቅስቃሴዎች ና ሌሎችም ማስተማርና ማሳደግ ወደ አላህ መጣራት በጥሩ ማብሰር አለባቸው፡ የፖለቲካን ስራ ብቃት ላላቸው ሰዎች መተው አለባቸው ከነዋሪዎች ና ከደዕዋው ልጆች ከተማሪዎቹ፡ የፖለቲካውን ስራ ከሚፈልጉት፡ ያ ስራ ወደ ሰው ተፈጥሮ ግቦችና ኢስላማዊ እሴቶች የሚደገፍ፡ የኡማውን ጥቅሞች በታማኝነትና በብቃት የሚያገለግል፡ ሰውኛ ኢስላማዊ ሀገርና ስርዓት ውስጥ ለሁሉም ነዋሪዎች የሚበቃ የሆነ፡ ለሙስሊሞችም ሙስሊም ላልሆኑትም፡ ያለመለየት ወይም ወገንተኝነት። እኛ የኑወርሶችን ና ሌሎችንም የደዕዋ እንቅስቃሴዎች ና ድርጅቶቻቸውን ሚና አስፈላጊነት ባላወቅንበት ጊዜ በስህተት ውስጥ ነን፡ እንደ “ጎለን” እንቅስቃሴ የቁርኣን ሂፍዝ ትምህርት ቤቶች በቱርክ ተሞክሮ ውስጥ፡ ያረጋገጠችውም ከዐረቡ ዓለም በማያንሱ ሁኔታዎች ውስጥ፡ የበለጠና የጠነከረ ባይሆን፡ ቱርኪያና ኦቶማን ሀገር ከአውሮፓ ጋር ባላት ጂኦግራፊያዊ ና ታሪካዊ ግንኙነት ምክንየት።

ኢስላማዊ እንቅስቃሴዎች በደዕዋ ስራ ላይ ቢያተኩሩና የፖለቲካውን ሜዳ ለወጣቶቹ ቢተውት በብሩህ አስተሳሰብ ና ከሌሎቹ ቡድኖች ጋር በጋለ ውድድር እንዲገቡበት፡ ደዕዋ የምትጓጓለትን በነሱ እውን እንዲታደርግ፡ እነዚያ መለያቸው ጥሩ አስተሳሰብና አመለካከቶች ስነምግባሮች ታማኝነት ስለሆነ፡ በቱርክ እንደምናየው፡ ያ የተሞከረው አካሄድ ነው።

### ደዕዋና ማደስ

ኢስላሚስቶች ወደ ስልጣንና አስተዳደር መድረስን -የአስተሳሰብን ና የደዕዋን ስልቶች ሳይሆን- በዚህ ሰዓት ኡማውን የተጋፈጠው ችግር መሰረታዊ ችግር

አድርገው ሲመለከቱት ተሳስተዋል፡ እናም እሱ በመረጋገጡ ደዕዋውን ያሰጉት ችግሮች ይፈታሉ ብሎ ማሰብ።
የዚህ ማስረጃው የኢስላማዊ እንቅስቃሴዎች አስተዳደር ዓመታት በከፊል ሀገሮች የተውት ተጽእኖ -የቱርክ ተሞክሮ ስኬቶች ሲቀሩ በከፊል ሀገሮች መንግስቶች ውስጥ የተሳተፉ ከፊል ኢስላማዊ ግለሰቦች ሲቀሩ- አወንታዊ አልነበረም፡ ይልቁንስ በጥቅሉ አሉታዊ ነበር፡ እነኚህ እንቅስቃሴዎች ብዙ ደጋፊዎቻቸውን ወደ መክሰር አድርሷል፡ ከኢስላማዊ መፍትሄ ደጋፊዎች በርካቶችንአደናግጧል። እዚህጋ ሰበቡ በአመራሮችና በማህበረሰቡ ውስጥ በእኩል ደረጃ የሚሸፈን መሆኑ ግልጽ ነው። ደዕዋ አድራጊ መሪዎች አስተሳሰብን አላቀረቡም የሰፊ ህጉን ባህሪ የሚቀይር አመለካከቶችም፡ በተለይ የተማሩትና ተንቀሳቃሽ ቡድኖች። የዚህ ጭፍሮች ከፊል -እንደ ምሳሌ- በምእራቡ ናሙና የመደምደም እስረኛ ከመሆን አልተወገደም፡ በአስተዳደር ስርዓት እሱን ወደ መላበስ ይቋምጣሉ፡ በሴቶች ጉዳዮችም፡ በኢኮኖሚ ስርአትም፡ በማስተማርም፡ የውስጥ መንፈሳዊ ፍጥረተ ዓለማዊ የሙስሊሙ ማህበረሰብ እይታ ግንባታ ከምእራባዊ ቁሳዊ ፍጥረተ ዓለማዊ እይታ ጋር የማይስማማ መሆኑን ሳይረዱት።
ከዚህ ነገር ተፈጥሯል -ተግባራዊ ሆኗልና- ድቅል ሁኔታ ውጫዊ የምእራቡን እይታ አለው፡ ውስጡማ የአስተሳሰብና ባህል መጠልሸት ይደበቅበታል፡ ያየኡማውን አስተሳሰብ በክፍለ ዘመናቶች ያጋጠመው፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ለብልሽትና ለአምባገነንነትያመቻቸው።
አስተሳሰብንና የደዕዋን ስልቶች መለወጥና የተሟላ ኢስላማዊ የህይወትን አመለካከት ማቅረብ፡ እሱ ይበልጥ አስፈላጊው ምክንየት ነው፡ ያ ለምእራቡ ስልጣኔ ተለዋጭ የሚቀርብ። ሰሪዎችና ደዕዋ አድራጊዎች ኢስላማዊ እንቅስቃሴዎችም የዚህን ሚና አስፈላጊነት ቢረዱ፡ በማህበረሰቦቻቸው ተጨባጭ የሚፈልጉት ነገር በፖለቲካ በኢኮኖሚ በስነ ትምህርት በማስተማር በሌሎችም። ድክመታችን በተዛባው አስተሳሰባችን ውስጥ ነው፡ በተጨባጫችን ውስጥ ተጽዕኖ አሳዳሪ የደዕዋ ትግሎች በማጠራቸው ነው፡ ነገር ግን በእምነታችን በፍጥረተ ዓለማዊ መንፈሳዊ ስነ ምግባራዊ እይችን ተጋድሮት እሱ ነው ቁሳዊ ምእራብ ከኛ የመፍራቱ ምክንየት፡ እሱ ነው ቀጣይ ትግሎችን የሚያብራራው በአደገኛ ጦሮቹ በኢስላሙ ዓለም ውስጥ በደዕዋና ምርምር እንቅስቃሴዎችተቃራኒ።
የደዕዋና የእንቅስቃሴዎቹን ተግባር ወደ አስተሳሰባዊ ተሃድሶና በሁሉም ስልቶች ማድረስ ማዞር አለብን፡ በተይ በስነ ትምህርትና በማስተማር መስክ የኢስላምን

እሴቶች ና ዓላማዎችን ማደላደልን በሚያገለግል በቤተሰብ በመጀመር በትምህርት ቤት በመስጊድ በጁምዓ በመገናኛ ብዙሃን በአስተሳሰባዊና ማህበራዊ ክለቦች ለህጻናትም ለአዋቂም ተግባርንና ግንኙመቶችን መብቶችንም ግዴታዎችንም እይታንም አለባበስንም ከኢስላም እይታ አኳያ በሚያገለግሉመስኮች።
አናሳ ጽዮናዊዎች በምዕራቡ ህዝቦች ላይና በምጣኔ ሃብቶቻቸው ላይ ለመቆጣተር ችለዋል አስተሳሰብንና ግንዛቤን በመቆጣጠር መንገድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን በመቆጣተር፡ የመገናኛ ብዙሃንና ባንኮችን፡ የገንዘብ ተቋማትን፡ ይህ ነገር ለማጭበርበርና ለማሳሳት አስቻላቸው፡ ፖለቲከኞችን መግዛትና ህዝቦችን ለበዝበዝማደላደልንም፡ በሃገሮቻቸው በአስተዳደር ተቋማት ላይ ጫና ማድረግ፡ እነዚህን ህዝቦች የማያገለግሉ ጥቅሞቻቸውን አገልግሎት ወሰ ማይሰጡ ፖለቲካዎችና ጠርነቶች ለመሳብ አስችሏል፡ እሱ ደግሞ የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ጂሚ ካርተር የገለጸው ነው፡ የሃገሩ ፖለቲካዎች ለሃገሩ ግልጋሎት አይደሉም ነገር ግን እነሱ ለእስራኤል ግልጋሎት ናቸው ሲል፡ እሱ ደግሞ ይህን ንግግር መግለጽ የሚችለው አሁን ብቻ ነው፡ ምክንየቱም አሁን ፖለቲከኛ ስላልሆነ፡ እነሱም ተነሱበት ቅጥረኞቻቸውንም ቀሰቀሱበት። የቀድሞው የማሊዢያ ጠቅላይ ሚኒስተር ሙሐመድ ሙሃዲር እንደሱ አድርጓል፡ ሌሎቹም ከነዚያ ከጀገኑትና የነዚያን የተቆጣጠሩ አናሳ ጽዮናዊዎችነውሮችንየገለጹ።
በዓረቡ ዓለም በዓረቡ ማህበረሰቦች ውስጥ የተደረጉት የአስተያየት አሰሳዎች በእርግጥ ገልጸዋል ሁላቸውም በኢስላም እሴቶች ያምናሉ፡ የብዙዎቻቸው ተግባር ደግሞ ተቃራኒ ነው፡ ለዚህ ደግሞ መሃይምነት እንጂ ሌላ ፍቺ የለውም፡ የኢስላማዊ ግንዛቤ መስጠት እጥረትና የአስተሳሰብ የተሃድሶ በጊዜው ተጨባጭና ተግዳሮቶቹ አቅሞቹ እጥረት ስላለ፡ በስነትምህርታዊ አስተሳሰብ፡ ከተስፋ አስቆራጭ ስልጣናዊ የጥሪ ንግግር የማምለጥ እጥረት ስላለ።
የደዕዋ ተቋማት ከነጻነት በምታረጋግጠውና ከአስተሳሰባዊ የደዕዋ ትግል ከምትሰጠው መጠን ኡማው በፖለቲካዊውና ኢኮኖሚያዊው ስራ ስኬታማ ይሆናል፡ በቁሳዊና ስልጣኔያዊ እድገትም፡ ይህ የአላህ ድንጋጌ ነው

( 62 : وَلَن تَجِدَ لِسُنَّةِ ٱللَّهِ تَبۡدِيلٗا ﴿٦٢﴾ (الأحزاب

“ለአላህ ድንጋጌ ፈጽሞ መለወጥን አታገኝም” (አል-አህዛብ፡ 62)

إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُغَيِّرُ مَا بِقَوۡمٍ حَتَّىٰ يُغَيِّرُواْ مَا بِأَنفُسِهِمۡ ﴿١١﴾ ( الرعد: ١١ ).

እንዲሁም "አላህ በህዝቦች ዘንድ ያለውን ጸጋ በነፍሶቻቸው ያለውን (ኹኔታ) እስከሚለውጡ ድረስ አይለወጥም" (አል-ረዕድ፡ ١١) ፡፡ ለውጥንና ስኬትን የሚሻ ሰው በአላህ ፍቃድ ደዕዋ ያድርግ ከዚያም ደእዋ ያድርግ ከዚያም ደዕዋ ያድርግ፡፡

## በሰውኛ ኢስላማዊ አስተዳደር ና በዓለማዊ ሊበራሊስት መሀከል ያለው ልዩነት

የወሰን የለሽ ዓለማዊነት ትርጉም፡ በአስተዳደር በፖለቲካና በሃይማኖት መሃከል በመለየት ብቻ ትርጉም፡ ኢስላሚስቶች የማይቀበሉት ደንብና ትርጉም ያደርገዋል፡ ምክንየቱም እሱ በስነልቦናዊ መነሻዎች የተሞላ አመለካከት ነው ማራቅንና ኢስላምን ማገድ ወደ ስነምግባራዊ መላቀቅ መጣራትን የሚሻነው፡፡

የምዕራቡ ማህበራዊ እምነት በፖለቲካና በሃይማኖት መሃከል መለየት የሚሻ ዓለማዊነት ብቻ አይደለም፡ ነገር ግን በተለይ በአውሮፓ ማህበራዊ ሊበራሊስት ማለት ነው፡ የኢኮኖሚ አቅጣጫው ምንም ቢሆን፡ የካፒታሊስት ስርዓትም ሆነ የሶሻሊስት ወይም የኮሚኒስት፡፡

በአውሮፓ የሊበራሊስት አነሳስ መንስኤው የአውሮፓዊ ህዝቦች አጸፋዊ ምላሽ ነው፡ በቤተክሪስቲያ አምባ ገነንነትና ብልሽነት ላይ በስልጣን ላይ በነበረችበት ጊዜ በአስተዳደር አምባገነናዊ ሆነች አበላሽችም፡ የአውሮፓ ሕዝቦች አብዮት ቀሰቀሱ የቤተክርስቲያንን ስልጣንና የአምባገነን ካህናቶቿንም አስገዳጅነት አስወገዱ፡ በዚህም ለቤተክርስቲያ የምታቀርበው አልቀረም፡ ምክንየቱም እሷ ዘንድ ክርስትና የቀረው ፍሬ ነገሩ ስርዓተ ጸሎትና መንፈሳዊነቶች ብቻ እንጂ አይደሉም እናም ከፊል አፈታሪኮች፡፡

ይህ ጉዳይ በማህበራዊ ግንኙነቶች መስክ ላይ ክፍተቶችን አስገኝቷል፡፡ ግለሰቡን ወደ ጭቃው ክፍልና ወደ እንስሳዊ አምርቶቹ እንዲመለስ አድርጎታል ለሚሰራው ሁሉ መነሻ እንዲሆኑት፡፡ ቤተክሪስቲያንማ የማህበረሰቡን ህይወት አቅጣጫ በማስያዝ ትልቅ ተጽዕኖ የሌላቸውን ቅርጻዊ ተግባሮቶቿንና አፈታሪኮቻቸውን የመተግበር ነጻነት ትቶላታል፡ -በብዛት- የምእዕራቡ ህዝቦች በመንፈሳዊ ስነምግባራዊ ሁኔታ በክፍተት ላይ ሆኑ፡ በህይወታቸው ውስጥ ዓላማ ወይም ትርጉም አልቀረላቸውም ጥፍጥናና እርካታ መፈለግ ካልሆነ በስተቀር ግለሰብ "ሰው" እሱ ነው መመለሻ፡ የዚህ ትርጉሙ በዚህ ሰው ዘንድና በማህበረሰቡ ዘንድ

ትክክለኛን ነገርና ስህተተኛን ነገር ለመወሰን ብቸኛው መመለሻው እሱ ግላዊ/ገለልተኛ ያልሆነ መመለሻ ነው፡ በተፈጥሯዊና በአፈነገጠ መካከል ለመለየት እድል የለም ወይም በስነምግባራዊና በእንስሳዊ መሃከል፡ በዚህም ቁሳዊዎች የሰው ልጅ አዕምሮ የፈጣሪን መኖር አለመኖር ማወቅ አይችልም ብለው ከሚያምኑት ህዝቦች ይሆናል።

ይህ ደግሞ እነሱ እምነት የለሾች ናቸው ማለት አይደለም፡ ይልቁንስ ቋሚዎቻቸውን የሚይዙ በእሴቶቻቸውና ተፈጥሯዊ ስነምግባራዊ መርሆቻቸው የሚያምኑባቸው፡ አምላካዊ ሃይማኖታዊ አዕምሯዊ ተጥሯዊ የመምራት መመለሻ የላቸውም ማለት ነው፡ ስለዚህም እነሱ በ "አላቅሞች" ማለክለክ ስህተት ውስጥ ናቸው። ተግባራቶች እንስሳዊ አነሳሾችና ፍላጎቶች ማፈንገጦች ያንቀሳቅሷቸዋል፡ እውነታና ትክክለኛ ነገር በአስተሳሰባቸው ውስጥ የተበላሸ የጎደሉ ነጥቦች ናቸው አስገዳጅ ተፈጥሯዊ መመለሻ አይደሉም፡

إِنْ هُمْ إِلَّا كَالْأَنْعَامِ ۖ بَلْ هُمْ أَضَلُّ سَبِيلًا ﴿٤٤﴾ ( الفرقان : 44 ).

"እነርሱ እንደ እንስሳዎች እንጂ ሌላ አይደሉም ከቶውንም እነርሱ ይልቅ መንገድ የተሳሳቱ ናቸው" （አል-ፉርቃን : 44） ።

የ"አላውቅም" ሁኔታ የአውሮፓ ህዝቦች በህብረታቸው ህገመንግስትና ሰነዶቹ የነሱ ስልጣኔ የክርስትና ስልጣኔ ነው ተብሎ እንዲገለጽ ፍቃደኛ ላለመሆናቸው ምክንየቱ። የአውሮፓ ሁኔታ ዓለማዊነት ብቻ አይደለም ነገር ግን እሱ "ቁሳዊ ዓለማዊነት ነው" የማህበራዊ ሊበራሊጎኑ ዛሬ በመጀመሪያ ደረጃ ለመንፈሳዊና ስነምግባራዊ መናዱ እሱ ነው ተጠያቂ፡ በምዕራቡ ዓለም ከቤተሰብ መናድና እየጨመረ ለሚሄደው ማህበራዊ ጭካኔ መሰራጨት።

ኢስላማዊ መንፈሳዊ ምትካዊ ዜጋዊነት ቁሳዊ ምዕራባዊ ዓለማዊነት ማለት ነው？ እነኚህን አመለካከቶች ማዳን አለብን ኢስላማዊ ኡማ ዘንድ ለምትቀሰቅሰው መዋለል፡ በተለያዩ ወገኖች መካከል በማሰብም ባለማሰብ በአመለካከቶች ለሚሰቡት ተግባራቶችና ግጭቶች ሲባል ይህ ነገር ደግሞ ገንቢ የሆነን ግንኙነትና ውይይትንያውካል።

ቀላሉ አረዳድ "የምዕራቡ ዓለማዊነት" የአስተዳደር ስርዓትና ስልጣኖቹ ከ"ሃይማኖት" ያእ"ክርስትና " የሆነ ከተለያዩ ቤተክርቲያኖቿ ጋር መሃከል የተለየበት የፖለቲካ ስርዓት ነው ብሎ ያምናል። በዚህም በሙስሊሞች ብዙሃኖች ዘንድ በሙስሊም ማህበረሰብ ውስጥ "ዓለማዊነት" የግድ ምዕራባዊ ያደርገዋል

ኢስላማዊ ምንነቱንም ይቀይረዋል የሚል እምነት ሰፍኗል። ከዚህም በመነሳት በተለያዩ ጭፍሮች መሃከል ፍልሚያ ይሽከረከራል በማህበረሰቡ ማንነትና የ“እምነቶቹ” ና “ስልጣኔው” “ውርሱ” የስልጣኔያዊ “ውርሱ” መጨረሻ ላይ የነኘህን ደንቦች ወደ አለማጥራት ይመልሳሉ።

ከምንም በፊት ማጥራቱ የሚገባው እሱ “ሃይማኖት”ማለት ምን ማለት ነው? እሱ ካለፉት “ሰማያዊ”ሃይማኖቶች በተለይም “አይሁዳዊነት” ና “ክርትና” ነውወይስ “ሃይማኖት” ማለት የሃይማኖት አመለካከት “ፍሬ ነገር” ና በሰው ልጅ ህይወት ያለው ሚና ማለት ነው፡ “ስነፍጥረታዊ እይታ ማለት ነው ያ ለግለሰቦችና ለሰው ልጅ ቡድኖች የህይወትን ትርጉምና ግቧን በሷ ውስጥ የመንቀሳቀስንዓላማ? ከዚህም በመነሳት የዘመናዊው ”የምዕራቡ ሃይማኖት“ እሱ ክርስትና አይደለም፡ ይልቁንስ ጭቃዊ እንስሳዊ ” ቁሳዊነት ነው“፡ ህጉ ደ።ግሞ “የጭቃው መበዳደል ነው” እሱ ”ሃይማኖት“ ና ፍጥረተ ዓለማዊ እይታ ነው የኢስላማዊ ምትካዊ ሰውኛ መንፈሳዊ ”ስነፍጥረታዊ እይታ“ ተቃራኒ ያ ህጉ ፍጹም ”ፍትህ“ የሆነ

لَّا يَنْهَىٰكُمُ ٱللَّهُ عَنِ ٱلَّذِينَ لَمْ يُقَٰتِلُوكُمْ فِى ٱلدِّينِ وَلَمْ يُخْرِجُوكُم مِّن دِيَٰرِكُمْ أَن تَبَرُّوهُمْ وَتُقْسِطُوٓا۟ إِلَيْهِمْ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلْمُقْسِطِينَ ﴿٨﴾ (الممتحنة : 8 ).

”ከነዚያ በሃይማኖት ካልተጋደሏችሁ ከአገሮቻቹሁም ካላወጡዋችሁ (ከሃዲዎች ) መልካም ብትውሉላቸውና ወደነርሱ ብታስተካክሉ ኣላህ አይከለክላችሁም ኣላህ ትክክለኞችን ይወዳልና “ (አል-ሙምተሂና፡8) ።

وَلَا يَجْرِمَنَّكُمْ شَنَـَٔانُ قَوْمٍ عَلَىٰٓ أَلَّا تَعْدِلُوا۟ ۚ ٱعْدِلُوا۟ هُوَ أَقْرَبُ لِلتَّقْوَىٰ ۖ ﴿٨﴾ ( المائدة: 8 )

“ህዝቦችንም መጥላት ባለማስተካከል ላይ አይገፋፉችሁ አስተካክሉ እርሱ ( ማስተካከል) ለአላህ ፍራቻ በጣም የቀረበ ነው” (አል-ማኢዳህ፡8) ማህበራዊ ጎኑ “ሊበራሊስት”ማለት መዝናኛዎችንና “ስሜቶችን” ትክክለኛ ሰዋዊ ተፈጥሯችን“ ያለመጠበቅ መከተልና ማለክለክ ማለት ሆኗል፡ እርሱ ደግሞ ትክክኛ የሆነውን ነገር ከመስራት የነጻነት መብት ከትክክለኛ ተፈጥሮ ጋር የሚጋጭን ነገር ወደ መስራት የመብት ሙግት መሸጋገሩ አይቀሬ ጉዳይ ነው፡ ይህ ደግሞ መብት አይደለም ይልቁንስ የማህበራዊ “ስርዓት አልበኛነት ነው” እሱ ደግሞ በታሪክ ውስጥ የማህበረሰቦችንና የስልጣኔዎችን መናድ የሚያሳውቅ ሁኔታ ነው፡ ያንን

የተከበረው ቁርአን በኖሕ ወገኖች በሹዓይብ ወገኖች በሉጥ ወገኖች በሌሎችም ሁኔታዎች እንደገለጸው።
በኢኮኖሚ መስኩማ የ "ቁሳዊው ምዕራብ ሃይማኖት" የሚያንጸባርቀው እሱ በህዝቦች መሃከል መፋለምን ነው፡ ሃይለኛው (ቅኝ ገዢ) ደካማውን ያድናል፡ እጅን ማስቀመጥ "የባለቤትነት ሰነድ ነው"፡ እሱ የ"ካፒታሊስት"አመለካከት ነው። የምዕራቡ ሕዝቦችና በነሱ ምህዋር የተሽከረከረ "ሃይማኖት" ወይም "ሃይማኖቶች ካሏቸው፡ ልክ ለኢስላማዊ ሕዝቦች "ሃይማኖት" እንዳላቸው፡ ምዕራቡ "ቱርክ" ወደ "አውሮፓ ህብረት" መቀላቀሏን የማይቀበሉበትን ምክንየት እንረዳለን እሷ ሁሉንም የ"ዲሞክራሲን" መሳሪያዎች ከማሟላቷ ጋር፡ አስደናቂ የኢኮኖሚ ተግባር እውን ከማድረጓ ጋር፡ በአስተዳደር በስልጣን በፖለቲካዊ ፕሮግራሞችና በሀይማኖት የደዕዋ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ መሀከል መለየትን በተግባር አረጋግጣ እያለች ከመንፈሳዊ ስነምግባራዊ እምነት የሚወክለውን ለደዕዋና ለሀገር ውስጥ ተቋማትና ድርጅቶች የተወ አድርጋዋለች። ማለትም በህዝቡ አመለካከት "አለማዊ" "ዲሞክራሲያዊ" ሀገር ሆናለች፡ እንደዚሁም ምዕራቡ እሱን ለማገልገል ከሚያስ መጣቸው አናሳ ሙስሊሞች ለምን እንደሚመጣበትም እንረዳለን ከዚሁም ጋር በ"ሃይማኖቱ" በ"ባህሉ" መብት ከሆነው ነገር እንኳን ይከለክላቸዋል። በ"ልብስ ጉዳዮች" እሱ ግላዊ ጉዳይ ሆኖ ሳለ ከፊል ሀገሮቹ የኒቃብን መብት ይነፍጋሉ እሱ " እሱ ራስን ብቻ መሸፈን ሆኖ ሳለ" ከፊሎቹ የአዛን ሚናራዎችን ይከለክላሉ፡ የአብያተ ክርስቲያናት የቃጭሎች ምሰሶዎች በሺዎች የሚቆጠሩ ተገትረው ሳሉ፡ እንዳውም ከፊላቸው ቁርኣን ማንበብ እርም ማድረግ ይሻል፡ ማስረጃቸው ያነገር ከ"ባህላቸው" ጋር አይስማማም ያበላሸዋል ነው።
እነሱ በስልጣንና በሃይማኖታዊ ሰበካ መሃከል መለየት ወይም በነሱ ተሞክሮ "ዓለማዊ" በሚሉት እሙስሊሙ አጠገብ ማህበራዊ ሊበራላዊ እሴቶች ማለት አለመሆኑን ይልቁንስ እነሱ መንፈሳዊ ስነምግባራዊ ኢስላማዊ መሆናቸውን ያውቃሉ፡ ከምታስገኘው ማተራመስና ካልተፈለገ ተጽዕኖ ይፈራሉ፡ ከልቅነትና እንስሳዊ ማምለጥ ካህናቶችና በስነምግባራዊ ቆሻሻዎች ንግድ ጥቅሞቻቸው በኩል ማህበረሰቦቻቸውም የዚህ ነገር ሱሰኞች ስለሆኑ።
ይህን ካወቅን፡ በሙስሊም ማህበረሰብ ውስጥ የአስተዳደርን ስርዓት ዜጋዊ ብለን መግለጹ ለምን የበለጠ ተስማሚ እንደሆነ እናውቃለን "ዓለማዊ" ሳይሆን፡ ምክንየቱም የአስተዳደር ሥርዓት በነጻ የማህበረሰቡ ፍላጎት መሰረት መቆሙ ይገባል፡ ነጻነቶችንም ዋስትና መውሰድ አለበት

لَآ إِكۡرَاهَ فِي ٱلدِّينِۖ (٢٥٦) ( البقرة: 256 )

"በሃይማኖት ማስገደድ የለም" (አል-በቀረህ፡ 256)

"የሰበካን" ነጻነት ይይዛል ወደ "ፍትህና መተዛዘን መረዳዳት ተጠያቂነቶችን መሸከም" መርሆች፡ የአስተዳደር ባለስልጣኖች ምንም አይነት ገደቦችን ሳያስቀምጡ፡ ያም እሱ የአስተዳደር ተቋማት ያለ "ብልሽነትና አምባገነንነት" የመተግበርን ደህንነት ዋስስትና መጠበቅ ነው።

ኢስላማዊ መንፈሳዊ ሃይማኖት ምትካዊ ስነምግባራዊ፡ እሱ ለሰው ልጆች የመድህን መርከብ ነው፡ ጥራቱን በመመለስና የመቀጠሉን ዋስትና ተቋማቶቹን በመገንባት መስፈርት ከጊዜውና ከቦታው ተጨባጭ ጋር እንዲሁም ከጊዜያቶች ተግዳሮቶች ጋር በመሄድ ወይም "ጥንታዊነትና ዘመናዊነት" ብለን የምንጠራው።

"የኢስላማዊ አስተዳደር ስርዓት" ትርጉም እሱ ነው ኢስላማዊ የአስተዳደር ስርዓት ሊጠራበት የሚገባው። በዓለማዊ እንኳን ቢጠራ፡ እሱ በመንፈሳዊ ስነምግባራዊ "ዓለማዊነት" ይተረጎማል፡ በዚያ የታሰበው የባለስልጣኖቹን እጅ  ከሃይማኖታዊ ትምህርትና ከደዕዋ እንቅስቃሴ ማራቅ ስለሆነ።

እዚህ ጋር ኢስላም የሙስሊሙን ሰው ስነልቦና የሚቀላቀል መንፈሳዊ ርቀቱና ስነምግባራዊ እሴቶቹ ያሉት መሆኑ አይርቅም፡ በነሱም በሕይወት ውስጥ መያዝን ያውቃል። ስለዚህም ከኢስላማዊው ሁኔታ ጥሩ አገላለጽ፡ እሱ"ኢስላማዊ የአስተዳደር ሥርዓት" ነው ብሎ መግለጽ ነው።

መንፈሳዊ ስነምግባራዊ ኢስላማዊ ፍሬነገር ያ ሙስሊም ሰው የሚያምንበት፡ ብዙ ጥፋቶች ተቀላቅለውበታል፡ የሙስሊሙን አስተሳሰብና መንገዶቹን የስነትምህርታዊ መሳሪያዎቹን እስካዳረሰ ድረስ፡ በእምነትና በተግባር መካከል መቆራረጥን እስካስገኘ ድረስ። ነገር ግን የሙስሊሙ ስነልቦናዊ መንፈሳዊ መያዙ በሕይወቱ ተጨባጭ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ቀጣይ በሆነ እንቅስቃሴ ውስጥ ያደርገዋል። ይህ ስነልቦናዊ ተፈጥሯዊ አእምሯዊ መንፈሳዊ አነሳሽ ደግሞ እሱ ለኡማውና ለሰው ልጅ የመድህን ሃይል ነው፡ በአዲስ መልኩ ወደ ሰላም የብስ መመራቷን ያገራል።

እንደዚሁትክክለኛው ስያሜ ያለኢስላማዊው ማህበረሰብና ለአስተዳደር ስርዓቱ የሚገባው እሱ"ኢስላማዊ የአስተዳደር ስርዓት ነው" በደዕዋና የሃይማኖት ትምህርት መሀከልና በስልጣን በአስተዳደር መሀከል መለየት ማለት ነው፡ የዚህ የመለየት ዓላማ የስልጣን ሰዎች እንዳይደላደሉ ነው የሃይማኖትን መርሆች

ከማበላሸትና ህዝቡን ለመቆጣጠር እንዳይጠቀሙት፡ ስልጣንንና ሃብትን የብቻቸው ለማድረግ እንዳይጠቀሙት አምባገነንነት ና ብልሽት እንዳይስፋፋ። ኡማው-በኔ አስተሳሰብ- በመንትያ መንገዶች ላይ ናቸው በሰበካዊና ፖለቲካዊ መሀከል መለየት ያስፈልጋል፡ ኢስላማዊ አስተሳሰብን ከመበላሸት ከመበላሸት ያጋጠመውን ማስወገድ፡ ኢስላማዊ ትምህርቶች አመለካከቶች ያጋጠመውን ከመሳንደዕዋ አድራጊዎች የሰው ልጅ ፍጥረት እውቀቶችን ባለማወቃቸው ሰበብ፡ ከሰው ልጅ አፈጣጠር ጋር ተያያዥ የሆኑትን ሳይንሳዊ እውነታዎች ማለት ነው፡ በሕብረተሰብና ሰብአዊነት ትምህርቶች መታገዝ-ለምዕራቡ ሥነፍጥረታዊ ቁሳዊ እይታ ተግባራዊ ከማድረግ ዓላማ የጠራች ስትሆን-የኢስላምን እምነትና እሴቶቹን ሥነምግባሮቹን በህጻኑ እድገት መሰረት እንዴት እንደምት ተክል በማወቅ፡ ያንን አማኝ ባሪያዎቹን የሚወደውን አላህ ለመውደድ፡ ከስልጣናዊነትና ከማስፈራራት ፍላጎትን ከመጫን የራቁ በመሆን

﴿ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ أَشَدُّ حُبًّا لِّلَّهِ ﴾ ( البقرة : 165 )

“እነዚያ ያመኑትም አላህን በመውደድ (ከነርሱ) ይበልጥ የበረቱ ናቸው” ( አል-በቀረህ፡165) ። ለኢስላሚስቶችና ኢስላማዊ ፓርቲዎች እጅግ አስፈላጊነው ለሕዝቡ መብት መያዝና ለሱ መታገል፡ የሚያስተዳድረውን አካል በመምረጥ ነጻነት፡ በፓርቲዎች መብዛትና በስልጣን ሽግግር መብት መሰረት በኡማው ብዙሃን እምነት መሰረት፡በማንኛውም ከነኚህ መርሆች ተቃራኒ የሚሰራ ፖለቲካዊ ፓርቲ ፊትለፊት መቆም፡ እሱን መግለጹና ማጋለጡ፡ ማንኛውንም ህጋዊ ስልቶችን በሱ በሱ ተቃራኒ መጠቀም፡ የህዝቡን ሀሳብ ብሩህ ማድረግ መርሆቹንና ስልጣናዊ መርሆቹን አደጋዎች በመግለጽ፡ ከጠንካራ ተግባር ጋር፡ ከሁሉም ተቋማትና ከሰሪ bud ኖች ጋር በመረዳዳት፡ የተውሒድን እምነት ለማደላደልና ለመተካት፡ የሰውን ልጅ ክብርና የመረዳዳቱን ዋስትና ለመስጠት፡ እውነትና በጎን ለማስፈን፡ እሴቶችንና ጥሩ ስነምግባሮችን በማህበረሰቡ ውስጥ ለማሰራጨት፡ ለኡማውና ለሰው ልጅ አገልግሎት ሲባል።

**ማጠቃለያ**

በኢስላማዊ ኡማ ሕይወትና በፖለቲካዊ ታሪኩ ውስጥ ውስብስብና የበረታ ዝብርቅርቅ ጉዳዮች አሉ፡ ግንኙነት በፖለቲከኞችና በፉቀሃኦች ሊቃውንቶች ና ሃገር መሃከልተሳከሯል፡ በብዛት ብልሽትና አምባገነንነት ባለስልጣን በቁስ በመኖርና ከዚህ ጋር በሚጎዳኝ የስነምግባር መጥፉት ውጤት ይከሰታል፡ ጥቅሱን በመተቸት ና በመቀየር፡ ገዢው በአምላክ ፍላጎት እንደተመረጠ ሰውና የአምላክን ጥቅስ መራጭ ተናጋሪ ተደርጎ እስከተቀደሰ ድረስ።

ስለዚህም በአስተዳዳሪ ባለስልጣንና በደዕዋ መሳሪያዎች ማህበረሰቡን አቅጣጫ ከማስያዝ መሃከል ወደሱ የምንጠራው መለየት እሱ ለቅደም ተከተሎች መሰረት መጣል ነው፡ እነዚያ ከአጠቃላይ ጉዳዮች ጋር የሚያያዙ የምትክነትን ትርጉም የሚያረጋግጡ መካሪ አዋቂዎችንና የለውጥ ሰዎችን የደዕዋ ሰዎችን የሞያና የልምድ ባለቤቶችን ያለምንም ማራቅና ማግለል እንዳውም ከዚህ መለየት የተሻው ሚናቸውን ማንቀሳቀስ ነው፡ ከአስተዳደሩ ቁጥጥር በመራቅ ያ አብዛኛውን ጊዜ ሃይማኖትንና ተወካዮቹን ለሱ ግልጋሎትና ለተከታዮቹ ለረዳቶቹ ግልጋሎት በመበዝበዝ ላይ የሚሰራ።

ብልሽትና አምባገነንነት አልተስፋፉም ቅርሳዊ ፖለቲካዊ ቋንቋዎች“ነዋሪዎችን” ወደ “ተራ ሕዝብ” ና “ ምሁራን” ብለው የከፈሉ ጊዜ እንጂ እንዲሁም ገዢው የማሕበረሰቡን አቅጣጫ ማስያዣ መንገዶችን ከተሾመባቸው ና ኡማውን እሺ ለማስባል ብልሽቱንና አምባገነንነቱን ጥሩ ለማስመሰል በተጠቀመ ጊዜ እንጂ፡ አስተዳዳሪው ሀገር ተቋም የለውም፡ በመቀጠልም መብቶች ተደፈሩ፡ እሱ ደግ በኸልፉኒ አመለካከት ግንባታ ይፈልጋል፡ ሃይማኖታዊ ለውጥም በአእምሯዊነትና ተግባራዊነት ላይ የሚመሰረት፡ በሃይማኖትና በስልጣን መሀከል ያለውን ግንኙነት በድጋሜ የሚያስተካክል፡ ለኢስላማዊ ማህበራዊ አስተዳደር ሀገር መሰረት የሚጥል፡ በሷ ውስጥ በአስተዳደርና በነዋሪዎች መሀከል ያለው ግንኙነት አቻ የሚሆንበት።

ነዋሪዎቹ በአስተዳደርና ባለስልጣን ፍላጎት ውስጥ የሚቀልጡ አካሎች ተደርገው አይታዩም ይልቁንስ የስልጣን መሰረትና ምሰሶ ግቦቹ ተደርገው ነው የሚታዩት፡ ኡማው ደግሞ ዜጎች ተደርገው ይታያሉ እንጂ ነዋሪዎች ተደርገው አይታዩም።

አላህን ትክክለኛነትንና መመራትን እንለምነዋለን እርሱ ሰሚ ጸሎትን ተቀባይ ነውና።

# ይህ መጽሐፍ

በእምነትና ፖለቲካዊ አስተሳሰቦች ላይ ያሉ አምባገነናዊነት ብልሹነት ላይ ዐዲስ መንገድን ያቀርባል፡፡ ስለ ሥልጣኔ የተቀመጡ ሕግጋትን ከተጨባጩ አንጻር በመዳሰስ

በእምነትና በሥልጣን ላይ ላሉ ክፍተቶችን በመጠቀም መስተካከልን ይጣራል፡፡ ለተጨባጭ የቀረቡ ምሳሌዎችን፣ ለተግባር የተመቹ ሐሳቦችን በማካተት ያቀርባል፡፡ ኢስላማዊ ሀገረመንግሥት አወቃቀርና ሶቅራጠሳዊ የሀገር አወቃቀርን እያነጻጸረ ይቀርብበታል፡፡ በሥልጣን ላይ የሚሰሩ ስሁት ምልከታዎችን ተግባራት ያጋልጣል፡፡

በባለሥልጣትና በዳዕዋ ተቋማት መካከል መኖር ስላለበትም ግንኙነት መረጃ ያቀርባል፡፡ ኢስላማዊ ቡድኖችና ፓርቲዎች እንዴት ፖለቲካን እንዴት ማከናወን እንዳለባቸው አቀጣጫ ይሰጣል፡፡ ይህ መንገድ ከሱልጣናዊ የመንግሥት ቅርጽ ወደ ራስ ገዝ አስተዳደራዊ ቅርጽ ያለ ሽግግር ነው፡፡ ይህ ሥርዓት ሁሉም ሰው የራሱን ጉዳይ የሚፈጽበት መንገድ ነው፡፡ ባለው ልፋትና አረዳድ ልክ የሚኖርበት ያበትን ዘመንና ቦታ ሁነት ሳይወድ በግዱ የሚሳበስበት ይህ ራስ ገዝ አስተዳደር እንዴት ብሎ ነው ስለ መወዳደና መተሳሰብ የሚጠራው? የተለያዩ ምሳሌዎችን እያነሳሳ በመጽሐፉ ይዳሰሳል::

ዐብዱልሐሚድ አሕመድ አቡ ሱለይማን (አላህ ይዘንላቸው)
በመካ ከተማ ተወለዱ፡፡ እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር ከ1988- 1999 ድረስ በማሌዢያ የዓለም ኢስላማዊ አስተሳሰብ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ሆነው አገለገሉ፡፡

በአሜሪካ ሀገር በ1973 በፔንሶቬንያ ዩንቨርስቲ በሀገራት ግንኙነት ላይ የዶክትሬት ዲግሪያውቸውን አገኙ፡፡ በበርካታ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ጥናቶችንና መጽሐፍትን አበርክተዋል፡፡ ከእነርሱም ውስጥ ‹‹ ነዘሪያቱል ኢስላሚያ ሊዐላቀቲ አልዱወሊያ፣ ኢቲጂሀት ጀዲደቱ ሊልፊክር ወልመንሀጁል ኢስላሚያ፣ አዚመቱል ዐቅል አልሙስሊም፣ አልዑንፍ ወኢዳረቱ አልሲራዕ አሲያሲ ፊ ፊክሪ አልኢስላሚ በይነ አልመብዳእ ወልኺያር፣ አዝመቱል ኢራደቱ ወስዊጅዳኑል አልሙስሊም፣ አልረእዩጡ አልከውኒያ አልሀዳረቱ አልቁርአኒያ፣ ኢስላህ አልኢስለማ አልሙዓሰራ›› ይጠቀሱበታል፡፡ በ2021 ወደ ማይቀረው አኺራ ተሸገሩ አላህ መልካ ሥራዎቻቸውን ሁሉ ይበላቸው በሰፊው ምሕረቱ ያካባቸው፡፡